# ትክክለኛው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር



A calendar as ancient as Enoch, a Christianity dating from the birth of Christ, a computes as great as Demetrius, a land of refuge to the lord _ all this is here!

ኅሩይ ስሜ

www.ethiopianorthodox.org

# ትክክለኛው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ፤አለሙ የተሳሳተውን የጎርጎርዮስ ዘመን አቆጣጠር መከተል፣ ዛሬ ከጌታችን ልደት በኋላ

ጎሩይ ስሜ 2000 ዓ.ም መሆን 2000 ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

## ማውጫ


ለመፀሀፈ መንደርደሪያ የሆነው አጠቃሎ ........ 9

ምእራፍ አንድ

መግቢያ እና መነሻ ........ 11

ምእራፍ ሁለት

የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ታሪካዊ ፍንጮች ........ 18

ምእራፍ ሶስት

የግብጽ /ቅብጥ/ ቤተ ክርስቲያን ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙትነት ........ 37

ምእራፍ አራት

ኢትዮጵያ እና ጌታችን ‘ሰመነ ሥጋዌ ........ 58

ምእራፍ አምስት

የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያ ዮልዮሳዊ ነውን? ........ 63

ምእራፍ ስድስት

ክርስቲያናዊው ዘመን አቆጣጠርና መንደርደሪያው የሥነ-መለኮት ትምህርት ........ 73

ምእራፍ ሰባት

የምእራባውያን ዘመን አቆጣጠር አጭር ታሪካዊ አመጣጥ ... 86

ምእራፍ ስምንት

የጌታችን የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደትና የሄሮድስ መንግስት ........ 96

ምእራፍ ዘጠኝ

የቅድስ ሉቃስ ወንጌል ታሪካዊ ማመልከቻና አይሁዳዊው ጆሴፈስ የፃፈው የአይሁድ ታሪክ ........ 121

ምእራፍ አስር

አቡነ አውላቤዎስ ስለ ጌታችን ልደት የገለፀው ማስረጃ........ 126

ምእራፍ አስራ አንድ

ሊቁ ገማልያል ስለ የገሊላው ይሁዳና የጽፈት ዘመን የተናገረው ማመላከቻ ........ 132

ምእራፍ አስራ ሁለት

በዘመን መቁጠሪያው ላይ ያለ ተቃውሞ ........ 139

መደምደሚያ ........ 144


www.ethiopianorthodox.org

## የጥናታዊው ፅሑፍ መንደርደሪያ ሆኖ የቀረበ አጠቃሎ

## (Abstract)

ለዚህ መጻሐፍ ጥናት ማዘጋጅያ አርእስት ትክክለኛው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር አለሙ የተሳሳተውን የጎርጎርዮስን ዘመን አቆጣጠር መከተልና ዛሬ ከጌታችን ልደት በኃላ 2000 ዓ.ም መሆን የሚል ሲሆን በዚህ ጥናት በጠቅላላ የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ/ክ አባቶች በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ትክክለኛ ክርስቲያናዊ የዘመን መቁጠሪያን እንዳስረከቡን የሚያሳዩ የተለያዩ ፍንጮችን ከጥንታዊ የታሪክ ማስረጃዎች ጋር በማጣቀስና ጠቅለል ባለ መልኩ የጎርጎሪዮሳውያኑን ስህተት አጉልቶ የሚያሳይ ተደርጓል:: ብሎም በህዝብ ዘንድ ስለ ዘመን መቁጠሪያው ያለውን ሃሳብ፣ ድጋፍና ተቃውሞን ጨምሮ የሚያሳይ ይሆናል::

ኢትዮጵያ ያላት ልዩ የዘመን መቁጠሪያ ከጎርጎሪያዊው ጋር ሲነፃፀር በይበልጥ የተሻለ ክርስቲያናዊ ዘመን መቁጠሪያ የሆነ ሲሆን በዚህም የጌታን ልደት ዘመን በአግባቡ ያገናዘበና የዘገበ መሆኑን የሚያሳዩ ታሪካዊ ምንጮች ይጠቀሳሉ:: በዋናነት ትኩረት የሚሰጠው ክፍል በሀዲስ ኪዳን ወይም በክርስትና ዘመን ባለው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ነው:: በተቃራኒው ደግሞ የዩልዮስና ጎርጎርዮስ ዘመን መቁጠሪያ ብሉያትንና ሐዲስን በከፈለው በጌታ ልደት ቀንና ዓ.ም ላይ የተዛባና አንድ ወጥ ያልሆነ መሆኑን ለማሳየት የሚያስችል





ስራ የያዘ ክፍል ይኖረዋል:: እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ብዙ ኢትዮጵያውያን ደፍረው ይህንን ለመግለፅ ሲበረቱ አይታዩም:: በምእራቡ አለም ደግሞ ሀቁን የማወቅ ችሎታና መረጃም ቢኖራቸው እንኳን የምእራባውያንን ስልጣኔ ብሎም የካቶሊክና የፕሮቴስታንት ሃይማኖትን የበላይነት የሚያስደፍር ስለሚመስላቸው ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ለመሸፋፈንና ለማደናገር ሲጥሩ እናስተውላለን:: በዚህም ከራሳቸው ተርፈው ሌላውን አለም የተሳሳተ የዘመን መቁጠሪያ ተጠቃሚ እንዲሆን አድርገውታል:: ስለምን ይህ እንደሆነ ጥናቱ የሚዳስሰው ክፍል ሲኖረው በተያያዥ የኢትዮጵያን የዘመን አቆጣጠር አስመልክቶ ህዝቡ የሚያነሳው አስተያየት፣ ጥያቄ፣ ድጋፍና ተቃውሞ ሊዳሰስ የሚያሻው ክፍል ነው:: በጠቅላላው በጥናቱ ዙሪያ ትክክለኛው የዘመን መቁጠሪያ የትኛው እንደሆነ ለማሳየት የሚያስችል ክፍል ሲኖረው በይበልጥም የጥናቱ ውጤት «የኢትዮጵያ አስራ ምእት የአለም አስራ ምእት ነው» ወደ የሚያስብልበት መንገድ የሚያሸጋግረን ነው የሚል ግኝት አለው::




www.ethiopianorthodox.org

# ምእራፍ አንድ

## መግቢያ

የሰው ልጅ ባሳለፈው ረዥም ታሪክ ውስጥ አያሌ ክስተቶች የየራሳቸውን ጥላና አሻራ ጥለው አልፈዋል፡፡ በዚህ ረዥም ዘመን ውስጥ ሰው የታዘበውንና የገጠመውን አካባቢያዊና ማህበራዊ ችግሮች እንዲሁም ደስታዎች በትዝታ ማህደር ውስጥ ከትቦ ለትውልድ ያወርስ ዘንድ በማንኛውም አጋጣሚ ሲጥር ኖሮአል ይህንን ተከትሎ ይመስላል እንግዲህ የዘመን መቁጠሪያ /Calender/ እና የዘመን አቆጣጠር ለመጀመሪያ ጊዜ ለመመስረት የቻለው፡፡ (Breasted, 1916)

በሌላኛውና በመንፈሳዊው ገፅታ ደግሞ የዘመን አቆጣጠር መፅሀፍ ዘመንን ባስገኘው በእግዚአብሔር የአለምን መፍጠር ወይም ፍጥረተ አለምን ተከትሎ ከመጀመሪያው ጥንተ እለት የተነሳ መሆኑን ያስረዳል በዚህ መልኩ የዘመን አቆጣጠርን የሚገልፀውና የሚያስተምረው የቤተክርስቲያን መፅሀፍና ትምህርት ባሕረ ሐሳብ (የሐሳብ ባህር ወይም የቁጥር እንዲሁም እውርን የሚመራ ወዘተ) በመባል ይገለፃል፡፡ (አስራት እና ገብረሕይወት፣ 1987)

ከዘመን አቆጣጠር አጀማማር ጋር የተያያዘው ገለፃ እንደሚጠቁመው ህዝቦች የታሪክና የተፈጥሮ ክስተቶች ጋር ትስስር ያለውን ማህበራዊ ህይወት ለመመዝገብ ብሎም ለመጠበቅና አስቀድሞ ለመወሰን ይቻላቸው ዘንድ የተመሰረተ



www.ethiopianorthodox.org

ስለ መሆኑ ብዙዎች ይናገራሉ:: የዘመን አቆጣጠር የየትኛ ውም ስልጣኔ ውስጥ ጉልህ ቦታ ያለውና ለዚህም በአለም ውስጥ የተነሱት የግብፅ፣ የባቢሎን፣ የቻይና፣ የቀይ ህንድ የኢንካና አዝቴክ እንዲሁም የማያ ስልጣኔዎች ለዚህ ህያው ምስክሮች ናቸው (World History, 1950)

የዘመን አቆጣጠር ዋነኛ ጥቅሙ ለእርሻ ስራ የወራቶች፣ የወቅቶች ዑደትን አስቀድሞ ለመተንበይና ለማወቅ እንዲሁም አስፈላጊውን ዝግጅት ለመከወን፤ ለንግድና ለጦርነት ተዛማጅ ጥንቃቄዎችና ጉዞና ዘመቻ ለማድረግ፤ ለአስተዳደርና ለሃይማኖት መደበኛ ቀኖችንና በአሎችን ለመወሰን እንዲሁም ዘመናዊ አሰራርንና ቁጥጥርን ለመጀመር /Management/ የግድ የሚያስፈልግ ጥበብ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም::

በአለም ስልጣኔ ውስጥ ቀደምት የሆነውና ዘመናዊው የዘመን አቆጣጠር በግብፃውያን ከጌታችን ልደት በፊት በ3000 ዓመት ግድም የተጀመረ ሲሆን በ365 የፀሀይ ቀንና በ12 ወር ከ5 ቀን የተዘጋጀ ነበር (Gordon, 1970)

እንደ ባህረ ሀሳብ ዋነኛ አዘጋጅ ሊቅ አቡሻከር ደግሞ የባህረ ሃሳብ ቀመር እና ትምህርት ስለ ዘመን አቆጣጠር መጀመሪያ የሚነሳው በመጀመሪያ ከሙሴ ከዚያም ከሐዋርያት በማስከተልም ከየግብፅ ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ዲሜጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት የተሰጠ ጥበብ መሆኑን ነው:: ለማንኛውም ወደ ኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ስንመጣ በየትኛው የጥንት



ዘመንና በማን ዘመን ይቆጠር እንደነበር ሙሉ ማስረጃው በግልፅ አይታወቅም:: ነገር ግን ክርስቲያናዊው የዘመን አቆጣጠርን ከቅዱስ ድሜጥሮስ የባህረ ሃሳብን ትምህርት ቀጥሎም የደቀ መዝሙሩ የአቡሻከር ቅንብር ስለ መከተላችን ብዙና ግልፅ ማስረጃዎች አሉ:: (ጌታቸው፣ 1993)

ከዚህ ጋር የክርስቶስ ልደትን በተመለከተ ለመላው አለም የክርስቲያን ዘመን ወይም አመተ ምህረት መሰጠት ተያይዞ በግልፅ እንደሚታወቀው በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞና ሀገራችን ካላት ቀደምት የብሉይና ኦሪት ግንኙነት ጋር ትክክለኛውን የጌታን ልደት ለመመዝገብ እንደረዳ ይታመናል::

በመሆኑም የኢትዮጵያውያን የዘመን አቆጣጠር ከክርስቲያናዊው ዘመን / Christian era/ እንዴት እንደሚጀምር ብሎም በተያያዥ በህዝቡ ዘንድ ያለውን ግንዛቤና እውቀት ምን ያህል እንደሆነ ማጤን እና የፅሁፍ ማስረጃ መተው ለወደፊት ለሚመጣውም ትውልድ አስፈላጊና ወሳኝ ነው::

ከዚህም ባሻገር በዘመን አቆጣጠሩ ዙሪያ ባለው ተቀባይነትና ተቃውሞም የተጠቃሚውን ሀሳብ ከወዲሁ መረዳትና ጥያቄውንና አመለካከቱን መገምገም ከባህል መጠበቅና ቅርስን ከመንከባከብ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚያስችለው ያደርገዋል:: ስለሆነም ዘመን አቆጣጠራችን ካለው ማራኪና ልዩ ብሎም ጥልቅ ቅርስነት አኳያ በዙሪያው



www.ethiopianorthodox.org

በሚያውጠነጥኑ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ላይ ሰፊ ምርምር ማካሄድ እንዳለብን ጊዜው ጠቋሚ ያደርገዋል::

**የጥናታዊው ፅሁፍ መነሾ /Problem/**

የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ቀመር ከቅድመ አቡሻክር ጊዜ ጀምሮ የነበረና ፍፁም የጠነከረ ልዩ እሴት ሲሆን አቡሻክር ደግሞ በተደላደለው መሰረት ላይ የፀናና መልካም የሆነ አስተዋጽኦ አበርክቷል:: ነገር ግን ብዙ ከሚጠበቅብን ከኛ ኢትዮጵያውያን ስራ ስላልተሰራ መላው አለም ስለ ትክክለኛው የዘመን መቁጠሪያና ዓ.ም ሊያውቅ አልቻለም:: ከዚህም በዘለለ የዘመን መቁጠሪያውን ትክክለኛነት የሚጠራጠሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን መበራከታቸው አሌ የማይባል ሀቅ ነው:: ይህንን በመያዝ ምዕራባውያኑ የለተያዩ ነቀፌታቸውንም ሰንዝረዋል:: ስለዚህም ዋነኛው ዘመን መቁጠሪያው የተሳሳተና አገሪቷን ወደ ሰባት አመት የሚጎትት ነው እያሉ መናገራቸውን አዳምጠናል:: ይህ ችግር ለጥናቱ መነሾ በመሆን የነዚህን የተከናወኑትን የሃሳብና የእውቀት ልዩነት ለመሙላት ታሳቢ ያደረገ ፍንጭ ይኖረዋል::

**ማረጋገጫና ጥቅም /Justification/**

ትክክለኛውን የክርስቲያኖች ዘመን መቁጠሪያ መነሻን የያዘው /Christian era/ የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያ ምንጩ የተካተተው በ«ባህረ ሀሳብ» የባእላት፣ የሰንበትና የቀናት



መቀመሪያ ወጥ ስራ ውስጥ ነው:: ይህ የባህረ ሀሳብ ቀመር እና ፍፁም ሚስጥር በአለም ላይ ትክክለኛውን የክርስቲያን ዘመን መጀመሪያ /Christian era/ በሰፊ ታሪካዊ ማገናዘቢያዎቹ ማመሳከሪያዎቹ እንዲረጋገጥ ያደረገ ሲሆን እነዚህን መረጃዎች በጥንቃቄ ለተረዳና ላነበበ ሰው የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያ የአለም ወይም ትክክለኛው ዘመን መቁጠሪያ መሆኑን ለመረዳት አይቸገርም:: ነገር ግን ምዕመናንም እንኳን በዚህ ትምህርት እውቀት መጎብኘታቸው ያጠራጥራል::

ይህ ጥናት መጠናቱ የማህበረሰቡን ጠቅላላ ንቃተ ህሊና የሚገመግምና ባህሉንና ሃይማኖቱን በምን መልኩ መጠበቅና ማወቅ እንዳለበት ያስተምራል :: አያይዞም በአለም ላይ ያለውን የባህል ወረራና ሉላዊነት ንቅናቄ በአስተማማኝ ክንድ ለመመከት በቂ ዝግጅትን የሚፈጥር መድረክ በመሆን ያገለግላል :: ይህ ደግሞ በጠንካራ ሁናቴ ነገ ሊነሱና በባህልና በሀይማኖት እንዲሁም ቅርስ ላይ የተሰሩ የማጥላላትና የመናቅ ሃሳቦችና ጥያቄዎችን ከስር ምንጫቸው ለመረዳት ብሎም መፍትሄ ለማፈላለግ የሚያገለግልበት አመቺ ጉልበትን ይፈጥራል :: ከሁሉም በላይ ግን ስለ ሃይማኖታችን፣ ቤተክርስቲያናችንና ስለ ባህላችን ፍፁም የሆነ እና የታመነ መረጃ ማበርከት ስለሚያስችል ጥቅሙ የጎላ ነው ::



www.ethiopianorthodox.org

ጠቅላላ ዓላማ /General Objective /

በጠቅላላ ላለው እውቀት ዝንባሌ አስተሳሰብና አስተያየት በዘመን መቁጠሪያው ላይ ሰፊ ጥናት ማበርከት

የጥናቱ ንዑሳን አላማ /Specific Objectives/

ለዘመን መቁጠሪያው ያለውን ድጋፍና ተቃውሞ ምክንያት ማወቅ

1. በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ክፍሎች በማጥናት ስለ ዘመን መቁጠሪያው ያላቸውን ዝንባሌና አስተያየት መረዳት
2. ስለ ዘመን መቁጠሪያው ያለውን ጠቅላላ እውቀት፣ ትክክለኛነትንና ብቃት በህብረተሰቡ ዘንድ ማስተዋወቅ
3. በዘመን መቁጠሪያው ላይ ያለውን ጠቅላላ ግንዛቤ ከተለያዩ አቅጣጫዎችና መደቦች መተቸት

የጥናታዊው ፅሑፍ ጥያቄዎች /Research Questions /

የጥናቱ ጥያቄ የሚሆነው የሕዝቡ ጠቅላላ እውቀት በዘመን መቁጠሪያውን ትክክለኛነት በመገንዘብ ደረጃ ምንድን ነው የሚል ነው? በማስቀጠልም

1. ዘመን መቁጠሪያው አለም አቀፋዊ ትክክለኛ ይዘትና ቀመር ከክርስቶስ ልደት መጀመሪያ ዓመት /Christian era/ ሲለካ በኛ ትክክል መሆኑን ማሳየት
2. ማህብረሰቡ የዘመን መቁጠሪያውን ቀጣይነት በምን ያህል እየተንከባከበና እያረጋገጠ ነው?



3. ዘመን መቁጠሪያው ይቀየር የሚል ተቃውሞ ካለ የተቃውሞ ምክንያት ምንድን ነው?
4. የጎርጎርዮስን ዘመን መቁጠሪያ መውረስ ይገባል ለሚሉ ክፍሎች ዋነኛ ምክንያታቸውና ምንጩ ምንድነው የሚሉትን ያካተተ ይሆናል?

## የጥናቱ ስልት /Methodology/

በዚህ ጥናት ውስጥ በብቸኝነት እና በዋናነት የጥናት ስልት በመሆን የሚሰራበት ዘዴ ሰነዶችን የመመርመር /analysis on texts and documents/ ብቻ ሲሆን በጣም ውስን በሆነ መልኩ ሰዎችን ስለ ዘመን መቁጠሪያው ያላቸውን አስተያየት አስመልክቶ ቃለ መጠይቅ ይደረጋል::

## ዋቢ መረጃዎች /Source/

ከድህረ ገጽና በተለያዩ ጊዜዎች በዘመን መቁጠሪያው ዙሪያ የተደረጉ ክርክሮች የታሪክ መፅሀፎችና የቤተ ክርስቲያናችን አዋልድ መፃህፍት በማገናዘብና በማመልከት በዋቢነት በማጣቀስ ግልጽ የሆነ መረጃ ለማቅረብ ይሞከራል:: ከዚህ ውጭ የጐርጐሪያዊውን ሀሳብ ለማረጋገጥ የተፀፉ ስራዎችን ከመረጃ መረብ በማሰባሰብ አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም እንዲሰጥ ለማድረግ ታስቧል:: ይህም ጐርጐሪያውያኑ ስለ ልዩነታችንና ስለ ክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ ያሰፈሩትን ስራ ስህተቱን አጉልቶ ያሳየዋል የሚል ሀሳብ



www.ethiopianorthodox.org

አለን:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ስለ አቆጣጠሩ የተፃፉ የተለያዩ መፀሀፍትንም ለመዳሰስ ጥረት ይደረጋል::



## ምእራፍ ሁለት

### የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ታሪካዊ ፍንጮች

ዘመንን የሰው ልጅ መቁጠር የጀመረበትን ጊዜ በታሪክ መርምሮ ለመድረስና መረጃ የሚሆኑ ተጨባጭ ሳይንሳዊ ግኝቶችን ለማቅረብ እጅግ ያስቸግራል:: ይህ የሆነበት ምክንያት ዘመኑ እጅግ ሩቅ ከመሆኑ የተነሳ ነው:: ነገር ግን በጥቂቱ ያህል የሰው ልጅ ዘመንን ለመቁጠር ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች መካከል ዋነኛው በአመት ውስጥ የተከሰተን ታላቅ ክስተትና የሳደረውን ተጽእኖ ከዘመን አቆጣጠሩ ውስጥ በመጨመር አንድ ወጥ አቆጣጠርን ለመመስረት ሥእላዊ መግለጫ የመፍጠሩ ሁናቴ አንዱ ዘዴው ሆኖ ተገኝቶአል:: ይህን መሰል ጥንታዊና ቅድመ ታሪካዊ የዘገባና የዘመን አቆጣጠር በጥንት ጊዜ በአሜሪካ ይኖሩ የነበሩ የዳኮታ (Dakota) ቀይ ህንዶች ይጠቀሙበት የነበረ ዘዴና ጥንታዊውን ሰው የሚወክል ሂደት መሆኑን ማህበረሰባዊ ታሪክ ያረጋግጣል::[1]

ይህን ካልን ዘንድ አለማችን ካስተናገደቻው ብዙ ታሪካዊ ክንውኖች መሃል የጌታችን የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልና የክርስትና ሐይማኖት ያሳረፈውን የሚያህል በጐ ተጽእኖን የሚወዳደር ምንም ነገር አልተገኘም:: ይህ አለማቀፋዊ እውነታነቱ ከሥነ-መለኮት ትምህርት ብቻ



www.ethiopianorthodox.org

የሚመነጭ ሳይሆን በታሪክም ተአማኒነት ያለው ስለ መሆኑ ብዙ አያነጋግርም:: ስለሆነም የጌታችን ልደት ውሉ እያደር አለም አቀፍ የዘመን መቁጠሪያ ድንበርና የአዲስ ዘመን ከፋች (beginning of the Christian era) መሆኑን ምእራባውያን፣መለካውያን ምስራቃውያኑ (Greek Orthodox) እንዲሁም በኛ ዘንድ ያለው ዘመን መቀጠሪያ ህያው ምስክር ነው:: ስለሆነም የጌታችንን የልደት ዘመንን በቅጡ መረዳት ዘመነ ሐዲስን ወይም ዘመነ ክርስትናን (Christian era) በጥልቅ ለማወቅ እንዲሁም የዘመን መቁጠሪያን ለመመስረት በጣሙን ውስኝና ያለ እርሱ የማይቻል መሆኑን እንድንገነዘብ ያደርገናል::

ይህ እወነታ ደግሞ የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያና የምእራቡ ዓለም የሰባት ወይም ሰምንት አመታት ልዩነት እያሳየ እንዲገኝ ዋናው ምክንያት ሆኖአል ወደ ሌሎቹ ተዘዋውረን ታሪካዊ ዳሰሳን ከመስጠት በፊት ስለ የራሳችን የዘመን አቆጣጠር አመጣጥ ምንነትና ትውፊት ወሳኝ የሆኑ ታሪካዊ ምልከታዎችን ማየት እንዳለብን ግልጽ ነው:: የክርስትና ሐይማኖት ከአምላካችን ከክርስቶስ ጀምሮ እዛሬ ላይ ኦርቶዶክስ ርትእት እስክትባል ድረስ ቅዱሳን ሐዋርያት ብሎም ሐዋርያነ አበው ከዚያም ጳጳሳት አባቶች እያለ ተያይዞ መምጣቱን በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ እና አዋልዳት ንባብ ላይ ተጠቅሶአል:: ይልቁንም በፊት አሰቀድሞ በጌታ ልደት ዘመን



በግብፅ፣ ሰሜናዊ ሱዳን፣ እና ኢትዮጵያ አምላክ በሰደት መኖሩ በኋላም በዘመነ ሐዋርያት በግብፅና፣ በሰሜን አፍሪካ ፣ በሶርያ እና በአረብ ሀገር ድረስ ወንጌል መነገሩ ስለ አምላክ መወለድ መበሰሩ ብሎም ይህ ሁሉ መቼ እንደሆነ ከዘመኑ ጋር መሰበኩ ተዘግቦአል::[2]

ኢትዮጵያውያንም የእዚህ እፃ ተቋዳሾች እንደሆኑ በመፅሀፍ ቅዱስ ላይ በግልጽ እንደተፃፈው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በ34/35 ዓ.ም የክርስትናን ጥምቀት በረድኡ በቅዱስ ፊሊጶስ ተጠምቆ ወደ ሀገሩ ደስ እያለው እንደገባ ይገልፀልናል (የሐሥራ8:26) [3]

በዚህም ስለ ጌታ ልደት የዘመነ ፍዳ ህልፈት የአመተ ምህረት መሰጠትን በጥልቅ ከሚያወሳው ከረድኡ ፍሊጶስ ተረድቶ ለትውልድ እስከ ትውልድ እንዲተላለፍ አድርጓል:: ይህ ሲባል የጌታ ልደት ዘመን በትክክል ተዘግቦ እኛ ጋር ስለ መድረሱ በሌላም ወገን ማረጋገጥ ይቻላል:: ይኸውም የግብጽ የመጀመሪያ ሊቀ ጳጳስ የነበረው እና የክርስትናዋ መንበር መስራቸ ቅዱስ ማርቆስ ከወንጌሉ ጋር የጌታን የልደት ዘመኑን ከልደቱ ታሪክ ጋር አስተምሮ ለቅዱሳኑ ሐዋርያነ አበው ያወረሰው እስከ ቅዱስ ድሜጥሮስ (230 ዓ.ም) ሊቀ ጳጳስ እና የባሕረ ሐሳብ መስራች ቀጥሎ ሲወርድ በ13ኛው ክ/ዘመን ላይ በአባ አቡሻከር ማብራሪያ የሚሻገረው የኛው የባሕረ ሐሳብ ትምህርትና ዘመን መቁጠሪያ የጌታችንን የልደት ዓመት እና



www.ethiopianorthodox.org

ቀን በትክክለኛው እና በእውነታኛው ቀንና ዓመት ላይ ዘግበው እንዳወረሱን አመላካች ነው።

ይህንን ተከትሎ በትውፊት እንደሚነገረው «ከጌታችን እግር ስር በልደቱ ጊዜ ከስገዱት የጥበብ ሰዎች አንዱ ኢትዮጵያዊ ነው» የሚባለውንም ማጤን የስፈልጋልስ[4] በአንድምታ ወንጌል ዘ ማቴዎስ ምእራፍ 2 ቁጥር 1 ጀምሮ ስለ ሰብአ ሠገል (የጥበብ ሰዎች) በሚገልጸው ክፍሉ ይህንን ማንበብ ይቻላል።

« [የፋርስ ሰዎች ለሰብአ ሰገል] ደርሳችሁ መጣችሁን አሏቸው? አዎን አሉ። ምልክት አላችሁ አሏቸው። እናቱ ስንቅ ስጥታን ይህ ሁሉ ሠራዊት እየተመገበው ባያልቅ ክቡር ነገር ነው ከተማ ይዞ መግባት አይገባም ብለን በአፋአ ትተነው መጥተናል። አሉዋቸው እስኪ አሳዩን አሏቸው። ቢሄዱ ሲጤስ አገኙት ከዚህ የተነሳ በእሳት እንጂ አምልኩ ሲለን ነው ብለው በእሳቱ የሚያመልኩ ሆነዋል። » ይላል

ይህ የጥበብ ሰዋች ከፋርስ ተነስተው ጌታን ካዩ በኋላ ሀገራቸው ሲገቡ የገጠማቸውን እና የጤሰውም እመቤታችን የሰጠቻቸው የገብስ ዳቦ መሆኑን የሚያወሳ ለብዙ ታሪካዊና ሥነ- መለኮታዊ ሚስጢራት ማመላከቻ የሆነ ገፀ ንባብ ነው።

እነኚሁን የጥበብ ሰዎች የፋርስ ነገሥታት የምሥራቅ ነገሥታት እንዲሁም ሰብአ ሰገል በማለት መጽሀፍ ተአምረ ኢየሱስ በምእራፍ ሰምንት ከቁጥርም 2-3 ጀምሮ



ይጠራቸዋል። በታሪክ እንደ ሚታወቀው በፋርስ ከገኑት አምልኮዎች መካከል አንዱ የእሳት አምልኮ (fire worshiping persians and the Magai) እንደ ነበር ተዘግቦአል። ይህ በቁሙ የአንድምታውን ታሪካዊ አመጣጥ በማስረጃነት ያጠናክረዋል።

ፀሀፊው በ1997 ዓ.ም ላይ እንደሚያስታውሰው በዝዋይ ሀይቅ ላይ በምትገኘው በደብረ ፅዮን ደሴት ላይ ባለችው በቅድስት ድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን አለቃ የነበሩት አባት ስለ ቦታው ታሪክ ሲናገሩ «የጥንቱ ኢትዮጵያውያን በእሳት ምልክትነት ያመልኩ ነበር ያሉትን በዚህ አጋጣሚ ለማስታወስ ይፈልጋል። ስለ ነገሩ በዝርዝር ሲያስረዱ እንዲህ እያሉ ይጀምራሉ።

«በጥንት ጊዜ ዮዲት የምትባል ንግስት ተነስታ አብያተ ክርስቲያናትን እየተኮሰች ንዋያተ ቅዱሳኑን እየዘረፈች ወደ አክሱም ተቃረበች። ይህንን ያዩ አባቶች ታቦተ ፀዬንን ይዘው ሸሹ። ዮዲትም አክሱምን ከበረበረች በኃላ ታቦተ ጽዬንን ይዘው የሸሹትን ፍለጋ ማሳደድ ጀመረች። አባቶችም ብዙ ተጉዘው ዝዋይ ቢደርሱ ባህሩ ወሰን የሌለው ሆኖ አገኙት። ወደያውም ከዳርቻው ላይ ከተቆረሰ መሬት ላይ ወጥተው ወደ ታላቅ የሆነው ተራራ (ደብረ ጽዬን) ገቡ። (ዛሬ ላይ ቦታው ቱሉ ጉዱ ይባላል።) ታቦተ ጽዮንንም ማሳረፊያ ቦታ ሲፈልጉ በእሳት ምልክትነት ያምኑ ነበርና እሳት የወጣልን ቦታ እናሳርፋታለን ብለው ሁለት ቦታ ሲሞክሩ አልወጣ አላቸው።



www.ethiopianorthodox.org

በሶስተኛ ጊዜ ሲሞክሩ ከተራራው አናት ላይ እሳት ወጣላቸውና ዋሻ ፈልፍለው ታቦተ ጽዮንን የሰደቱ ዘመን እስኪያልፍ አስቀምጠው ጠበቋት» ብለዋል::[6]

ከላይ ካለው የጥበብ ሰዎች ታሪክ ጋር የእሳት አምልኮው ጉዳይ መጋጠሙና የጥበብ ሰዎች መሃል አንዱ ኢትዮጵያዊ ነው የሚለውን መፀሀፍ ቅዱሳዊ መረጃ የሚያጠናክር ያደርጋዋል:: በታሪካዊው ትንታኔ ለሚመለከተው ደግሞ በዮዲት ጉዲት ወረራ ወቅት ማለትም ከ 10ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ክርስትናን በቅጡ ሊረዳ የሚያስችለው የመስፋፋት ደረጃ ላይ በመሆኑ በአክሱምና በሰሜን ሸዋ ድረስ በእሳት የሚያመልኩ መኖራቸውን የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም::

ሁሉም ሰው እንደሚያውቀው ግን ኢትዮጵያውያን በመስቀል በአል ወቅት እንደሚደረገው ክብረ በአሉ ላይ ችቦን በማንደድና እጣን በመጨመር መስቀሉ የመገኘቱን ታሪክ አርአያ በማድረግ ተመሳሳይ ሥራ እነኝህ የጥንቱ አባቶች ሰርተው እንደነበር ወይም ሌላ መጠናትና መመርመር ያለበት የታሪክ ክፍል ያደረገዋል:: የቅድስት እሌኒ የመስቀሉን ማግኘ ት ታሪክ በአብዛኛው የሚታወቅና በየአመቱ አብነትዋን ህዝቡ የሚደግመው በመሆኑ እርስዋም ደመራን የመደመርዋን እሳት ለኩሳ እጣን የመጨመርዋን ከዚህም በኋላ እጣኑም መስቀሉ የተሰወረበትን ተራራ የጠቆመበትን ታሪክ መሆኑን



የሚያውቀው አማኝ የታቦተ ጽዮንን ማርፊያ በዚያው ሥርአት ፈልገው ነበር የሚሰኘው ሀሳብ ይበልጥ ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርገዋል::

የከርሰ ምድር ቁፋሮ ካስገኛቸው ተጨባጭ የታሪክ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት ብቻ ከሆነ ብዙ ጊዜ ከሚታወቀው የድንጋይ ላይ ፀሁፍ በመነሳት ክርስትና በኢትዮጵያ ምድር የመሰበክ ነገር «ሀ» ብሎ የሚጀምረው ከአብርሃ ወ አጽብሃ የመጠመቅና የከሳቴ ብርሃን አቡነ ሰላማ ዘ ኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ መሰኘት ጋር የተያያዘ ሆኖ ብቻ ነው:: ነገር ግን ከዚህ በፊት ክርስትና በኢትዮጵያ ህዝብ ጉያ ውስጥ መኖርዋን የሚያሳዩ ብዙ የታሪክ ፀሃፊዎች ግኝትን መመልከት ጉዳዩን በይበልጥ ያብራራዋል::

ከነዚህም መሃል ዶ/ር ትርሚንግሃም «ክርስትና በአክሱም ውስጥ ከባይዛንቲዩም (ቁስጥንጥንያ) ጋር ባለው የባህርና የንግድ ግንኙነት ምክንያት ቀደም ባለ ጊዜ ውስጥ እንደገባ ይታወቃል» ብለዋል:: [7]

በተመሳሳይ መልኩ ፕሮፌሰር ታደሰ በበኩላቸው የመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የአክሱም ንጉስ የነበረውን የዞስካለስን የግሪክ (በፅርእ ቋንቋ) እውቀትና የንግድ ግብይት ብልህነት ቅርብ ከነበሩ በዘመኑም ክርስትናን ከተቀበሉ የግሪክ ሰዎችና እንዲሁም አማካሪዎች በአክሱም ታላላቅ የወደብና የንግድ ከተሞች ውስጥ ተቀምጠው በሚያደርጉት ሥራ



www.ethiopianorthodox.org

የተስፋፋ እንደነበረ ግልጽ ነው ካሉ በኋላም የአብርሃ ወደ ክርስትና ሃይማኖት መግባት የተገኘው ህዝብ ቀስ በቀስ ወደ ክርስትና መግባት ባስከተለው መጠናከር እንዲሁም የሮማውና የቁስጥንጥንያው የንግድና የባህር ጉዞ የውጭ ግንኙነት ካለው ተፅእኖ እና የአክሱሙ አጋር ሀገር የቁስጥንጥንያው መንግሥት ሙሉ በሙሉ ክርስቲያናዊ መንግስት መሆን ጋር የተይያዞ የመምጣት ሂደት ነው ሲሉ ይደመድማሉ:: [8]

በተያያዥ የኢትዮጵያን ክርስትና ያጠኑ ሌሎች የታሪክ ፀሀፊዎችም ክርስትና በኢትዮጵያ ጥንታዊነቱ ከአጼ አብርሃ የቀደመ ስለ መሆኑ ይስማማሉ:: ጥንታዊ ከሆኑ የታሪክ ፀሀፊዎቹን ስንመለከት ደግሞ ይህ ጉዳይ ይበልጥ እየጠነከረ የማያጠያይቅ ሀቅ የሚያደርገው መሆኑን መረዳት ይቻላል::

ለዚህም ኘሮፌሰር ስርገው እንዳደረጉት ምርምር ጥንታዊያን (በዘመኑ የነበሩ) (Contemporary) የታሪክ ፀሀፊዎች አበውን በዚሁ ሃሳብ ላይ ይጠቅሳሉ:: ለምሳሌም ያህል ኦሪጅን (origen) እንደፃፈው «ወንጌል በመላዋ ኢትዮጵያ አልተሰበከም በይበልጥ ከወንዙ ማዶ ለሚኖሩት አልተሰበከም» ይላል:: እንደ የቤተ ክርስታያን ታሪክ ፀሀፊ ሩፊኖስ በተጨማሪም ሶክራተስ ደግሞ «ሐዋሪያት ወኔልን ለመስበክ እጣ ሲጣጣሉ ቅዱስ ማቴዎስ ኢትዮጵያን እንዲሰብክ እጣ ደርሶታል:: በዚያም ሐዋርያዊ ተልእኮ ስማእትነት በኢትዮጵያ ተቀብሎአል» ብለው የፃፉት ይገኛል:: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ



አባት በመባል የሚታወቀው አውሳቤዎስ «ጃንደርባው ለወገኖቹ ሐዋሪያ ሆነ» ሲል የመጀመሪያውንና ጥንታዊውን እንዲሁም መጽሀፍ ቅዱሳዊውን መረጃ ያጠናክራል ዮሐንስ አፈወርቅ በጥቅምት እለት በሚነበበው ድርሰቱ ላይ «ኢትዮጵያውያኑም ሰምተው ተረዱ» ሲል በሐዋርያት ሥራ ም2 ቁጥር 1 ያለውን የመንፈስ ቅዱስ መውረድና ልሳናት ለሐዋርያት መገለጥ አያይዞ የኢትዬጵያውያን በቦታው መገኘትና ማመንን ያመጣል:: እንዲሁም «የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሐዋሪያ ቅዱስ ቶማስ ነው በማለት ይዘግበዋል:: አባ ጀሮም ደግሞ ቅዱስ እንድሪያስ ነው» በማለት ሌላ መረጃ ይሰጣሉ::

ኘሮፌሰር ስርገው ሲያስረዱ ገና በ1ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ የክርስቲያን ማህበራት የነበሩና እነኚህም የጃንደረባው ስብከት ፍሬና በርሱ ስራ ላይ የግሪክ ክርስቲያን ነጋዴዎች አገልግሎት የተደመረበት አንደ ነበረ ይጠቁማሉ [9]

በመፀሀፍ ቅዱስ የወንጌል ምንባብ ላይ ትኩረት ሰጥተን እንድምታዊ ትርጓሜን ካጠናን ስለ የጌታችን ልደት ሁናቴ በሥፋት ከፃፉት መካከል የቅዱስ ማቴዎስን እና የቅዱስ ሉቃስን ወንጌል እናገኛለን:: ቅዱስ ማቴዎስ የወንጌሉን መጀመሪያ በማቴዎስ ምዕራፍ 1 ላይ «የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መፀሐፍ» በማለት ይከፍታል:: ይህም ዋናው ምክንያት ትንቢት የተነገረለት



www.ethiopianorthodox.org

ሱባኤ የተቆጠረለት የዘመነ ፍዳ አሳሳፊዋ የዘመነ ምህረት ሰጭዋ ጌታ መድሐኒአለም እርሱ ክርስቶስ የመወለዱን ዘመን ለመንገር ነው:: አንድም አዲስ ዘመን ወይም ዘመነ ምህረት ሆኖአልና ሲል ሰው ሁሉ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አንድ ብሎ እንዲቆጥር ነው:: ይህም በምን ይታወቃል ቢሉ አብርሃም ለኪዳነ ኦሪት መሰረት ነው:: ጌታችን ደግሞ ለኪዳነ ሀዲስ ሰጭዋ ስለሆነ ሁለቱ ዘመኖች መገለጣቸውን ለማጠየቅ «የአብርሃም ልጅ» ብሎ አመጣው ማለት ነው::

ቅዱስ ማቴዎስ ስለዚህ በሰበከበት ቦታ ሁሉ ዘመኑን አንድ ብሎ የ5500 ዘመን ህልፈትን ተረድቶ እንዲቆጠር ያስተምራል:: ከላይ ባየነው መሠረት ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌል ሰብኮባቸዋል ከተባሉት ቦታዎች አንዷ ኢትዮጵያ ናት:: ስለዚህ የጌታን ልደት እንድንረዳ እና ክርስቲያናዊ ዘመን መቁጠሪያ እንዲኖረን ምክንያት ሆኖአል ማለት እንችላለን::[10]

ቅዱስ ሉቃስም ስለ ጌታ ልደት ወራቱን በብርዳማው ጊዜ መሆኑን ዘመኑን ደግሞ በነገስታቱ ቄሬኔዎስ በሶሪያ ደጀዝማች በተባለበትና ሰው የሚቆጠርበት ትእዛዝ ከቄሳር /አክቴቪያን/ በመጣ ጊዜ እያለ ይጽፋል:: ከሌሎቹም መረጃዎች ጋር ስለ ደቡብ ንግስት ሳባ ከጌታ መዋእለ ስብከት ትምህርት ያለውን ታሪክ በወንጌሉ ማቴዎስ ጽፎአል (ማቴዎስ 12:42) ይህንንም ማለቱ እና ስለ ኢትዮጲያ መጥቀሱ ጌታ እምነትዋን እንደመሰከረላት ወደ ሃገርዋ በእምነትም እንደገባች ምግባሯ



ህዝበ እስራኤልን መገሰጽያ እንዳደረገላት ብቻ ሳይሆን በእርሷ ህዝቡንና ሀገሩን መናገር ልማድ ነውና የኢትዮጵያ ሰዋች አምልኮ በአሪት የመሆኑን ነገር ሊያመለክት ወደ በነቢያት ትንቢት ያልቀረቡትን፣ ዘመኑንም የልተረዱትን የጌታቸን ዘመን እስራኤላውያንን የበለጡ መሆናቸውን እንዲሁም በጌታ ዘመን ኢትዮጵያውያን መገለፁን ተረድተው ለማመንም የፈጠኑ መሆኑን የሪጋግጣል ለዚህም ነው በወንጌለ ዩሐንስ (20:29) ጌታ «ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው::» ያለው ለኢትዮጵያውያን ነው የሚባለው::[11]

ሌሎች የኢትዮጵያን ክርስትና ያጠኑ ፀሀፊዎችም የክርስትናው ጥንታዊነት ከአፄ አብርሃ የቀደመ ስለመሆኑ ይስማማሉ:: ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የሜሮዌ ሰው እንጂ አትዮጵያዊ አይደለም በማለት የሚከራከሩ ሌሎች ሰዎች ቢኖሩም የመረጃቸው ተጨባጭነት ግን አይታይም::[12]

ይህንንም የሚያስብለው ሜሮዌ በአይሁድ ሃይማኖት የተጠናከረ ማህበረሰብ ያለው ሰልጣኔ ያለመሆኑ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ወደ እስራኤል /እየሩሳሌም/ ሐይማኖታዊ ጉዞ የሚያደርግና የባህር ወደብ ባለቤት ጭምር ሥልጣኔ አለመሆኑ ነው::[13]

ይልቁንም በኢትዮጵያ ጥንታዊ የኦሪት እና የክርስትና እምነቶች መገኘት ልማዶቹም ሥር የሰደዱ መሆናቸውን ለመረዳት አያደግትም:: መረጃዎቹም በቀላሉ በየቦታው



www.ethiopianorthodox.org

የሚታዩ ሀቅ ሆነው እናገኛቸዋለን:: ስለሆነም ጃንደረባው ኢትዮጵያዊ ነው ከሚባለው ታሪካዊ እውነት ውጭ የጌታን የልደት አመት እንዲሁ ተገንዝቦ ለሀገሩ ሰዎች ያስተማረ ሐዋሪያ እንደሚያስኘው ለመረዳት አይከብድም ::

ይህ በዚህ እንደለ ትተን ስለ ኢትዮጵያዊው ዘመን አቆጣጠርን አስመልክተው ከፀፉት ጥቂት ኢትዮጵያውያን መከከል እንዳንዶቹ የሚሉትን መመልከት ይጠቅም እንጂ አይከፋም ከአቶ ጌታቸው ስንጀምር ስለ ኢትዮጵያዊው ዘመን አቆጣጠር በፃፈው መፀሀፍ ላይ የዘመን አቆጣጠሩን መጀመርያ ሙሴ በኋላ ሐዋርያት ቀጥሎም ቅዱስ ድሜጥሮስ እንዲሁም አቡሻከር እያቀነባበሩት ወደኛ እንደደረሰ ከገለፀ በኃላ «እኛ ኢትዮጵያውን መቼ ወደኛ እንደመጣነው በትክክል የሚታወቅ ነገር የለም ግን መጀመሪያ እራሳችን የደረስንበት የዘመን አቆጣጠር ሥርዓት እንደነበረን የሚያሳዩ አንዳንድ ምልክቶች አሉ :: በዚያም ላይ የውጭውን እወቀት በተደጋጋሚ በተለያዩ ዘመን እንዳመጣነው አያጠራጥርም »[14] ሲል የሃሰቡን ምልከታ ይሰጥበታል ሌሎች ይህንን ጥያቄ በሥፋት የልዳሰሱት ሆኖ የቀረበትም ሁኔታ አለ::[15]

የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ልዩ የሚደርገው ሌላው ክፍል አመቱን በአራት ወቅቶች የመክፈሉና እነዚህም ወቅቶች በቀን ሳይቀር የተከፋፈሉ መሆናቸውን በጥሞና ሰው እንዲያስተውለው አስገነዝባለሁ::



በዚህም መረጃ በብሉይ ዘመን የነበረው አቆጣጠራችን ኢትዮጵያዊ የሚያሰኘው እንደሆነ እንረዳለን:: ይህ ደግሞ ከዘመነ ሐዲስ በፊት ስለ አለው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የራሳችንና ምንጩም ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚነሳ በጣም ጥንታዊ ዘመን መቁጠሪያ ሥርአትና አቆጣጠር እንደሆነ እንረዳለን:: አንባቢያን ልብ ሊሉ የሚገባቸው ነጥብ ቢኖር በዚህ ስራ የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ዘመነ ብሉይን የማይጠቀልል በዘመነ ሀዲስ ብቻ ላይ የተደረገ ጥናት የመሆኑን ነገር ነው:: በዘመነ ሥጋዌ በግብፀ እስክንድርያ በሐዋርያው ማርቆስ የተመሠረተቸው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በቅዱስ ድሜጥሮስ ከዚያም በቅዱስ አትናቴዎስ አማካኝነት ለኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ቀቢነትና ሿሚነት የተቀበልነው እንደሆነ መረዳት እና የዘመኖቹን ክፍፍል ማጤን ያስፈልጋል::

ከዚህ በተለየ መልኩ አወሮፖውያኑ (እንግሊዛውያኑ) በቢ.ቢ.ሲ. የኢትዮጵያን አስራ ምእት ዘገባ) ስለ ጉዳዩ አፋቸውን ሞልተው እንደተናገሩት «የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የመነጨው በ42 ቅድመ ልደተ. ክርስቶስ በነበረው በጁሊየስ ቄሳር ትእዛዝ የወጣውን ዘመን መቁጠሪያና አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ በተወሰነው ውሳኔ የተቀበሉት ሲሆን አሁን ካለው ጎርጎሪያዊ ዘመን ጋር ልዩነቱ ከዚህ የተነሳ የመጣ ነው::» ብለዋል::



www.ethiopianorthodox.org

«ከዚህም ውጭ የአስራ ምእቱ በአል ለዳንሰና ለፈንጠዝያ ሰበብ እንጂ እወነታኛው አሥራ ምእት ከተከበረ ሰምንት አመት አልፎታል:: ብለውም ነበር:: ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ኢትዮጵያዊውን ዘመን አቆጣጠር ለማንቋሸሽ ብሎም እኛ ትክክለኛ ነን በሚል ከንቱ የኩራት መንፈስ የመነጨ ባዶ ጩኸትን የማሰተጋባቱ ጉዳይ ስለሆነ በተገቢው ቦታ የዚህን ሀሳብ ምንነትና ስህተት ለይተን ለማየት ወደሚያስቸል ምእራፍ ላይ እስክንደርስ ድረስ እናቆየዋለን::



## የምእራፍ ሁለት

## ማገናዘቢያ ጥቅሶች

1. James Breasted, ( PH.D) **Ancient Times : A History of the Early world.** (Boston, 1916) P.46
2. የሐዋርያት ሥራ 8:1-4 ፣የሐዋ 2:13፣ማቴ 28:16
3. በሐዋርያት ሥራ 8:39 ላይ የተጠቀሰው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በ34 ዓ.ም እንዴት ይጠመቃል ቢሉ ነገሩ የሚፈታው የጌታችን እድሜ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ 33 ዓመት ከ 3 ወር በመሆኑ በ34 ዓ.ም እያለ ከሚለው በመነሳት ነው:: በአመቱ ለስግደት ጃንደረባው ወጥቶ ከሆነ በ35 ዓ.ም ይሆናል:: እንደ ኦሪቱ ትእዛዝ መሠረት በአመት ወደ ኢየሩሳሌም መውጣት ህግ ነበርና በ34 አመት የመጣ ከሆነ ደግሞ ከ34 ዓ.ም ተጠምቋል በሚል አመቱን የተረዳነው ነው:: ክቡር ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም እስከ ዛጉዬ /አዲስ አበባ፣1966 ዓ.ም/ ገጽ 252 ተመልከት
4. ሚኒሊክ መርእድ አለሙ፣መጸሐፍ ቅዱስና ኢትዮጵያ (አዲስ አበባ፣1999 ዓ.ም ) ገጽ65-110
   ይኸው መጸሐፍ ላይ በስፋት ይህንን ጉዳይ ያብራራዋል:: ይልቁንም ማስረጃዎቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በመሆናቸው ትውፊቱን በመረጃ ያጠናከረውና



www.ethiopianorthodox.org

ያበለፀገው ስለሆነ በጣሙን «ይበል» የሚያሰኝ ሥራ ያደርገዋል:: እንደ አንድምታው ትርጓሜ (ዘ ማቴዎስ) የሰብአ ሰገል ነገስታት ስም ማንቱሲማር፣ ሜልኩ ፣ በድድ አስፋ ይባላል:: በድድአስፋ ምስራቃዊ ስም ሳይሆን የዛጉዌ ነገሥታት በኃላኛው ጊዜ የሚሰየሙበት ጋር ይመስላል የሚሉ ማመልከቻዎች ሲሰነዘሩ ኖረዋል::

5. ይህ ገፀ ንባብ በአንድምታ ወንጌል ዘማቴዎስ ያለ ቢሆንም በስፋትና ጥልቀት ለማየት ተአምረ ኢየሱስ /ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ማተሚያ ቤት 1990ዓ.ም/ 7ኛ ተአምር ገፅ 28-33 ያለውን ተመልከት::

6. <u>የካቲት 1997 ፀሀፊው ከደብረ ጽዮን ማርያም አስተዳዳሪ</u> ጋር ያደረገው ውይይት ስለ ቦታው ገለፃ ላይ የሚያስታውሰውን ከዚህ ፀሁፍ ላይ ገልፃል::

7. See, J. Triminghm, **Islam in Ethiopia** ( London. ,1952) P. 38 ይህንን መፀሀፍ መመልከት ያሻል ነገር ግን በውስጡ ስለተካተቱት ነጥቦች በኃላ ወሳኝ አስተየየት ይሰጥበታል::

8. See, Professor Taddesse Tamrat, **Church and State in Ethiopia 1270-1527** (Oxford, 1972) P.21



9. See; Triningham; p. 38 specially footnote 1; Professor Sergew Hable Sellassie, **Ancient and medievial Ethiopian History to 1270** ( Addis Ababa, 1972) P.97

10. See; Trimingham. P.38 the footnote indicates that according to Socrates and Ruffinos. Mathew preached in Ethiopia. በዚህ መረጃ ላይ ሁለት ታሪክ ፀሀፊዎች አንድ ቅዱስ ሐዋርያን ማንሳታቸው ለነገሩ ትኩረት የሚያሰጠው ያደርገዋል::

11. እንደ ቤተክርስቲያን ትምህርት በእስራኤል የነበሩ አይሁድ ጌታ በእጁ ገቢረ ተአምራት እየሰራ በአፉም ሌላ ሰው ያላስተማራቸውን ትምህርት እያስተማረ ቢሰብካቸው ስላልተቀበሉት ትንቢትና ነብዮችም ሁሉ ወደ እነርሱ እየተላኩ አምላካቸውንም በዓይን አይተው ያላመኑት የኦሪት ልጆች ሲያደርጋቸው በአለም ላይ ከእስራኤላውያን ውጪ ኦሪትን ለመቀበል እና የእግዚአብሔር ህዝብ ለመባል ከጣኦት አምልኮም ለመውጣት የፈጠኑ ኢትዮጵያውያን ኦሪትን ከወንጌል ጋር አስተባብረው በሰዓቱ የጌታን ፊት ሳያዩ እና ገቢረ ታምራቱን ሳይመለከቱ በመቀበላቸው ብፁአን ይሰኛሉ የሚል ትምህርት አለ::

12. ይህንን ጄ. ኤስ. ትሪሚንግሀም እስልምና በኢትዮጵያ (ለንደን 1952) ገፅ 38 ከማገናዘቢያ ጥቅስ ቁጥር 1 ላይ



www.ethiopianorthodox.org

የፃፉት ሲሆን ፕሮፌሰር ሰርገው በጥንታዊውና መካከለኛው የኢትዮጵያ ታሪክ መፅሀፋቸው ገፀ 97 ምላሹን ከፀሁፉ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ያስቀምጡታል::

13. See; Professor Sergew, p.97

14. አቶ ጌታቸው ኃይሌ ባሕረ ሐሳብ የዘመን አቆጣጠር ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋር (ኮሌጅቪል ሚኒሶታ፣ 1993 ዓ.ም) ገፀ 19 የአቶ ጌታቸው ሀሳብ ላይ "የኛ" ከጥንት አባቶቻችን ያገኘነው እና ሊቀ ነብያት ሙሴ፣ሐዋርያው ቅዱስ ድሜጥሮስ እያለ የሚመጣው ዘመን አቆጣጠር በማለት የለየው ይመስላል የኛ ጥንታዊ ዘመን አቆጣጠር የተባለው ግን ምን እንደሆነ ምንም ፍንጭ አልሰጠም ይልቁንም ከጥንት ከሊቀ ነብያት ሙሴ እስከ አሁን ድረስ ያለውን በአግባቡ ጠብቆ መያዝ በራሱ የኛ ሊያስብለው ይገባል ወደሚል ሃሳብ መምጣት ተገቢ ነው ለምሳሌም እንደ መጽሀፈ ሄኖክ ለማለት ተፈልጐ ነው አለበለዚያ የኛ ስለተባለው ጉዳይ ግልፀ ማስረጃ ማቅረብ ያስፈልጋል::

15. ሊቁ ፕሮፌሰር ሰርገው ስለዚህ ጉዳይ ሲያሰርዱ የጠቀሱት የሁለት የዘመን አቆጣጠር ጠበብት ሐሳብን ነው:: ይህም ጁልያን አፍሪካዊ የሚባል በ221 አመተ እግዚእ አለም ከተፈጠረ 5500 ዘመን ላይ ጌታ ተወለደ



ሲል መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን አበው እድሜ ደምሮ እጌታ ላይ ደረሰበት ሌላኛው ደግሞ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሳ ፓንዶር የተሰኘ ሰው የአለም እድሜ 5,492-3 ነው በማለት ካሳወቀው የተነሳ ልዩነቱ 7 እና 8 አመት ቅድመ ልደት ሲመጣ የኢትዮጵያው በጁልያን የጌታ ልደት 1 ዓመት በፓንዶር ደግሞ በ7 ዓመተ እግዚእ ነው ያለውን ተከትሎ በኛና በአወሮፓ መካከል ልዮነት አለ ሲሉ ቢያስረዱም አውሮፖውያኑ ከላይ የተጠቀሰውን የፓንዶርን ትምህርት ስለ መቀበላቸው የሚታወቅ ነገር የለም ይልቁንም የዘመን መቁጠሪያቸውን ምስረታ የሚጠሩት ከዲዮናሲዮስ ኤክሲጆስ በመሆኑ ይህ ምልከታ ግልጽ ያልሆነ ክፍል ሆኖ የቀረበ ይሆናል? ነገር ግን እንደዚህ ሆኖ የቀረበ ይሁን እንጂ ከዚህች ምልከታ በቀር ልዩነቱን በግልፅና በሰፊው የዳሰሰ ስራ ምንም አልተገኘም በዚህ ፀሁፍ ውስጥ የጁሊያን አፍሪካዊ ሀሳብ የሚለውን ከየጁልያን «ካላንደር» ከሚባለው ጋር ያለውን ልዩነት አሰተውል::



www.ethiopianorthodox.org

# ምእራፍ ስስት

## የግብጽ (ቅብጥ) ቤተክርስቲያን ከኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙት

በጥንት ጊዜ ግብፃውያኑ ዘመን አቆጣጠርን ከዋክብትን በመቁጠር ጀምረውት ነበር ይህንንም አምስት አለማትን (planets) ሠላሳ ስድስት ከዋክብትን ለቆጠራ በመለየት ለምርምራቸው መነሻና መወሰኛ የዘመኑን ማመላከቻና የማገናዘቢያ ነጥቦች አድርገዋቸዋል:: የጥንቱ ግብፃውያን ስለ ኮከብ ቆጠራ ስለ ወቅት ስለ የአመቱ ቀናት መጨነቃቸውና መጠበባቸው እንዲሁ ለከንቱ አልነበረም:: በበረሃው ሀገራቸው የወቅት መፈራረቅ ከዝናብና ከልምላሜ ጋር ወይም ደግሞ ሙቀትና በጋ ከደመናና ከቅዝቃዜ ጋር የተያያዘ ሳይሆን ከአባይ መሙላት ጋር የተዛመደ በመሆኑ እንጂ:: ስለሆነም አባይ ድንገት ሞልቶ በሚፈጥረው ደለል ምርትን ለማምረት ወይም ንብረትን ለማዳን አስቀድሞ ክረምት የሚገባበትን ወቅት ጠንቅቆ ማወቅ ይገባ ስለነበር ነው:: ከዚያም አልፈው የውሃውን ጥልቀት በየጊዜው በመለካት ቀስ በቀስ እየደገ መሄዱንና አለመሄዱን ያጤኑም እንደነበር ዛሬ ላይ በጥናት ታወቋል:: ይህንን ሁሉ ከ2776



ቅ.ል.ክ. በፊት እንዳከናወኑት በአንዳንድ መረጃዎች ላይ ይወሳል::

በግብፃውያን የዘመን አቆጣጠር መስረት 365 1/4 ቀናቶች አመቱ የተከፋፈለ ሲሆን ይህም በፀሀይ ኡደት ከመቁጠር የመጣ መሆኑ በታሪክ ይታወቃል አመቱም በወራቶች የተከፋፈለ ሲሆን ይህም በ12 ወራቶች እያንዳቸው ሰላሳ ቀን ያላቸው እንዲሆኑ ተደርገዋል:: ቀሪዎቹ አምስት ቀኖች እራስቸውን የቻለ ወር የተሰራላቸው ናቸው:: ይህም በዘመኑ ከነበሩት በጨረቃ ኡደት ከተመሰረቱ የዘመን መቁጠሪያዎች በጣሙን እርቆ የቀደመና የመጠቀ ዘመናዊ እና ተግባራዊ የሆነ ዘመን መቁጠርያ የደርገዋል::[1]

ይህ ታዲያ እንደሚያመለክተን ጥንታዊ ሥልጣኔ ከተነሳባቸው ከግብፅ፣ ከሜሶጶጣሚያ፣ ከህንድ፣ ከቻይና እና ከኢትዮጵያ ውጭ ድፈን አውሮፖና ሌሎቹም ገና በየዋሻው እንደ አውሬ በሚንፏቀቁበት የእውቀትንና የትምህርት ብሎም የዘመኑን የጊዜውንም ሁናቴ ለመመርመር በማይቻሉበት የሥልተ ምርት ሁናቴ እና ሥልጣኔ ውስጥ የነበሩ መሆናቸውን እንድንገነዘብ ያደርገናል:: እውነታው ይህ ከሆነ ደግሞ አንድ ስልጡን ህዝብ ለሌላ ስልጡን ህዝብ ሥልጣኔውን እያቀበለ ከሚያወርስው ታሪካዊ ሂደት ውጭ ከየዋሻው እና ከደን ውስጥ መንደሮች ብሎም ከየረግረት እንደ ከርከሮ ከመኖር የመጡት የአውሮፓ ዘላናዊ ጉሳዎች ምንም አይነት



www.ethiopianorthodox.org

የዘመን አቆጣጠር ቀመር ለነዚሁ ሀገሮች የማዉረስ ብቃት የሌላቸው መሆኑንም እንድናጤን ያደርገናል:: ዛሬ ዛሬ ታሪኩን ጠንቅቆ በማያወቀው ወጣትና ብሎም ባለው አንፃራዊ የአለም የምጣኔ ሀብት ብልጫና ልዩነት በመጠቀም አውሮፓውያን ብሎም ሰሜን አሜሪካ በስልጣኔ ጥንትም ገናና እንደነበሩ ለማስመሰል የሚያደርጉት የባህል ወራራ ምነኛ አስቀያሚና አስነዋሪ ድርጊት መሆኑንም እንረዳበታለን:: በይበልጥ ይህ ደግሞ «የአውሮፓ ዘመን መቁጠሪያ አለም አቀፍ ይሁን እና ከኛ ዘመን መቁጠሪያ ውጭ ሌላው ሁሉ ካልጠፋ» በማለት በማን አለብኝነት የሚያዘሩትን ሁከት ለሚያስተውለው ሁሉ ምንኛ ትዝብት ውስጥ ይጥላቸው ይሆን ?

በተያያዥ የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠርን አጀማመር የሚገልፁ ታሪካዊ ትችቶች እንደሚያስረዱት ኢትዮጵያውያን ያላቸው የዘመን አቆጣጠር አጀማመሩ ከሄኖክ መፀሀፍ አንድምታዊ ትንታኔ የተወጣጣ ውርስ ነው የመባሉ ነገር ነው:: በመፀሀፈ ሄኖክ ላይ ቅዱስ ሄኖክ በሰፋት ስለ ከዋክብት እና የአመት ወቅቶች፣ስለሚወጡበት እና ስለሚገቡበት የሰማይ መስኮት፣ ስለ ኡደታቸው ሁሉ አንድ በአንድ ይዘረዝራል:: ይህንንም የሰማይ ሥርአት የሥርአቱም መጋቤ መላእክትንም ስም ወደ ስማይ ተነጥቆ እንደጐበኘና ጥልቅ የሆኑ ሚስጠራትን እንደተረዳ ይገልፅልናል:: እነዚህም በጥቂቱ ከተወሰዱ ጥቅሶች ስናያቸው ይህንን ይመስላሉ::



መፀሀፈ ሄኖክ 21:1-መጨረሻ «ስለ ፀሀይ ኡደት ቁጥር 6 ላይ ፀሀይ የሚወጣባቸውን ስድስት መስኮቶችን አየሁ:: ፀሐይ ከሚገባባቸው በታዎች 6 መስኮቶችንም አየሁ:: ጨረቃም በነዚያ መስኮቶች ይወጣል ይገባል:: ቁጥር 9 ላይ በዚያም መስኮት በግራና በቀኝ ብዙ መስኮቶች አሉ (ሚያዝያ ነው) ቁጥር 17 ላይ በነዚያም ወራት እስከ ሠላሳ ቀን ድረስ ቀኒቱ ከቀን ትረዝማለች ሌሊቱም ከሌሊቱ ታጥራለች በቁጥር 18 ላይ በዚያችም ቀን ቀኒቱ ከለሊቱ ሁለት እጅ ትበልጣለች ጠንቅቀው ቢቆጥሯት ቀኒቱ አሥር ክፍል ትሆናለች ሌሊቱም ስምንት ክፍል ትሆናልች::

ቁጥር 23 ላይ «ፀሀይም ወደ ምሥራቅ ይመለሳል ወደ ስድስተኛይቱም ደጃፍ ይገባል የጳጉሜ ቀን ከሷ ጋር ስለ ኖረች በስድስተኛይቱ ደጃፍ ሠላሳ አንድ ቀን ይወጣል ይገባል በዚያችም ቀን ቀኒቱ ከሌሊቱ ትረዝማለች ቀኒቱም የሌሊቱ እጥፋ ትሆናለች ቀኒቱም አሥራ ሁለት ክፍልን ትሆናለች ሌሊቱም አስራ ስድስት ክፍልን ትሆናልች» (ስኔ) ምእራፍ 22 ቁጥር 1 «የዚህን የፀሀይ ሥርአት ካየሁ በኋላ ስሙ ጨረቃ የሚባል የታናሹን ብርሃን ሌላ ስርአት አየሁ ... ሁለተኛ መሄጃውን ሁለተኛ ትእዛዙንም አየሁለት» ይላል:: ምእራፍ 24 ቁጥር 1 «በፍጥረቶቹ ሁሉ ላይ በኮከቦቸም ሁሉ የተሾሙ የሺህ አለቆች የሚመሯቸው የወር መጋቢዎችን



www.ethiopianorthodox.org

የሚመሩ የ91 መጋቢዎች በዚያ ይወጣሉ::» እያለ ጥልቅ የሆኑትን ሚስጢራትን ይዘረዝራል::

ይህ መፀሀፍና ትምህርቱ እጅግ ጥንታዊ ከመሆኑ የተነሳ የተፃፈው በዚህ ጊዜ ነው ለማለት ያስቸግራል:: በመሆኑም የመጽሀፉ ኢትዮጵያ ውስጥ መገኘትና ስለ የከዋክብት ሂደት እና የወቅቶች የጊዜና የወር ቀመር ስለአለው የቤተ ክርስቲያን ዘመን አቆጣጠር ሥርአትን በማጥናት የመጀመሪያው ጥንታዊና ልዩ ኢትዮጵያዊ ዘመን ማቁጠሪያ ዘዴና ትምህርት እንዲሁም መንደርደሪያ መሆኑ በቤተ-ክርስታያን አበው ዘንድ እና በአፋአዊ ትውፊት ይነገራል::[2]

ከዚህ የምንረዳው ነገር ቢኖር ስለ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ሰው ለማስረዳት ከተነሳ ዘመን አቆጣጠሩን በሁለት ታላላቅ ክፍሎች መክፈል ያስፈልጋል ይህንንም በብሉይ ኪዳን ጊዜ እና በሀዲስ ኪዳን በማለት በሁለት ታላላቅ ክፍሎች መክፈል ያስፈልጋል:: በዚህም የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ምንጩ መፀሀፍ ቅዱሳዊ ነው ለማለት እንችላለን::

ከላይ ያየናቸው ክፍሎች ሥርአት ባለው መልክ ስንተነትናቸው ዘመን አቆጣጠሩ ጥንታዊነት ከመፀሀፈ ሄኖክ ሲነሳ ኪዳነ አደምን ያጠቃልላል ከዚህ ጋር መፀሀፈ ኩፋሌ እንዲሁም ኦሪት ዘፍጥረትን ከእስራኤላውያን ጋር እኩል እየቆጠርን በ5500 ዘመን የመጣበትን ሂደት ማስተዋል ይገባል ከመፅሀፈ ሄኖክ ውጭ ኩፋሌ ላይ ያለውን አዳም



የተቀበለውን ቃል ኪዳን ከአምስት ቀን ተኩል በኋላ አድንሃለሁ የሚለው ቃል ይህም የሚፈታው በ2ኛ ጴጥሮስ ም3 ቁጥር 8 ያለው ጥቅስ ሲሆን በዚህም አንድ ቀን አንድ ሺህ አመት እንደሆነ የሰረዳናል::

የዲያቆን በእምነት ምትኩ መጽሐፍ ይህንን በማብ ራራት እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ ይበል እጅጉንም ይበል የሚያሰኝ ስራ ነው:: ስራውንም ለወደፊቱ በይበልጥ አጠናክሮ ታሪክን ጨምሮ የእዝራ ሱቱኤልንም ቀመር ጠንቅቆ ቢያቀርበው ባሕረ ሐሳቡንም በይበልጥ አስፋፍቶና አጥልቆ ከባዱን ለኛ በሚገባን ቋንቋ እየፈታና የእያንዳንዱን ቃል መሠረታዊ ትርጉም እንደሚያብራራ ተስፋ አደርገለሁ:: ስለ የኢትዮጵያም ዘመን አቆጣጠር በተሰሩ ስራዎች ይህ የበለጠ መረጃ የሚሰጥ ሆኖ አግኝቸዋለሁ:: ለወደፊትም የተሻለ ሆኖ ስለ ኢትዮጵያዊው ዘመን አቆጣጠር አጉልብቶ እንዲፅፈው አስተያየቴን ሳልሰጥ ማለፍ አልፈልግም

በተጨማሪም ዘመን አቆጣጠራችን በኦሪት ዘ ፍጥረት ያለውን የዘመነ አበውን እድሜ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 5 ቁጥር 1-30 ያለውን ደምሮ 5500 የሚያመጣ ዘመን አቆጣጠር እንደሆነ መገንዘብ ያሻል:: ይህንን በጣም ከባድና ሰፊ የሆነ የጥናት ክፍል (የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በዘመነ ብሉይ) ለመዳሰስ ጊዜን የሚወስድ ምርምር በአበውና በነብይያት ሱባኤያት ላይ እነዚህም ሱባኤ አዳም ስንበተ ሄኖክ (መፀሀፈ



www.ethiopianorthodox.org

ሄኖክ ትርጓሜ) ሱበኤ ኤርምያስ ሰንተ ዳንኤል ሀሳበ እዝራ የሚባሉትን የባሕረ ሐሳብ የትምህርት ክፍሎችን በቅጡ ማገናዘብና ማጥናት ያስፈልጋል:: ይህንንም ከጥንታዊውና ከረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ጋር በማስተባበር ታላቅ የሆነ ድርሰትን መፀፍ ያስችላል[3]

ከዚህ ጋር ተያይዞ በዘመነ ሀዲስም የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር እንዲሁ ጥልቅ የሆነ ብዙ ምንጭቸ ያሉት በመሆኑ ሁሉንም መርምሮም ወጥ የሆነ ሥራን ማበርከት ለዚህ ትውልድ የተሰጠ ሃላፊነት ይመስላል:: እነዚህም እንደ ወቅያኖስ የሰፋ (በእውነትም ባሕረ ሐሳብ) የዘመን አቆጣጠራችንን ሊያስገነዝቡ የሚችሉትን ምንጮች በስርአት ብዙ ዘመን የሚያጠና ሰው በአሁኑ ሰአት በጣም አስፈላጊ ነው:: ምንጭቹም አቡሻከር ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቅዱስ ኤጳፋንዬስ ዘ ቆጵሮስ ቅዱስ ቄርሎስ ዘ እስክንድርያ ሳዊሮስ ዘ ዕስሙናይ ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ እና ሌሎችም ታላላቅ ሥራዎችን መመልከት ግድ ነው::

ይህ ስራ በጥልቀት የሚያውጠነጥነው በወሳኝ መረጃዎችና በይበልጥ ደግሞ በዘመነ ሀዲስ ያለውን የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ላይ ሲሆን አላማው ደግሞ ዘመን አቆጣጠራችን ከትክክለኛውና እውነተኛው የጌታ ልደት ዘመን የሚነሳ መሆኑን የማረጋገጥ ይዘት ብቻ አለው ::



የግብፅ ዘመን አቆጣጠር ጥንታዊና ሰፊ ታሪክ በማሳለፍ ለአወሮፓውያኑ የባህላዊና የጨረቃ ኡደት ላይ የተመሰረተውን በአፈ ታሪክም ላይ የሚያውጠነጥነውን በዋናነት የሮሜ ዘመን አቆጣጠርን እንዲሻሻልና ወደ ሥልጣኔ መዳረሻ እንዲደርስ ያበረከተው ተፀእኖ ወደፊት የምናየው ይሆናል:: ስለዚህም የቅብጥ (ግብጽ) ዘመን መቁጠሪያ ከክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ ጋር ያለውን ትሥሥር መመልከት ከተነሳንበት አርእስት ጋር ታዛማጅ የደርገዋል::[4] ግብጽ የክርስቶስ የስደት ሀገር ናት /ማቴ 2:1/ ሀዋርያት እና አርድእት ወደ ግብጽ ወርደው ሠብከውባታል:: ቅዱስ ማርቆስም መንበሩን በእስክንድርያ በማድረግ አስከሞት ድረስ ወንጌልን እየሰበከ ለክርስትና እና ለቤተ ክርስቲያን በግብጽ መተከል ተጋድሎአል::

እስከ ዛሬ ድረስ የተገኙት የቅብጥ ክርስቲያኖች አባቶቻችን ከሐዋርያት እንዲሁም ከወንጌል መሰረትነት የተማሩትን ትምህርት ይዘው የዘመናትን የምንፋቅና ጉርፍ የአህዛብ የግድያ ፈታና መአበል ተሰቅቀው ሳይክዱና ሳይጠፉ አምላካቸውን የሙጥኝ እንደያዙ ሰለመዝለቃቸው መረዳት አያዳግትም:: ክርስትና «ሀ» ብሎ በእስክንድርያ ከተሰበከበት ጊዜ አንስቶ ሰማእትነት በአህዛብ እና በሮሜ ቄሳሮች ምክንያት የግብጽ ክርስቲያኖች እፃ ሆና ነበር:: በዚህም ሁናቴ በ13 ተኛ ው መቶ ክፍለ ዘመን መንፈስ ቅዱስ ሚስጠራቱን የገለጸለት



www.ethiopianorthodox.org

አቡሻከር ባሰፋፋው በሐረ ሐሳብ እንደሚገልጸው የዘመን አቆጣጠር ሥርአትን መጀመሪያ ሙሴ በመንፈስ እግዚአብሔር ተመርቶ ሥርአትን እንደሰራ ሌዋውያኑም ያንኑ ቀመር እየተከተሉ የአይሁድ ባእላትን ሲያስሉና ሲያስተምሩ አመቱንም ከፍጥረተ አለም ጀምሮ ሲቆጥሩ ኖረዋል።

በጌታችን በመድሐኒታችን መወለድ ዘመነ ፍዳ በማለፉና አዲስ ኪዳን በመመስረቱ የአዲሱ ጊዜ ብሥራትና የምሥራቹን ቃል ከዘመኑ ጋር እየቆጠሩ ሐዋርያት ደግሞ ለክርስቲያኖች አስረክበዋል። ከዚህ በኋላ በ(188-230ዓ.ም) በእስክንድሪያ ላይ በመንፈስ ቅዱስ የተሾመው ቅዱስ ድሜጥሮስ መንፈስ ቅዱስ ሀይሉን በህይወቱ ገልፆ አእምሮውን አብርቶ ልቦናውን እና እጆቹን አበረትቶ ብዙ ሚስጢር እንደገለፅ ፣የዘመን አቆጣጠር ቀመርን እንዲሰራ፣ የበአላትን አከባበርን ከአይሁድ ባእላት ጋር እያነፃፀረ በሙሴ ከተቀመጠው ቀመር ጋር ህብረቱንና የሚለየውን የክርስተያን ቀመር አግኝቶአል። እንዲህ ማድረግ ብቻ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ ፃፍ ያለው ዘመን ድረስ ባለው አመታት ውስጥ ባእላቱን እና ዘመናቱን ሁሉ ገልፆ ፀፎታል።

ይህንን ላስተዋለው ሰው መላው አውሮፖና ፣አለም ሁሉ ገና የወንጌል ጠላት በነበሩበት 2ኛውና 3ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ቅዱስ ዲሜጥሮስ ስለ ጌታ ልደት፣ ስለ ዘመን አቆጣጠር፣ ስለ አመተ አለምና፣ ስለ አመተ ፍዳ ወይም ኦሪት



እና አመተ ምህረት እያነፃፀረ መፃፉ የጌታን ልደት ለመረዳት እና በቅጡ ትክክለኛውን አመት ለማወቅ ምን ያህል የቀረበ እንደሆነ አያሳይም ወይ? በማለት ምእራባውያኑን ከባድ ጥያቄ እንድንጠይቅ ያደርገናል።

አባታችን አቡሻከርም የአባታችንን የድሜጥሮስን መንፈሳዊ ፀጋ ከታሪክና ከቀመሩ ጋር አስፍቶ በ13ኛው ክፍለ ዘመን የባሕረ ሐሳብ መጽሀፍትን ጽፎልን እንዳለፈ እንረዳለን። ከዚህ ጋር የሚዛመድ ታሪካዊ ሂደት ላይ እንደምንመለከተው በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ጳጳሳትን ለኢትዮጵያ በመጀመሪያ ጊዜ የቀቡትና የሾሙት የእስክንድርያ ፓትሪያርክ ቅዱስ አትናቴዎስ ለአባ ሰለማ ይህንኑ የሀይማኖት ሥርአትና ቀኖና እንዲያስተምሩና ህዝቡ እንዲጠብቀው መንፈሳዊ ትሕዛዝና ትምህርት በመስጠታቸው ከሀዋርያት እና ከግብጽ በቀጥታ እንዲሁም ከሀዋርያነ አበው የተረከብነው የቅብጥ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያናዊውን ዘመን አቆጣጠር ስለ መሆኑ አያጠራጥርም። አባ ሰለማ የጳጳስነትን ፣ ማእረገ ክህነትን ፣ስለ ክህናት አሻሻም፣ ስለ ዶግማ እና ቀኖና ሥርአት እና ሚስጢር ሲያጠኑ በግብፅ ውስጥ ለብዙ አመታት ተቀምጠዋል።[5]

እዚህ ላይ ግን ግብፆቹ እንደእኛ በአመተ ምህረት፣ እና በልደተ ክርስቶስ ወይም እንደ አውሮፓውያኑ በአመተ እግዚእ አይቆጥሩም። ይልቁንም እነርሱ በአመተ ስማእታት




www.ethiopianorthodox.org

ይቆጥራሉ:: እኛ ደግሞ በአመተ ምህረት እንቆጥራለንና ዘመናቸውም ከዘመናች ለየቅል ነው:: በኛ በኢትዮጵያውያኑ ዛሬ 2000 ዓ.ም ሲሆን በነርሱ ገና 1724 አ.ሰ. ነው ቢሉ ነገሩ እንዲህ ይፈታል::

በፊት እንዳየነው በግብጽ ክርስትና ገና ከመስበክዋ ሰይጣን እና ልጆቹ ተነስተው ለማጥፋት ተረባረቡ:: ይህ የፈተና ማእበል እንዳች ሳይላላ ቀጥሎ በ277 ዓ.ም ገደማ አሰቃቂ የሚሆን የዲያብሎስ የፈተና ዘመን ተጋረጠ ይህ ወቅት በሮሜ ግዛት ላይ ከተራ ወታደርነት ለቄሳርነት ደርሶ አንባገነን የሆነ ዲዮቅልጢያኖስ የሚባል ሰው የነገሰበት በመሆኑ በአስከፊነቱ የሚታወቅ ነው:: በይበልጥ ግን ዘመኑ «ዘመነ ሰማእታት» በመባል ተወዳዳሪ የሌለው የመከራ፣ የእንግልት እና የሰቆቃ እንዲሁም የሲቃ ዘመን የመሆኑን ነገር በሚገልፀው ሀረግ ይታወቃል:: ይህ ሰው ክርስታያኖችን ከምድረ ገጽ ሊያጠፋ ወዶ ይህ ነው የማይበል እልቂትን ከፈተ፣ በዚህም መከራ በአለም ላይ ካሉት ክርስቲኖች ሁሉ ግብጾቸ በይበልጥ፣ ተጨነቁ፣ ተጨፈጨፉ፣ አለቁ:: የከፈሉትም ስመአትነት ሊዘከር ሊዘረዝር አይቸልም:: በትንሹ ግምት ከስምንት መቶ ሺህ ሰው በላይ ሰማእትነትን ተቀብሎበታል:: [6]






ስእል 1 እንደ ስንክሳሩ ሰይጣን እራሱ ልጄ ሲል የጠራው የዲዮቅልጥያኖስ

ታላቁ ቅዱስ እንጦንስም ከበረሃው በአት ወጥቶ ብዙዎችን አበረታ ብዙ መከራም ተቀበለ:: የዲዮቅሊጢያኖስ ሹማምንቱ ሊገድሉት ሞክረው ነበር:: መንፈስ ቅዱስ ግን በዚህ ይሞት ዘንድ አልፈቀደምና ሊሞትላቸው አልተቻላቸውም እግዚአብሔርም መሳህቲውን እና አላዊውን ገኘ ያሳፈረው ዘንድ ስአቱ በደረሰ ጊዜ አባታችን ቅዱስ ጊዮርጊስን አስነስቶ ሊነገር በማይቻል የመከራና የሰቆቃ ኑሮ



www.ethiopianorthodox.org

ኖሮ የዘመነ ሰማእታትን እሳት በተጋድሎው በፈሰሰው የደም ብዛት አጠፋው፡፡




*ስእል2 የሊቀ ሰማእታት ፋጡነ ረዲኤት ብፅእ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሥእል*

የግብጽ ክርስቲያኖችም ዘመነ ሰማእታት አልፎ ቆስጠንጢኖስ ነግሶ አለም ሰላም የሚሆነው ክርስቲያኖች



ከግበበ ምድር የሚወጡበትን ጊዜ ባዮ ሰአት ተጋድሎአቸው ሊከበርላቸው እና ሊዘከርላቸው ለሚገባቸው ለሰማእታቱ ክብር ሲሉ «አንድ አመት ዘመነ ሰማእታት ካለፈ» በማለት አዲስ የዘመን አቆጣጠርን ህግ ሠሩ፡፡ ይህም ጥፋት የለውም የቅዱሳኑን የሰማእታቱን ተጋድሎ ለመዘከር የፀሎታቸው እና የአማላጅነታቸውን በረከት ለመቀበል ብለው ነውና ያደረጉት፡፡



ሕዝብ ፣ በተሰበሰበበት ፣ አደባባይ ፣ ክርስቲያኖቹ ፣ ተሰብስበው ፣ ወደተቀመ
ጡበት ፣ አራዊቱን ፣ ሲለቁባቸው ፣ አንበሳው ፣ ወደነሱ ፣ ሲራመድ ፣ ሴላው ፣
ነብር ፣ ነና ፣ ክምድጓዱ ፣ ብቅ ፣ ሲል ፣ ይታያል ።

*ስእል 3 እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ የክርስቲያኖች ኑሮ በሮሜ መንግስት ይህን ይመስል ነበር፡፡*

ስለዚህ ዛሬ በኛ 2000 ዓ.ም ላይ የግብፀ /ቅብጥ/ 1724 ዓ.ስ. ከሆነ በፊት ያለውን የጋራ አመት ወይም እኩል የቀጠርናቸው



www.ethiopianorthodox.org

276 ዓመቶች ስንጨምርበት 2000 ዓመት ምህረትን ይሰጣናል:: በዚህም የኢትዮጵያና የግብፀ የዘመን መቁጠሪያ አንድ ነው ምንጩም ቅብጦቸ አባቶች ሊቀ ጳጳሳቱ በሀዲስ ኪዳን ያወረሱን እነርሱም ከሀዋሪያት የተቀበሉት ያመነጩውም እግዚያብሔር ነው የሚባለው::

ማስረጃ: ዛሬ በግብጽ 1724 አ.ሰ. ነው በእኛ ዛሬ 2000 ዓ.ም ነው:: በ1724 አመተ ሰማእታት ላይ የጋራ የሆነውን ቅድመ አ.ስ. 276 ዓ.ም ሲደመር 2000 ዓ.ም ይሰጣል:: ወይም ከ2000 ዓ.ም ላይ 276 ዓመት ሲቀነስ 1724 አ.ሰ. ይሰጣል::

አንዱና ሌላው ማስረጃ መፀሀፈ ስንክሳር ነው በመጽሀፈ ስንክሳር ላይ መስከረም አንድን ገና ከመግቢያው «ይህ ወር የተባረከ ነው እርሱም የግብፅና የኢትዮጵያ የአመቶች መጀመሪያ ነው» ይላል:: መስከረም በጥንቱ እና በአሁኑ ቱት /ቶት/ በግብፀ ልማድ ወይም ርእስ አወደ አመትም በመባል ይታወቃል:: በአውሮፓውያኑ ይህ ቀን በሴፕቴምበር 11/12 የሚውለው ቀን ነው::

ከዚህ ባሻገር የኛ ዘመን መቁጠሪያ 365 ከ1/4 ቀን ያለው እያንዳንዱ ወር በ30 ቀን የተከፋፈለ 13 ወሮቸን የያዘና የመጨረሻዋም 5 ወይም 6 ቀን ያላት 13ኛዋም ወር ጳጉሜን በፀርእ / ግሪክ/ ሸራፊ በሚባል ስም ወር ያለው ነው:: ጳጉሜን የሚል የፀርእ ቃል መግባቱ ከእስክንድር



«ታላቁ» ጀምሮ እስከ ተሎሜ ሥርው መንግስት ማብቃያ ድረስ ግብፅ በጽርእዎች ለመገዛትዋ እና ከዚህ በፊት የተሰየመውን የጥንቱን ቃል የተበረዘበት ሂደት በግብጽ ስለ ነበር ነው:: ይህው በራሱ ከነርሱ እንደወረስነው የሚያመለክት መረጃ ነው:: [7]

ሌላው የኢትዮጵያ ባህረ ሀሳብ የፀሀይ አውድ ነው:: ይህ ማለት የፀሀይ ኡደትን የሚከተል ነው ማለት ነው:: ይሄ ደግሞ በጥንታዊው የግብጽ የዘመን አቆጣጠር ወደ ኋላ ደግሞ የቅዱስ ዲሜጥሮስን የባህረ ሐሳብ ቀመርን የሚያመለክት ውርስ መሆኑን ይገልፃል:: በተቃራኒው ሳባውያን በጨረቃ እያመለኩ በሚኖሩበት በጥንት ጊዜ ጨረቃዋን ስን (sin) ወይም አልሙቃህ (Almuqah) በማለት አማልክት ናት ብለው ይጠሩ ነበር:: ወራቶችንም በጨረቃ ልደት አመቱን የጨረቃ ኡደት አድርገው ዘመኑን ይቆጥሩ ነበር:: (Lunar month and year) ይህ ባህል እና ዘመን መቆጠሪያ ጨረቃን የበድዊኖች (Bedawin) የደቡብ አሬቢያ እና የሳባ ተወላጆች ሁሉ የዘመን መቁጠሪያ እንደሆነ መረደት አያዳግትም:: [8]

በሰሜን ኢትዮጵያ ላይ ባሉ በተለያዩ ቦታዎች ላይ በተደረገ የከርሰምድር ቁፋሮ ጥናት ሳባውያኑ በዚህ ልማድ እንደኖሩ የሚያረጋግጥበት ክፍል አለው:: በየሐ ቀበሌም የጨረቃ ቤተ መቅደስም ዛሬ ድረስ እንደ ቆመ ይህንኑ ታሪክ



www.ethiopianorthodox.org

ይዘክራል:: ነገስታቱም እስከ አፄ አብርሃ ድረስ «አለመለቀሃ» እያሉ ጨረቃውን ማምለካቸውን የሚገልፁ የድንጋይ ላይ ፅሁፎች (Inscriptions) በብዛት ይገኛሉ:: [9]

ይህ ታሪካዊ መረጃ ተቻኩለው የዩት እንደሆነና በጥቅሉ ከወሰዱት ወደ የተሳሳተ ድምዳሜ (Hasty generalization) እንድንደርስ ያደርገናል:: ስለሆነም ኢትዮጵያዊው ጥንታዊ ዘመን አቆጣጠር የሚጀምረው በጨረቃ ኡደት ነው ወደ ሚለው ሀሳብ ሊያመራ ይችላል:: ነገሩን በጥሞና ስናስተውለው ግን በጥንታዊው የኢትዮጵያ ሥልጠኔ ውስጥ ሶስት ዋና ዋና ታላላቅ የሃይማኖት፣ ማህበረሰባዊ፣ የፖለቲካ ቡድኖች እንደነበሩ የምንገነዘብበት መድረክ ይፈጥርልናል:: እነዚህም ሳባውያን ፣ ኦሪታዊያን እንዲሁም ባህላዊ ሀይማኖት (traditional warship) ተከታዮች የሆኑ አማውያን ወይም /ነባር ህዝብ/ መሆናቸውን እንረዳለን:: [10]



## የምእራፍ ሶስት
## መገናዘቢያ ጥቅሶች

1. ____ .**World History** (vol. I) USA Armed forces institute ( Wisconsin , N.D) p.48 ; See In debth this source; James Brestade (PHD) **Ancient times:A history of the Early world** ( Boston,1916) pp.45,467

2. ይህ መፅሀፍ አዳም ሰባተኛ ትውልድ በሚሆነው በሄኖክ የተፃፈ ነው:: በመፅሀፍ ቅዱስ ገፀ ንባብ በኦሪት ዘፍጥረት ላይ5:1-32 በተጠቀሰው በሄኖክ ይህ መፅሐፍ ተፅፎአል ከሙሴ መነሳት በፊት ሲዘከር የሚከብድ የአለም ሁናቴን የሳለፈው ይህ መጽሐፍ (የጥፋት ውሃ) እና የዘመኑ እርቀት ተያይዞ ስለ ዘመን አቆጣጠር መነሻ ጥንታዊና ብቸኛ እንዲሁም ልዩ መረጃ ያደርገዋል:: ስለ መፅሐፉ ከሙሴና ከኖህ የቀደመ ሆኖ መገኘት ጥያቄ ቢነሳ አበው «ለሙሴ ስለ አዳም የገለጠ መንፈስ ቅዱስ የሄኖክንም መፀሐፍ ለሙሴ ገልጦለት ጽፎታል » ሲሉ ያስረዳሉ:: የኖህ ልጅ የነበረው ቃይናም ከጥፋት ውሃ ከወጡ በኋላ የቀደሙት ሰዎች የፃፉትን ጽህፈት አገኛት አነባበትም ሸሸጋትም እያለ የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል የጽሁፍ ስራ ሊተርፍ የሚችልበትን ሌላ ማመልከቻ ይሰጠናል:: (ኩፋሌ 8:35-36) ይህ መፅሀፍ (ሄኖክ) ስለ



www.ethiopianorthodox.org

ዘመን አቆጣጠር የሚገልፅ ቢሆንም ቅሉ እንድምታዉን ተንትነው የሚያስረዱ የጠሩ ሊቃውንት አበው ካልሆኑ በስተቀር ማንም ተራ ሰው አይቻለውም በመሆኑም አበው በተሰጣቸው ፀጋ አንድ ብለው ስለ መጽሀፉ በጥልቅ እንዲያስረዱ ከማለት ውጭ ፀሀፊው ባለው ውስንና ኢምንት እውቀት አንዳች ማለት እንደማይቻል ማሳሰብ ይፈልጋል::

3.ማሕበረ ቅዱሳን ዝክረ ዘመን መጪው ዘመን እንደይቀድመን እንነሳ /ሜጋ አሳታሚ 2000 ዓ.ም/ ገፀ 20-27 ዲያቆን በእምነት ምትኩ የኢትዮጵያ ታላቁ ሀብት ባህረ ሀሳበ የዘመን አቆጣጠር /ባህርዳር ዩኒቨርስቲ ዋናው ግቢ 1999/ ገፅ 1-22 90-115

4. ክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ መነሻው የጌታችን የመድሐኒታችን ልደት ሲሆን ከዚህ ሌላ የጌታን እድሜ በወንጌል ውስጥ እንደ ተጠቀሰው አድርጎ ማነፃፀር የሚችል መሆን አለበት:: የዚህ ዘመን መቁጠሪያን ምዕራባውያኑ የማይጠቀሙት መሆኑ ተረጋግጦአል:: በሚቀጥለው ምእራፍ በስፋት የሚታተት ክፍል ስለሆነ ምእራፍ አምስትን ተመልከት

5. Sergew Habile Sellassie, pp.99, 101,102 See that Constantius wrote to Ezana and Saizana Pleading that frumentius learn ecleastical matters once again from the Arian pope George

6. አስራት ገብረ ማርያም እና ገብረ ሕይወት መሐሪ የዘመን አቆጣጠር /አዲስ አበባ ፣1984/ ገፅ 20-40

7. የጥንታዊ ኢትዮጵያ ታሪክ ብቸኛ ተመራማሪ ፕሮፌሰር ስርገው በጥንታዊ ኢትዮጵያ ታሪክ መፅሀፋቸው ገፅ 200 እና 201 ላይ የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የግብጽ (ቅብጥ) ቤተ ክርስቲያን ስለ መሆኑ በአፅንኦት ይደመድማሉ:: በይበልጥ ግን ጥንታዊው የግብፅ የጳጉሜ ወር ስግር (sager) እንደሚባል አሳይተዋል:: በኛ በህረ ሀሳብ ላይ ይህን ቃልን የሚጠቀም በመሆኑ በይበልጥ ዋና መረጃችን ያደርገዋል:: ይልቁንም የበጥሊሞስ (ቶለሜ) የፅርእ ንጉሶች ግብፅ ላይ በስልጣን ኑረው የራሳቸውን ቋንቋ እየጨመሩ የመበረዛቸው ስራ በጳጉሜና በተለያዩ በግብፅ ቃላቶች ላይ ትራፊው ዛሬ ድረስ እንዲታይ ምክንያት ሆነዋል ስለሆነም የዚህን ቃል መረጃነት ልብ ማለት አስፈላጊ ነው::

7. Philip K.Hitti, **History of the Arabs: From the earliest times to the present** ( London, 1970) P.87

8. Sergew Habile Sellassie pp.60,117,118

9.ተክለ ፃድቅ መኩሪያ ገፀ 91፣206 ላይ ያለወን በጥንቃቂ በማንበብ ስለ ሀሳቡ ምንነት መረዳት ያስችላል በዚሁ መፀሀፉ / የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም እስከ ዛጉዬ/ ላይ




www.ethiopianorthodox.org

ባለው ሶስት ተነፃፃሪ የነገስታት ስም ዝርዝር ላይ ከጌታ ልደት በፊት በኢትዮጵያ የነገሱ ነገስታት ቶማጽዬን ፡ ጽዬን ግዛ እየተባሉ የሚጠሩ እንደነበሩና እነዚህም እንደ እስራኤላውያን ነገስታት እንዳንዶቹ በኦሪት ሲፀኑ በሌላ ጊዜ በዚያው ባለው አምልኮ ሌሎቹ ሲወድቁ የኖሩ ነገስታት እንደሆኑ እንረዳለን:: በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያ ኦሪት የገነነችበት በኋላም የምትዳፈንበት እንደገና የምትነሳበትን ሂደት ከነገስታቱ እስከ ህዝቡ ድረስ ያለውን ትስስር ይጠቁመናል::



## ምእራፍ አራት

## ኢትዮጵያ እና ጌታችን በዘመነ ሥጋዌ

ከምድረ እስራኤል እና ከግብጽ ውጭ በአዋልዳት ውስጥ የጌታችን ስደትን አስመልክቶ በስፋት ተጠቃሽ የሆነች ሀገር ኢትዮጵያ ናት ይህንንም በሙላት እና በስፋት የሚያትተው ድርሳነ ኡራኤል ነው::

እንደ አንድምታው አገላለጽ «ወይወርድ እግዚእነ ውስተ ምድረ ግብጽ ተፅዒኖ ዲበ ደመና ቀሊል ወፋኖቶሁ ዘእም ዓለም ርኢኩ አእጓዳተ ኢትዬጵያ ይደንግፃ» (የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ) ያለውን መሠረት አይርጐ «ወገሩ እግዚነ ኢየሱስ ውስተ አድባር ሊባኖስ ወውስተ ምድረ ግብፀ ወብሔረ እግዚእ ምስለ ማርያም እሙ » ይላል ጌታ ከእናቱ ጋር ወደ ደጋማ ተራራ ወደ ግብጽና ወደ ኢትዮጵያ መልእኩ ለዮሴፍ እንደነገረው ስያመነታ ተሰደደ ይህም ኢሳያስ ወደ ግብፅ መውረዱን ሲያመለክት ዕንባቆም ደግሞ በዚያው አያይዞ ወደ አትዬጵያ መግባቱን ገልፃል (ትን. ኢሳ 19:1) (እንባቆም 3:6-7) ይላል::

የዋልድባ ገደም ታሪክም ስለ ጌታ ወደ ኢትዮጵያ መግባት ገዳሙንም የመባረኩን ታሪክ ይገልፅልናል በ1983 ዓ.ም የተተመው የገዳሙን ታሪክ የያዘው መጽሀፍ ስለዚሁ ሲገልጽ እንዲህ ይላል «....[እመቤታችን ከጌታችን ጋር በደመና ሆነው ኢትዮጵያን ሲጐበኙዋት]... ደብረ ዳሞን ተመለከትን



www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ በኋላ አክሱም ደረስን ከአክሱም ተነስተን ደብረ አባይ ደረስን:: ዳግመኛም ከዚህች ቦታ ተነስተን በደመናው ላይ እንደሆን ተከዜን ወንዝ ተሻግረን ዋሊ ከሚባለው ገደም ወይም በርሃ ደረስንና ከዚያ በሚገኘው በርሃ ዋሻ ውስጥ ገባን በዚያችም በረሀ ታላቅ ዋሻ በማግኘታችን እህል እንበላና ውሃም እንጠጣ ዘንድ በውስጧ አረፍን ነገር ግን ምንም የሚበላ አላገኘ ንም ዋሻው የአለው በበርሃ ውስጥ ነበርና ያን ጊዜ ልጄ የብረት አንካሴ ያላት የዬሴፍን በትር ወስዶ የአንዱን እንጨት ሥር ቆፈረ ከእንጨቱም ውስጥ የወጡት ሥሮች 318 ነበሩ:: የአንዱን ሥር አምጥቶ እናቴ ይህን የእንጨት ሥር አንች ብይው አለኝ ያን ጊዜ ልጄ ሆይ ከሰንዴ በቀር ሌላ እንጨት መብላትን አለመድሁም እና ይመረኛል ብዬ መለስሁለት ይህ ይመረኛል የምትይው የእንጨት ሥር ከማር እና ከስኳር ይበልጥ እየጣፈጣቸው የሚመገቡት ቅዱሳን መነኰሳት አሉ (ቁርፋ ነው) አለኝ...ዳግመኛም ልጄ ከኛ ጋር ከግብፀ አገር የመጡትን እነዚህን ሦስቱን አንበሶች በዚህች ገዳም ካሉት አንበሶች ጋር ተደባለቁ አላቸው ምድርን በላይዋ ላይ ሣር በቅሎ እንዳለበሳት እናንተም ብዙ ተባዙና ምድርን ሙሏት አላቸው ልጆቻችሁ እናቴን ለሚወዱ ለቅዱሳን ሁሉ ለሥጋቸው ድካም ማረፊያ እስከ ዓለም መጨረሻ እንደ ፈረስና በቅሎ ለመጓጓዣ ያገልግሏቸው በዚህች ገዳም ውስጥ ያለጥፋት የተባረኩ ሆነው ይኑሩ ብሎ ባረካቸው» ይላል::



በዚህም ታሪክ ላይ የአባ ሳሙኤል አናብስት ለእርሳቸው እንደ በቅሎ ያገለግሏቸው እንደነበረ ከድርሳናቸው ላይ እንረዳለን::

በድርሳነ ኡራኤል ላይ በተጨማሪ ስለ ጌታችን በስደቱ ዘመን ከእመቤታችን ጋር በኢትዮጵያ ምድር እና በግብጽ የተሰደደበትን እና የባረካቸውን ቦታዎች ሁሉ ይዘረዝራል በደቡብ ጎንደርም እመቤታችን በስደትዋ ወቅት ካረፈችባቸው ቦታዎች አንዷ የሆነችው እና ከግብጽ መምጣትዋን የምታጠይቅ ግብጣይት ወይም ግብፃዊት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ትገኛለች::

ድርሳነ ኡራኤል ዘህደር ቁጥር 22 ላይ እመቤታችን ከዮሴፋ አረጋዊ እና ከስሎሜ ጋር በብርሀት ደመና ላይ ሆና ኢትዮጵያን እንደጐበኘች የአስራት ሀገርዋ ሆና እንድትወስደው አምላካችን ልጅዋ እንደሰጣት ይናገራል::

በቀጥርም 38 ላይ እመቤታችን ከጌታችን ጋር ወደ አክሱም እንደደረሱ በዚያም የኢትዮጵያ ንጉስ ባዜን ታቦተ ፅዮንን ለመሳለም ምምጣቱን በሚያስደንቅ ቋንቋ ያስረዳናል::

በድርሳነ ዑራኤል ላይ እንደተገፈውም እመቤታችን ከኖረችባቸው ቦታዎች ውስጥ ዋና የሆኑት የጣና ደሴቶች ናቸው:: በድርሳኑ ታህሳስ 22 የሚነበበው ክፍል ላይ ስለ እመቤታችን በደሴቲቱ ከጌታጋር ስለ መኖርዋ ይገልፃል:: በቁጥር 22 ላይ እመቤታችን በደሴቲቱ ውስጥ ሥስት ወር



www.ethiopianorthodox.org

ከ10 ቀን ያህል ተቀምጣለች የሄሮድስንም መሞት እመቤታችን በጥር 18 መላእኩ ኡራኤል እንደነገራት ተጽፎአል::

ዛሬ በየረር ተራሮች ላይ እና በዚያ ባለችው በባእታ ቤተ ክርስታያን እንደሚነገረው እመቤታችን በሰደቷ ወራት አምላክ ልጆዋን ይዛ በብሩህ ደመና ላይ እንዳለች ኢትዮጵያን ስትባርክ በተቀደሰው እግሮቸዋ በየረር ተራራዎች ላይ ባሉት አለቶች ላይ እንዲቆመችባቸው አባቶች ያስረዳሉ::

በዚህም የጌታችን ልደት ዘመንን ለመረዳት እንዲሁም ለማወቅ ግብፁና ኢትዮጵያ ለወንጌሉ ምን ያህል የቀረቡ እንደሆኑ እንረዳለን:: በላይ ባየነው ክፍልም በየቦታው የአምላክ መገለፅን ህዝቡ በትውፊቱ እያስታወሰ እንደሚያወርሰው እና በትውልድ ውስጥ እየቀጠለ መገኘቱንም እናይበታለን::

በተጨማሪም ስለ መፀሀፉ አመጣጥና አፃፃፍ የሚተርክ ክፍል ያለው ሲሆን ፀሐፊው ቅዱስ ዮሀንስ አምጭው ቅዱስ አባ ህርያቆስ እንደሆኑ እንዲህ እያለ ይገልጸዋል:: «ይህ መፀሁፍ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው አምላክን የወለደች የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ቅደሴዋን የደረሰላት በቁስጥንጥንያ ውስጥ በምትገኘው የብህንሳው ኤጲስ ቆጶስ አባ ሕርያቆስ ነው:: ያመጣውም የአክሱም ገበዝ የሚሆን እንበረም ሊቀ ከህናት በነበረበት ጊዜ ሁለቱ የኢትዮጵያ ነገስታት አብርሃና አጽብሐ ከነገሱበት ዘመን በኃላ ነው በጣዕመ ዜማው አንደበቱ የማረ ካህኑ የሬድና አለምን የናቀ የሮሙ ንጉሥ



ጻድቁ አባ አረጋዊ ከንጉሱም ከገብረ መስቀል ጋር ሳሉ ይህንን መጽሐፍ በክብር ተቀበሉ» በማለት በጥቅምት የሚነበበው የድርሳኑ ቁጥር 54-59 ላይ ተፅፎአል:: (ድርሰነ ዑራኤል በግእዝና በአማርኛ አዲስ አበባ ግንቦት 1991 ትንሳኤ ዘጉባኤ)



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ አምስት

## የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያ ዩልዮሳዊ ነውን?

በአሁኑ ሰአት ሥጋዊው አለም በድምዳሜ የያዘውነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ዮልዮሳዊ ነው! የሚል ከንቱ ሀሳቡ ነው። ከሁሉ አስቀድሞ ግን ዩልዮስ ቄሳር ስለመሠረተው ዘመን መቁጠሪያ፣ ስለ የግብፅ ዘመን አቆጣጠር ልማድና የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያ ስለ አላቸው ባህሪያት በደንቡ መረዳትና ማወቅ ማናቸውንም መላምት ከመዘላበድና የራስን ድብቅ የባህል ወራራ በግልጽ ባዶ በሆነ ተረት ውስጥ አሾልኮ ለማስገባት ሲሞክሩ ከመታየት ያድን ነበር። ስለነዚህ ዘመን መቁጠሪያዎች ታሪካዊ አመጠጥና ሂደት ጠንቅቆ ማወቁ ያላቸውንም ትስስር ብሎም ልዩነት እንዲሁም የሚያገናኛቸውን መሰመር ለመመርመርና ለመረዳት ያስቻላል።

ስለዚህም ይህ አይነቱ ሂደት በጣሙን የላቀና ተቀዳሚ ተግባር ነው። አንዳንዶች የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያ ዮልዮሳዊ ነው ብለው መፃፍቸውን ተከትሎ ሌሎችም (BBC, brodcasting live on Ethiopian millennium clebrations) በቀጥታ ሥርጭት ሳይቀር ይህንኑ መናገራቸውን አጢኖ ይህንን አባባልና ትምህርት ምንነት በቅጡ በማየት ውሳኝ ምላሾችን እንድንሰጥ ያስገድደናል።




ዩልዮስ ቄሳር በ58 ቅ.ል.ክ በሮሜ ከጀነራልነት ተነስቶ አምባገነን ለመሆን የበቃና የቄሳርነትን ማእረግ በሰሙ ያቋቋመ የሮሜ ወታደር ነው። ይህ ሰው በብዙ ድሎቹና በብዙ ዘመቻዎቹ የተፈራና የታወቀ በኃላም ለስልጣን መንደርደሪያው የጠቀመው ሰው ነበር። ዩልዮስ በዛ ጓደኞቹ በጩቤ ተወግቶ በ14 «ማርች» ከመሞቱ በፊት አንድ ወሳኝ ስራ ሰርቶአል። ይኸውም በሮማውያን ዘንድ የነበረውን ኋላቀር ዘመን አቆጣጠር ወደ ዘመናዊና ተቀባይነት ያለው ወይም ሊያገኝ ወደሚችል ደረጃ ማምጣት ነበር። ከዩልዮስ ቄሳር በፊት እንደሚታወቀው የሮማውያን አቆጣጠር በጨረቃ ኡደት ላይ የተመሰረተ የጨረቃ ወሮች ያሉት እና መነሾው ከአፈ ታሪካዊው የሮሜ ከተማ ግንባታ ጋር የተያያዘ ነበር። እንደ ሮማውያኑ ባህላዊ የዘመን አቆጣጠር ልማድ በሮሙለስ (Romulos) ንግስናና የሮሜ ግንቦታ ለዘመን መቁጠሪያቸው መነሻ እንደሆነ ይናገሩ ነበር።

ሮሙለስ ሬሙስ (Remus) ከሚባለው መንትያው ጋር የነገሳታት ልጆች ነበሩ ይባላል እኒህ ልጆች በተወለዱ ጊዜ በሥልጣን የነበረው አጐታቸው ሲያድጉ መንግስቱን የሚቀሙ ይሆናሉ የሚለውን ንግርት ሰምቶ በጭካኔ ይገደሉ ዘንድ አዝዞ ነበር። ግደል የተባለው አሽከር ግን ልቡ ስለራራላቸው በቅርጭት ውስጥ ከከተተ በኋላ በታይበር (Tiber) ወንዝ ላይ ለቀቃቸው። ይህ ወንዝ ዛሬ ሮሜን ለሁለት የሚሰነጥቃት



www.ethiopianorthodox.org

በመሆኑ ታዋቂ ሆኖ እስከ ዛሬ አለ:: እንቦቃቅሎቹም ከወንዙ ደለል ላይ አርፈው ሲላቀሱ ልጆቸዋ የሞቱባት ተኩላ በመምጣት በመንጋጋዋ እያተሸከመች ወደ ዋሻዋ ወሰዳ አሳደገቻቸው:: እረኛም የሆነ ልጅ የሌለው ሰው በታይበር ወንዝ ደርቻ ሲንቀሳቀስ ልዩ የሆነ ድምጽ ከዋሻዋ ሲወጣ ሰምቶ ቢመጣ ሁለት ደስ ደስ የሚሉ የፋፋና መልከ መልከም ወንድ ልጆች በማየቱ ተደንቆና ተደስቶ ወደ ሚስቱ ወስዶ አኖራቸው:: ባደጉም ጊዜ በጦር ሃይለኛ ሆነው የእረኛውን ዘመዶች እና ህዝቦች (Latins or Ethruscans) የሚባሉት ሳይሆኑ አልቀሩም ተከታይ በማድረግ ጠላቶቻቸውንና አጎታቸውን አጥፋተው የሮሜን ከተማ ተኩላዋ ባዳነቻቸው ስፍራ ላይ መገንባት ጀመሩ::



ስዕል 4 የሮሜ መስራቾች ሮሙለስ እና ሬሙስ



ነገር ግን ታናሽየው ሮሙስ ስልጣን ለታላቁ ይለቅ ዘንድ ምልክቶችና ስምምነቶች ስላሰገደዱት ተበሳጭቶ ታላቁን በማንጓጠጥና በመቀለድ «ከተማውን ጠላቶች እንዲህ እያደረጉ ቢያፈርሱትስ ብሎ ቢንደው ታላቁም ተቆጥቶ «እኛም እንዲህ እንመልስላቸዋለን» ሲል በጦር ወግቶ ገደለው:: ይህን አፈ ታሪክን የጥንቶቹ ሮሜዎቸ ተርከው «የሮሜ አሳዛኝ ግንባታ ለዘመናችን የመጀመሪያ ዓመት ነው::» በማለት ይቆጥሩት እና ይከተሉት ነበረ::[1]

ይህ የዘመን አቆጣጠር በመጋቢት (March) የሚጀመር ሲሆን 10 ወሮችና ከነዚህም መካከል ስድስቱ 30 ቀን ሲኖራቸው አራቱ ብቻ 31 ቀን ያላቸው ነበሩ በጠቅላላው 304 ቀናቶች ያሉት የጨረቃ ኡደትን የተከተለ ነበር ይኸው ዘመን መቁጠሪያ ከሮሙለስ ቀጥሎ መንገሱ በሚነገርለት በኑማ ፖምፓሊየስ (715? - 673?) ቅ.ል.ክ ሁለት ወሮች ተጨምረው ነበር:: እነዚህም ጥርና የካቲት ናቸው ሮማውያኑ ጎዶሎ ቁጥር ባላቸው ወራት ክፋነት ስለሚያምኑ ይህ ንጉስ በጥር ላይ አንድ ቀን በመጨመር 30 ሲያደርገው የካቲትን ደግሞ በ28 ቀናት በመተው በጠቅላላው ከቀድሞው ላይ 51 ቀናት ጨምሮበታል:: ስለዚህ የአመቱ ቀኖች ወደ 355 ደርሰው ነበር ወራቱም ከ10 ወደ 12 አድገዋል ::

በዚህ የአቆጣጠር ልማድ ዘመናትን ያሳለፉት ሮሜዎቹ በ43 ቅ.ል.ክ[2] ላይ ዩልዮስ ቄሳር ከእስክንድርያ



www.ethiopianorthodox.org

ሶሴጅነስ የሚባል ብልህ የኮከብ ቆጣሪና የዘመን አቆጣጠር አዋቂ አስመጥቶ ይህንን ግራ የተጋባ የዘመን አቆጣጠር ወደ ግብፃውያን ልማድ መልክ ለውጠህ አስተካክልልኝ ስለ አለው እርሱም የጨረቃውን ወር ወደ ፀሀይ የአመቱን ቀን ወደ 365 1/4 ለውጦ የወሮቹን ስሞች በራሳቸው ባህል ባለው ስም እንዲመቻቸው አስተካክሎ ወሮቹንም ወደ 12 ደልድሎ /በሮሜ ልማድ በነበረው አይነት/ አዲስ የዘመን መቁጠሪያ ሰራለት:: ዩልዮስም «የግራ መጋባት ዘመን» በማለት ቁድሞ የነበረውን ዘመን አቆጣጠር ጠራው:: ከአሁን በኋላም የሮሜ መቁጠሪያ ይህ ይሁን ሲል አዋጅን አወጀ::[3]

የጁልየሰ ዘመን መቁጠሪያ አቆጣጠር በሁለተኛ አመቱ ይህም በ44 ቅ.ል.ክ ላይ የሮማው ምክር ቤት ይህንን ዘመን መቁጠሪያ እንዲሰራላቸው ላደረገው ለጁልየስ ቄሳር ክብር ሲሉ ኩንታይልስ በመባል ይጠራ የነበረውን ወር ወደ ጁላይ /ጁሊየስ ከሚለው የመጣ/ ቀይረውለታል:: በይበልጥ ዘመን መቁጠሪያውን ላጠናከረውና ታላቅ ሥራን ሰርቷል ብለው ለሚያወድሱት ለአውጉስጦስ ቄሳርም ክብር ሲሉ ኦገስት የሚባለውን ወር በ8 አመተ እግዚእ (A.D) ላይ ሰይመውለታል:: ከዚያም በኋላ ሮሜ በቅኝ በምትገዛቸው ሀገሮች ላይ ሁሉ ይህ አዋጅ እንዲሰራበት የሚያስገድድ ስለነበረ በአብዛኛው የሮሜ ቅኝ በሆኑ ሀገሮች ላይ ይህ አዋጅ ሊፀና ችሎአል::



ይህ በዚህ ሁናቴ እየቀጠለ በመሄድ ዘመን በዘመን ላይ ተፈራርቆ አምስት መቶ አመታትን ካሳለፈ በኋላ አንድ አዲስ ሀሳብ መነጨ:: አስቀድሞ የሮሜ መንግስት ክርስትናን ለማጥፋት ያልፈነቀለው ድንጋይ አልነበረም:: በጌታችን ዘመነ ሥጋዌውም ቢሆን አይሁድ ከሳሽ ሲሆኑ ሰቃይ ደግሞ የሮሜ መንግስት ነበር:: እየዋለ ሲያድር ግን እነ ኔሮ የመሳሰሉትን ብሎም እነ ማርከስ አውሬሊየስ የሚባሉትን ፀረ ክርስትና ቄሳሮች ያቀፈ ኤምፓየር ሆኖ ተገኘ

ቆስጠንጢኖስ በ313 እ.ኤ.አ የክርስትና ህጋዊነትን እስኪያውጅ ድረስ በሮማ አለም ውስጥ ክርስቲያኖች የመኖር ያህል እንኳን ቦታ አልነበራቸውም::ድል የአምላክ ነውና ክርስትና መከራውን አልፋ ማሸነፍዋን የተገነዘቡት የሮሜ ገዢዎች በጣኦት አምላኮ ላይ የተገነባው ባህላቸው አብሮ ሊያከትም መሆኑን ለመረዳት ጊዜ አልወሰደባቸውም:: ስለዚህ አዲስ የሆነ ዘመን አቆጣጠርና የድሮውን ማንነታቸውን የሚሸፍን ሌላ ታሪክ ማስመዝገብ ፈለጉ::

በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዲዮናሲዮስ ኤክሲጀስ (Dionysius Exigus) የተባለ መነኩሴ ስለ ጌታችን የልደት ዘመን የግሉን ጥናት ካካሄደ በኋላ ቅደመ ልደተ ክርስቶስ እንዲሁም ከጌታችን ልደት በኃላ ያለው አመት ወይም አመተ እግዚእ ( Before christ and Anno Domini) በማለት ከፋፍሎ ጌታ ተወልዶበታል ያለውን ግምታዊ አመት



www.ethiopianorthodox.org

በማሳወቅ የሮሜ ነገስታት በሙሉ በዚህ እንዲመሩ በጽጽስናው ስልጣን ተጫናቸው:: ይህንን በመያዝ የዩልዮስን ዘመን አቆጣጠርን አሻሽለው ሌሎች አስር መቶ አመታትን ካሳለፈ በኋላ ዮልዮስ የቀመረው ዘመን መቁጠሪያ በ11 ደቂቃ ከ14 ስኮንድ ከእውነተኛው የፀሀይ ኡደት በሽራፊው 1/4 ቀን ምክንያት የቀደመ ነው በማለት በ1582 አመተ እግዚእ ላይ በፓፓ ግርጕሪዮስ አስራ ሰምንተኛው ወሳኔ ተሻሽሎ ዛሬ ድረስ የሚከተሉት ሆኖነዋል:: [4]

ዛሬ ላይ ደግሞ በግል ጥናትና መላ ምት የሃይማኖትን ነገር አስረዳለሁ የሚለው የምዕራቡ አለም ቀድሞ እንደ ጨረባ እነ ኤክሲጆስ የነገሩዋቸውን ሲደግሙ ኖረው ዛሬ ደግሞ በጥናት እንዳረጋገጡት «የኤክሲጆስ ግምት በአራት አመት የቀደመ ነው» ሲሉ በአራት አመት የአሁኑ ዘመን መቁጠሪያቸው እንደሚዘገይ እንዲሁም የተበላሸ ወይም እውነተኛ እንዳይደለ ይመሰክራሉ [5]

በዚህች እንኳን ማስረጃ ብንነሳ ዛሬ 2007 A.D የተሰኘ ው አመት በነርሱ ጥናት መሰረት ስህተት ሆኖ ትክክለኛው 2003 አ.እ የሚለው ከሆነ ለዚህ እንኳን ዘመን በመጠጋት ወደ ትክክለኛነት የሚያመዝነው የኢትዮጵያዊው 2000 ዓ.ም ዘመን መቁጠሪያ ነው:: ምንም እንኳን በሚቀጥለው ክፍሎች ስለ ኢትዮጵያዊው ዘመን መቀጠሪያ ትክክለኛነት የምንገልፅ



ቢሆንም በቀላሉ እንኳን ነጭጮቹ እርስ በእራሳቸው የሚነጋገሩት እና የሚያስተምሩት ምን ያህል የሚጣረስና የሚጋጭ መሆኑን ለማሳየት ብቻ ሲባል ይህንን ለማምጣት ተገድደናል::

ይህ እንግዲህ ስለ ዮልዩናዊው ዘመን መቁጠሪያ በአጭሩ የሚገልጽ ከሆነ አንድ ሰው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ዩልዮሳዊ ነው ለማለት የሚያስችለው ምን ተጨባጭ መረጃ ይኖረዋል::

የዩልዮስ ዘመን መቁጠርያ በ30 እና በ31 ቀን የተከፋፈለ እንዲሁም የካቲት ላይ 28 ቀን ያሉት ዘመን መቁጠሪያ ነው:: የኛስ? የዮልዮስ ዘመን አቆጣጠር በራሳቸው ስያሜ የተሰየሙ ወሮች አሉት እነ ኦገስት እና ጁላይ ደግሞ ከየት እንደመጣ በየትም ባህል ውስጥ ባእድ የቃል ዘር በመሆን ምንጬን ይገልፁ ነበር:: የዩልዮስ ዘመን መቁጠሪያ 12 የውር ድልደል ሲኖረው እኛ 13 አለን ታዲያ እንዲሁ በፍፁም የአይምሮ ጨቅላነት በሚስተዋልበት እነዚህን መሠረታዊ ልዩነቶችን ሳያዩ ዩልዮሳዊ ዘመን መቁጠሪያን ኢትዮጵያ ትጠቀማለች ለማለት የሚገፋፋ አለማ ምን ይሆን? ዮልዮስ አዋጁን ባወጀበት ስአት በሮሜ ቅኝ ያሉ ሀገሮች ሁሉ እንዲከተሉት ያስገደደ ነበር። በመሆኑም የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጣር ዩልዮናዊ ነው ማለት ከተፈለገ ኢትዮጵያ የሮሜ ቅኝ ተገዢ ነበረች ማለት ነው ወደሚለው መምጣት



www.ethiopianorthodox.org

ያስፈልጋል ታሪክ ግን ኢትዮጵያ የሮሜ ቅኝ ተገዢ ነበረች አይልም ይህ አባባል ስለዚህ በየዋህነት የተሰነዘረ ከሆነ ፍፁም ስህተቱን በተንኮል የተወረወረ ከሆነ ደግሞ ክፉ ምኞቱን የሚያስይ ከመሆን ውጭ ምንም ረብ የሌለው ነው።

ሮሜዎች እንኳን ታላቅ ስልጣኔ አለን እያሉ ሲኖሩ ስለ ዘመን አቆጣጠር የግብፅ ሊቅ አስተማሪ አስፈልጐአቸዋል። ከዚህም በመነሳት እንኳን ለኢትዮጵያ ጥንታዊ ስልጣኔ ቀርቶ ለሌሎችም ቢሆን ስለ ዘመን አቆጣጠር ምንም የሚያስተምሩትና የሚዘክሩት የሌላቸው ተማሪዎች መሆናቸውን እንረዳለን ስለሆነም ደግሞ የኛ ዘመን አቆጣጠር ዩልዮናዊ ሊሆን እንደማይችል ያረጋግጥልናል። በተጨባጭ ታሪካዊ መረጃዎች ላይ እንደተቀመጠው እና ከላይ እንዳየነው የኢትዮጵያን ዘመን አቆጣጠር በማስተዋል ረጋ ብሎ ላጠና ሰው ምንጩ ቅብጥ በሀዲስ ኪዳን ስለመሆኑ አያጠራጥርም ያም ባለፈው ምእራፍ በሰፊው ታትቷል።



## ምእራፍ አምስት ማገናዘቢያ ጥቅሶች

1. see Horniblow and Sullivan , **The March of Time mighty men and mighty deeds** (london, 1949)P.19; አስራት ገብረ ማርያም እና ገብረ ህይወት መሀሪ ገፅ 20-21

2. ሁል ጊዜ ቅ.ል.ክ. ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ማለት ሲሆን የአውሮፓውያኑን አቆጣጠር የሚያመለክት መሆኑን መረዳት ይገባል።

3. **The New encyclopedia Britannica** S.V. Calendar Vol. XV. (Chicago, 1993) pp.184-92,187,421-432,

4. Ibid, P.430

5 **Comptions encyclopedia** S.V. Calender; (university of chicgo, 1983) pp.28-29; **Seven day Adventist Bible commentary In seven Volumes** Vo1.5. (Review and Herald publishing Assoication, 1956) S.V Herod. P. 42.



www.ethiopianorthodox.org


# ምእራፍ ስድስት

## ክርስቲያናዊው ዘመን አቆጣጠርና
## መንደርሪያው የሥነ - መለኮት ትምህርት

ክርስቲያናዊው ዘመን እንዲሁም አቆጣጠር (Chrishan era and calendar) መንደርደሪያውና መሠረቱ ጅማሬውና ትምህርቱ ሁሉ የሚነሳው ከአምላካችን ከጌታችን ከመድሐኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ነው:: ይህንን አስመልክቶ ክርስትና አለምን የማሸነፍዋ ነገር ተደምሮበት በምእራቡ አለም በቅዱስ ቆስጠንጢኖስ አዋጅ (Edict of Millan) ክርስትና እውቅና ስታገኝ ብቻ ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን ወደ ክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ ምዕራባውያኑ መምጣት እንዳለባቸውም የጭላንጭል ያህል በአምሮአቸው ተስምቷቸው ነበር:: የግብፅ፣ የኢትዮጵያ፣ የህንድ እና የሶሪያ ክርስቲያኖች ደግሞ ከሐዋሪያቱ ስብከት ጀምሮ የዘመናት መክፈያ በሆነው በጌታችን፣ በአምላካችን፣ በመድሐኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ልደት እንዲቆጥሩ በክርስቲያን መንጋ ላይ የተሸሙት ሐዋሪያት አበው እንዲሁም ጳጳሳት በሙሉ የአዲስ ዘመን መጀመሪያና የአሮጌው እና የጥላው ዘመን ማሳለፊያ አድርገው የዘመን ሥርአትን ስርተዋል::



በዚህም የተነሳ በአለም ላይ ያሉት ሊቃውንት ሁሉ ይህንን የጌታን ልደት የክርስቲያን ዘመን መጀመሪያ /beginnings of Christian era/ በማለት ጠርተውታል የጌታችን መወለድ በክርስትና ትምህርት ውስጥ ሁለት ዘመኖችን የከፈለ አሮጌውን በአዲስ የተካ አለም አቀፋዊ ለውጥ ነው:: በዚህ በክርስቲያናዊው እምነት የዘመን አቆጣጠር ፅንስ ሃሳብ ላይ የተመሰረቱ የአለም ዘመን መቁጠሪያዎች ሁሉ ይህንኑ የሚያመላክቱና የሚገልፁ ቋንቋና ቃላት /terms/ ያሏቸው ናቸው:: እንደ ምእራብያውያን ልማድ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ እንዲሁም ዘመነ እግዚእ /Before Christ and anno domini which means in the year of our lord/ በመባል ይህ የዘመናት እኩል ክፍያ ሲታወቅ እንደ ኦርቶዶክሳወያኑ ሐዋርያዊ ትምህርት ግን ዘመነ ኩነኔ /ፍዳ/፣ ብሉይ ኪዳን የሚባለውና ሰሬ ሽፋን ያለው ክፍያ ጋራ ዘመነ ሐዲስ ወይም ምህረት በመባል የሚታወቀውን የያዘ እንደሆነ ይታወቃል::




ማመልከቻ 1. በዘመን መስመር (time line) ላይ የተመሰረተ የምዕራቡ አለምና የኦርቶዶክሳዊያኑ ዘመን አቆጣጠር መደርደሪያ ስነ መለኮታዊ ትምህርት ልዩነት የሚያሳይ



www.ethiopianorthodox.org


በማመልካቸው ላይ ያለው የዘመን መሥመር (time line) ከፍጥረተ አለም የሚነሳ እንደሆነ እና በህልፈተ አለም የሚገደብ ተደርጐ ውሱን መሥመር ሊሆን ያስችለዋል:: ምእራብያኑ በሚያመልኩት ደረጃ ሳይንሳዊውና ክርስቲያናዊው የተቀላቀለባቸው ማህበረሰብ ስለሆኑ ለፍጥረተ አለም መጀመሪያ የለውም የሚለውን ሀሳባቸውን ቀጣዩ ጨረር ያመለክታል:: ይህ አመለከከት ቁስ አካላዊ /materialists/ እንደሁም ዘገምተኛ ለውጣዊ /evolutionist/ ሲሆን ክርስቲያናዊ የሥነ መለኮት ትምህርትን የማይወክል እንደሚያደርገው ግልጽ ነው:: ለማንኛውም የክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ ሊይዛቸው የግድ የሚገቡ የሚባሉትን መረጃዎችና አመቶች እንዲሁም ታሪኮች ከመጽሀፍ ቅዱስ መነሻነት እንዳስሰዋለን::

ይህንን ከማድረግ በፊት ግን ይህ የኦርቶዶክሶች ባህልና ባሕረ ሐሳብ ልማድ የሚያዘው ትምህርትና መንደርደሪያ እንጂ ምዕራባውያኑ ካቶሊካውያኑ ቢሉ ፕሮቴስታንታውያኑ የማይቀበሉት አካሄድ ነው እንደ ምዕራባውያኑ ከካቶሊካውያኑ ቢሉ ፕሮቴስታንታውያኑ ሌሎቹም ክፍሎች አስተያየት መጽሀፍ ቅዱስ ማስረጃነቱ ጊዜያዊ፣ ህፀፃዊና፣ መረጃ አልባ ሲሆን እንደኛ ደግም በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት በእግዚአብሔር ፍቃድ ያለ ስህተት ያለ እንከን በፍፁም እውነትነቱ እና



በመጨረሻ ወሳኝ ማስረጃነቱን ይዘን ለማናቸውም ጥያቄና ምላሽ ማመሳከሪያም አድርገን እንታመንበታለን::

በዘመን አቆጣጠር ላይ ያለው የምእራብያኑና የኦርየንታል ኦርቶዶክሶች አለመግባባት የሚመነጨው ከዚሁ ዋና አንኳር ሃሳብ እንጂ ከሌላ አይደለም:: «መፀሀፍ ቅዱስ ይወስን» ብለን ለምንጠይቃቸው እንዲሁም መረጃ አድርገን ለምናቀርባቸው ክርክሮች/Arguments/ መልሶቻቸው ሁል ጊዜ «መፀሀፍ ቅዱስ ስህተት አለው» በሚል የክህደትና የምፍቅና መልስ ስለሚቋጩት ነው:: ይህ እንዳለ ሆኖ የኦርቶዶክሶቹ የክርስቲያን የዘመን መሥመር ከመፀሀፍ ቅዱስ ማስረጃነት አንፃር ምን እንዳሆነ እንመልከት::




ማመልከቻ 2:- የኦርቶዶክሱ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃና የዘመን መቁጠሪያ መንደርደሪያ ድንበር የሚያሳይ የዘመን መስመር

ክርስቲያነዊው የዘመን አቆጣጠር በዋነኛነት ከላይ የተዘረዘሩትን ሁሉ የሥነ - መለኮት ትምህርታዊና መፀሀፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች ያሞላ መሆን ይገባዋል:: እነዚህን



www.ethiopianorthodox.org

አመቶችን እና መረጃዎችን ከግልጽ ገለፃ ጋር ያልያዘ ዘመን አቆጣጠር ሙሉ በሙሉ ኢ-ክርስቲያናዊ ስለሆነ ወይም ክርስቲያናዊ ስላይደለ እንደ ማናቸውም በአለም ላይ ያለ እራሱን የቻለ ዘመን መቁጠሪያ ሊያዝ ይገባዋል። ስለሆነም በአሁኑ ሰዓት ቻይና፣ ጃፓን፣ ህንድ እና እስላማዊ ሀገሮች እንዲሁም ጥንታዊ ሥልጣኔዎችና አይሁድ የራሳቸውን ዘመን መቁጠሪያ ይዘው ሲጓዙ ይታያል። ወደ ቀደመው ነገር ስንመለስ ከላይ በተዘረዘረው ሁናቴ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችን ብሎም ድንበሮችን ያካተተ ማንኛቸውም ዘመን አቆጣጠር ክርስቲያናዊ ለመባል በሚከተለው ሁኔታ መረጃዎቹን መተንተን ይገባዋል። በመጀመሪያ ደረጃ ዘመን መቁጠሪያ ሁሉ ከጌታችን ከክርስቶስ ልደት በመነሳት የአለምን ዘመን ለሁለት መክፈል ይገባዋል በሚል መደርደሪያ ይነሳል በማስቀጠልም፣

ሀ. ስለ ጌታችን ልደት የሚያወሳው መረጃ ካለ በመጽሀፍ ቅዱስ የተጠቀሰውን የጌታችን በቤተልሔም በከብቶች በረት የመወለዱን ታሪክ የያዘ መሆን አለበት። ወራቱም በራድ ከመሆኑ አልፎ አምላክ ከናዝሬት ወደ ቤተልሔም ድረስ እመቤታችን ተጉዛ እንደወለደችው መፀሀፍ ቅዱስ እስከ ምክንያቱ በዝርዝር ይገልፃል። ይኸውም አስቀድሞ ያናገረው የትንቢት ቃል ይፈፀም ዘንድ «ቤተልሔም ከይሁዳ ከነገስታት



ሀገር ከቶ አታንሺም ልዑል ካንቺ ይወለዳልና» የሚለው ይፈፀም ዘንድ በቤተልሔም ተወልዶአል። (ትንቢ. ሚኪ. 5:2) አለማዊው ሂደት ደግሞ በዘመኑ ቄሳር ከነበረው ከአውጉስጦስ (አክቴቪያን) ዘንድ ሰው ሁሉ ይፃፍ (ይቆጠር) ዘንድ ትእዛዝ (አዋጅ) ሰላወጣ ቄሬኔዎስ ደጀዝማች በነበረበት ወቅት የአስራኤል ሰው ወደየ ወገኑ ከተማ (የይሁዳ ወደ ዳዊት ከተማ ቤተልሔም) የሌሎቹም ወደየ ወገኖቻቸው (አበው እስራኤል) በመሰረቱት ከተሞች ዘንድ እየሔዱ እንዲቆጠሩ በማስገደዱ ከይሁዳ ወገን የነበሩት ዮሴፍ አረጋዊ እና እመቤታችን ወደ ቤተልሔም ሊቆጠሩ መጡ በዚያም ዘመን እመቤታችን የመውለጃዋ ወራት ገብቶ ነበርና ጌታን በቤተልሔም የከብቶች በረት በነበረችው ዋሻ ወለደችው የሚለውን ታሪክ እናነባለን (ሉቃስ 2:1)

ሌላው ማስረጃ ደግሞ በቤተልሔም ከምሥራቅ የመጡ ነገስታት ከ300 ጭፍሮቻቸው ጋር ወደ ጌታ ዘንድ እንደቀረቡ በጥበብም መንፈሳዊ የተቃኙ በመሆናቸው ስብአ ሰገል ሲል መጽሀፍ ቅዱስ እንደሰየማቸው እነርሱም ጌታ አርባ ቀን ሞልቶት የእርግብ ጫጩቶችን እንደ ኦሪቱ ሥርዓት ሊሰዋ በእመቤታችን እቅፍ ከመሄዱ በፊት መሆኑን እንረዳለን ሰብዓ ሰገል በቤተልሔም አግኝተውታልና ወደ ኢየሩሳሌም ሳይወርድ ገና ከአርባ ቀን በፊት ደርሰዋል። (ማቴ 2:8-12) (አንድምታ ወንጌል ዘማቴዎስ)



www.ethiopianorthodox.org

ለ. ሁለተኛው መረጃ ከጌታ ልደት በኋላ የሄሮድስ ሰይጣናዊ ቁጣ እንደተቀጣጠለ ይኸውም የአይሁድ ንጉስ ወዴት ተወልዷል እያሉ ከምርጥ ጀግኖች ጋር የመጡትን ሰብአ ሰገል ነገስታተ ፋርስን በድንጋጤ ያየው ሄሮድስ ከእነርሱ በተንኮልና በሚያባብል ቃል ስለ ተወለደው ንጉስ እየመረመረ ኮከቡ የታየበትን ዘመን በጥንቃቄ ከተረዳ በኋላ ሁለት አመት እንዳሆነ አወቀ:: ሰብአ ሰገልም በሁለት አመት ጊዜ ከሀገራቸው ተነስተው በኮከቡ እየተመሩ ብዙ እርቀትን ብዙ ጋሬጣን አልፈው ከምርጥ ጀግኖቻቸው እና ጨዋዎች ጋር እየተመሙ መድረሳቸውን ተረዳ::

በዘመኑም ሄሮድስ ስልጣኑን ለማደላደል ሲል ከሮሜ መንግስት ጋር ሆኖ የአይሁድ ስልጣን ተጋሪዎቹን ሲዋጋ ሰንብቶ ኖሮ የእርሱም ተከታዮች ተራውም ህዝብ ጦርነት ሰልችቷቸውና ጠንክሮባቸው ነበርና «ከአለም ዳርቻ እኚህን ሃይለኞች የጠራ እኔን መች ያስነብተኛል» ብሎ ተጨነቀ:: አሁን ብቃወመው እነዚህ ያጠፉናል ይገድሉናል ሲል ሲፈራ ሲተባ ቆይቶ እኔም እንድሰግድለት ካያችሁት በኋላ ንገሩኝ በማለት ዘይዶ ሊያስወግደው አቅዶ ነበር:: ነገር ግን ሳይመጡ በቀሩበት ጊዜ እንደተሳለቁበት ተረድቶ ሰይጣናዊው ቁጣው ተቀጣጠለ::

በዚህም የጌታችን ስደት መጀመሩን በስደቱም ለ3 አመት ከ6 ወር በግብጽና በኢትዮጵያ መዘዋወሩን በዮሐ.እራይ



12:13 -16 ላይ ተፅፎ እንረዳለን:: በዚህ የመፀሀፍ ቅዱስ ገፅ ንባብ ሚስጥሩ ሲፈታ ወንድ ልጅ የወለደችውንም ዘንዶው ተቆጥቶ ሊያጠፉ አሳደዳት (ለጊዜው ሄሮድስ በቁሙ ግን ዲያቢሎስ):- የታላቁ የንስር ክንፍ ተሰጣት እያለ ሲዘረዝር የሄሮድስ ወታደሮች ጌታን ለመግደል የቤተልሔምን አውራጃ እንደበረበሩ ወደ ግብፅም መሔዱን ሰምተው እንደ ተከታተሉት የጌታ መላእክም በለሊት በህልሙ ለዮሴፍ እንደተገለፀ ከፊት እየመራ ከኋላ እየጋረደ እንደተሰደዱ ሲገልጽ ዘንዶውም በኋላዋ ታላቅ ጐርፍን አጐረፈ ሲል በቤተልሔም የፈሰሰውን 144 ሺህ ህፃናት ደም ይገልፃል:: ከእባቡም ፊት ርቃ አንድ ዘመን፣ ዘመናትም፣ የዘመን እኩሌታ ወደ ምትመገብበት ወደ ሰፍራዋ ወደ በረሃ እንድትበር የታላቁ ንሥር ክንፍ ተስጣት በዚያም ቆየችም ይለናል::

ሐ. ጌታችን የስደቱ ዘመን አልቆ ወደ ምድረ እስራኤል በመጣ ጊዜ በ12 አመቱ ወደ ቤተመቅደስ ገብቶ ከእናቱ ተለይቶ ለአራት ቀን የኦሪትን ሊቃውንት እና ሊቀ ካህናት ሲጠይቅና ሲያስረዳቸው ሚስጢር ሲገልጥላቸውና ማንነቱን ይረዱ ዘንድ ሲያመለክታቸው ያለውን ታሪክ እናነባለን:: (ሉቃ 2:42)

መ. ጌታችን ጊዜው ደርሶ ወደ አለም የመጣበትና የድህነት ሥራ በእጆቹ ታምራት እያፀና በአፉ ትምህርት እያቀና የሚሰብክበት በግልጽ ለህዝብ የሚታይበት ስአት



www.ethiopianorthodox.org

በደረሰች ጊዜ በይሁዳ ምድር ወደ ነበረው ወደ ዩርዳኖስ ባህር መጣ በዚያም የጌታን መንገድ እየጠረገ ህዝቡ ሁሉ ለወንጌል ትምህርት ልባናውን ያቀና ዘንድ የታዘዘው ንፁሁ ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት ነበር:: ጌታም ወደ ዩርዳኖስ ባህር በመጣ ጊዜ እድሜው 30 አመት ሆኖ ነበር:: ወንጌል ይህንን ሲያስረዳ «ኢየሱስም ሊያስተምር ሲጀምር እድሜው ሠላሳ አመት ሆኖ ነበር »ይላል (ሉቃስ 3:23)

ሠ. ጌታችን መጽሐኒታችን መላዋን እሥራኤልን ለ3 አመት ከ3 ወር ከሀገር ሀገር እየተዘዋወረ ያስተማረበት የድህነትና የምህረቱን ነገር ሊፈጽምልን ጊዜው ሲደርስ አዳም ሊቀጣ በሚገባው ቅጣት ካሳ እራሱን ስጥቶ በሞቱ ከሲኦል ውስጥ እና ከአጋንንት እግር በታች ተጠቅጥቀን እንኖር የነበርነውን የሰውን ልጆች በታላቅ ሃይል መንግስቱን የምንወርስበትን ከመከራ እና ከፍዳ (ከሲኦል) ነፃ የወጣንበትን ትንሳኤውን ሰጠን:: ይህም በመፅሀፍ ቅዱስ ተመዝገቦአል:: ይህንን ዘመን በዋና ማስረጃነቱ በመያዝ ተያያዥ ታሪኮችን ደግሞ በማመሳከር በጌታችን ዘመን ከተነሱ የታሪክ ፀሀፊዎች ሥራ ጋር በማያያዝ ስለ ክርስቲያናዊው የዘመን አቆጣጠር ከብዙ በከፊልና በዝርዝር መናገር ያስችላል::

መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተመዝግቦ ለታሪክ ማነፃፀሪያ ከሆኑት አበይት ምልክታዎች መካከል ጥቂቱን ስንመለከት ወሳኝ የሆኑ ድንበሮችን በዘመን መስመር ላይ በማስቀመጥ



የምንዘግበው ስለ ዘመን አቆጣጠር ከኢ-ክርስቲያናዊው የአለም ታሪክ ሂደት ጋር በተለየ መልኩ ስላለው ሁኔታ በይበልጥ እንድንገነዘብበት ነው:: ለምሳሌም ያህል የሚከተሉት ታሪካዊ ክንውኖች ስለ ክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ ታሪካዊ ማመሳከሪያ በመሆን ፍንጭ ይሰጣሉ::

ሀ. የጌታችን የስደት መልስ «ከሞተ ሄሮድስ» ጋር መያያዙ በሚገባ ተዘግቧል:: በወንጌል ማቴ2:19 እንደተፃፈው ሄሮድስም ከሞተ በኋላ እነሆ የጌታ መልአክ በግብፅ ለዩሴፍ በሕልም ታይቶ «የሕፃኑ ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ ሕፃኑን እናቱንም ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ አለው» ይላል:: ይህም ሄሮድስ ልክ ሲሞት ጌታችን ከግብፅና ከኢትዮጵያ ስደት የመመለሱን ጉዞ ጅማሬ እንረዳለን::

ለ. በተያያዥ ከሄሮድስ ሞት በኋላ ልጁ አርኬላዎስ በመንገሱ «የክፉ ልጅ ክፉ» እንዲል እንድምታው በይሁዳ ይቀመጥ ዘንድ አልወደደም ወደ ናዝሬትም ሄዶ ተቀመጠ:: ሲል (ማቴ 1:22-23) ታሪካዊውን ሂደት ይገልፃል ከሄሮድስ ሞት በኋላ በልጁ አርኬላዎስ አገዛዝ ወይንም ንግሥና ጌታ ከስደት መመለሱን በቀጥታም ናዝሬት መግባቱን እንረዳለን



www.ethiopianorthodox.org

ሐ. በቤተክርስቲያናችን ታላቅ ሚስጥር ጓዳነት ብቻ የተገለ በዓለም የተቃጠሉ እና የተበረበሩ እንዲሁም የተመዘበሩ የሃዋርያት መፃህፍት ሲጠፉ በእኛ የዳኑት ጌታ ናዝሬት ሲገባ ወይም የእድሜው ነገር ከልደቱ ጀምሮ እስከ እርገቱ የሚናገረው ላይ ስንት እድሜ እንደለው የሂደቱንና የታሪኩን ይዘት ሳይዘባርቅ በትክክል ያስቀምጠዋል:: (ተአምር ኢየሱስን ተመልከት)

ተአምረ ኢየሱስ ጌታ ናዝሬት ሲገባ 5 ዓመቱ ነበር ይለዋል (ምዕራፍ 8 ተመልከት) ጌታችን ወደ ግብጽ ሲሰደድ የስድስት ወር ጊዜ በመውሰድ (ይህም ከቤተልሄም እንደ አንድምታው ሳይውል ሳያድር ተሰዶ ግብጽ ሲገባ የሆነውን ሲያመላክት) ከግብጽ ደግሞ እስከ ናዝሬት መንገድ ይርቃልና በይሁዳ ሳይቀመጥ አርኬላዎስ መንገሱን ሰምቶ ይሄዳልና ለስደት ሲነሳ ሁለት ዓመት ቢሆነው ግብጽ ሲወርድ ሁለት አመት ከስድስት ወር ላይ 3 ዓመት ከ6 ወር ሲደመር 6 አመት ሆኖት ናዝሬት ሲገባ ከ6 ዓመት በላይ በደረሰ ነበር:: ስለዚህ ግብጽ ሲደርስ የስድስት ወር ህፃን ነበር የሚለውን ማስተዋል ያስፈልጋል::

ሰልስቱ ሀዲሳት ትርጓሜ እራዕይ ዮሐንስ ገፅ 424 ላይ ግብፅ እመቤታችን ስትሄድ 6 ወር ስትመለስም 6 ወር ወድሶባታል ይላል::



መ. የጌታችን የልደቱ ዘመን በአውጉስጦስ ፣ስቅላቱ ደግሞ በጢባርዮስ ቄሳር ዘመን ስለመሆኑ በግልፅ በወንጌል ተዘግቦአል:: ይህም ማለት በተሳሳተው ግሪጎሪያውያኑ ወይም ዩልዮናዊው ዘመን መቁጠሪያ አውጉስጦስ 27 ቅ.ል.ክ (ሉቃስ:2:2) ጢባርዬስ ደግሞ 14 ዓመተ እግዚእ (ሉቃ3:1) ዘመን ላይ መኖራቸውን ዘግበዋል:: ይህንንም እንዲህ ሲል ይገልፀዋል በዚያም ወራት አለም ሁሉ እንዲፃፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣች ቄሬኔዎስ በሶርያ አገረ ገዥ በነበረ ጊዜ ይህ የመጀመሪያ ፅሕፈት ሆነ «ጢባርዮስም በነገሠ በአሥራ አምስተኛይቱ ዓመት የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሐንስ መጣ»

ሠ. ጌታችን የተወለደበት ጊዜ በአውጉስጦስ ሰው ሁሉ የሚቆጠርበት (ለግብር የሚፃፍበት) አዋጅ የወጣበት መሆኑ ሌላ ታሪካዊ ሂደት ነው::

ረ. ከጌታችን ልደት በፊት በሮሜ ቅኝ የነበሩት አይሁድ ነፃነትን በመፈለግ በመጀመሪያ በቴዎዳስ በመመራት አመፅ ማስነሳታቸውን ሰዎችም በተፃፉበት ዘመን ወይም በተቆጠሩበት ይህም በጌታ ልደት አመት የገሊላው ይሁዳ ደግሞ ሌላ አመጽ ማስነሣቱ በግልጽ ተዘግቧል:: ይህም ሌላው የታሪክ ምልክታ ሆኖ እናገኛዋለን:: (ሐዋ ሥራ 5:37)



www.ethiopianorthodox.org

እነዚህን የአለማዊ ታሪክ ፀሀፊዎች የዘገቡትን ጊዜዎች ወይም ዘመኖች አለበለዚያ አመቶችን በማጥናት እና በማገናዘብ ከመፀሀፍ ቅዱስ የጌታችን ዘመን ጋር በማመሳከር ወደ ክርስቲያናዊው ዘመን መቁጠሪያ ላይ መድረስ ይቻላል:: በሚቀጥለው ክፍልም ይህንኑ በመፈፀም የክርስቲያናዊው ዘመን አቆጣጠር እና የዘመን መስመር (time line) ምን እንደሆነ እንረዳበታለን::



## ምእራፍ ሰባት
## የምእራባውያን ዘመን አቆጣጠር አጭር ታሪካዊ አመጣጥ

በአለም ላይ አሉ ከተባሉት ከቀደምት ዘመን መቁጠሪያዎች መካከል ግብፅ፣ ሜሶጳጣሚያ፣ ቻይና፣ ህንድ፣ ጃፓን እና የደቡብ እንዲሁም መካከለኛው አሜሪካ ስልጣኔዎች ተጠቃሽ ናቸው:: ከዚህ ጋር ሊደመር በማይችል መልኩ በጦር ሙያና አደረጃጀት ብቻ እየገነነ የሜዲትራኒያንን አለም ለማስገበር የቻለው የሮሜ ሥልጣኔ ግን ዘመን መቁጠሪያው ከባእድ አምልኮ እና ከወቅት መፈራረቅ ጋር የተያያዘ እጅግ ያልበሰለ ነበር::

በምእራቡ አለም እንኳን ጥንት ዛሬ ድረስ የስልጣኔ መሰረታቸው አድርገው በመውሰድ የግሪክ /ፀርእ/ እና የሮሜ ሥልጣኔ ላይ ሲመፃደቁ መስማት በጣም የተለመደ ነው:: ይህ ደግሞ የዘመን አቆጣጠር ሥርዓታቸውንም ጥንትነት ስንመረምር ከዚያው ተወራሽና ተመሳሳይ ከሆነ ጣኦት አምልኮ የፈለቀ በተረታዊ ትረካዎች የአየር ፀባይና የወቅት መፈራረቅ የሚገልፁበት ክፍል ያለው መሆኑን እንረዳለን:: ለምሳሌ ያህል «የአፖሎ ልጅ በፀሀይ ሰረገላ ላይ ወጥቶ ፈረሶቹን መያዝ ስላልቻለ ዝቅ ብለው በጋለቡበት በረዶው ቀልጦ ደረቅ በረሃ በመሆኑ በድንጋጤ ወደ ላይ በጣም ከፍ ቢያደርጋቸው ወደ



www.ethiopianorthodox.org

ላይ በመንጎዳቸው በሰሜኑ የአለም ክፍል በረዶ የተሸፈነ ሆነ» እያሉ የማያስተምሩት የጣኦት አምልኮ ሀይማኖት ነበራቸው::

የሮሜ ዘመን መቁጠሪያ ከግሪክ ስልጣኔ የተወረሰ ቢሆንም ቅሉ እንደ ዩልዮሳዊው ዘመን መቁጠሪያ እና አቆጣጠር ከ753 ቅድመ ልደት ክርስቶስ ጀምሮ ያለውን የሮሜ ከተማ ግንባታን እንደ ዘመን መቁጠሪያው መጀመሪያ /Beginning point of a calendar/ መጠቀም የጀመሩ ሲሆን ለብዙ ዘመናት ይህንኑ የዘመን መቁጠሪያ ይዘው ቆይተዋል:: ይህ የሮሜ ዘመን መቁጠሪያ በጨረቃ ኡደት ላይ የተመሰረተና በአስር ወር በኋላም በ12 ወር የተከፋፈለ ነበር:: ይህን በተለያየ ወርና አምልኮ ጋር የተያያዘ ዘመን መቁጠሪያ አስመልክቶ በጥንት ጊዜ ከመካለኛው ምስራቅ ሮማውያኑ የወረሱትም ሊሆን እንደሚችል አንዳንድ ፍንጮች ይጠቁማሉ::

ለምሳሌም ያህል በሮማውያን ስለ ከዋክብት ቆጠራ አስተማሪዎቹ ከቻላይዲያ (Chaldea) የመጡ በመሆናቸው ካላዲያንስ ወይም ቻላዲያንስ በመባል ይጠሩ እንደነበር እነርሱም ስለ ወቅቶች፣ ስለ ከዋክብት አቀማመጥ፣ ያስተምሯቸው እንደነበረ የተዘገበ ነው:: ኋላ ቀሩ የሮማውያን ጥንታዊ ዘመን አቆጣጠር ሌላው የሚታወቀው የመጀሪያው ወር የአመት መባቻው ክረምት ላይ መዋሉ ነው:: ይህ ወር ጃንዋሪ የሚለው አመጣጡ ሮማውያን በብርድ ወራት ከበር



ደጅ የሚኖር መንፈስ አለ ብለው ከማመናቸው የተነሳ ጃነስ (Janus or Sprit of the Door way) በማለት ከሰየሙት ሀረግ የተገኘ ነው:: ይህ ሥረ መሰረቱ በጣኦት አምልኮ ላይ የተንጠላጠለ ተረትና የወቅት ቀመር ዛሬ ድረስ ዘልቆ እንደሚገኝ ማስተዋል ይቻላል:: [1] በአብዛኛው የአለም ክፍል አዲስ አመት ተብሎ የሚታወቀው የፀደይ ወራት እንጂ ክረምት መግቢያ አይደለም:: ይህም በህንድ፣ ቻይና፣ በኢትዮጵያ፣ በእስራኤል እና በግብፅ ተጠቃሽ ነው::

ይህንን የዘመን መቁጠሪያ ይዘው የዘለቁ ሮሜዎቹ በጁሊየስ ቄሳር አማካኝነት ዩልዮሳዊ ዘመን አቆጣጠርን በግብፃዊው ሊቅ በሶሴጅነስ (sosigenes) አማካኝነት የተሰራላቸው በመሆኑ ወደ ተለያየ የአለም ክፍል ይህንኑ የዘመን መቁጠሪያ በቅኝ ሲገዟቸው በነበሩ ህዝቦች ላይ ጭነውታል:: በመሆኑም ለ400 አመታት በባርነት ይገዟቸው የነበሩት እንግሊዛውያን የሮማውያኑን የዘመን መቁጠሪያ እንዳለ ቢወርሱም የጥንት የባዕድና የጣዖት አምልኮ ኋላቀር ዘመን አቆጣጠራቸውን አሾልከው ያገቡበት በመሆኑ ዛሬ ላይ ቆመን ስንመረምር በተጨባጭ ማስረጃ እናረጋግጣለን::

ለምሳሌ ያህል የእንግሊዝ አንግሎሳክስን ጐሳዎች ጠረኛ አማልክቶች ነበሩዋቸው በእነዚህም የያንዳንዷን ቀን ለእነርሱ ግብር የሰጡ በመሆኑ ቀኖቹ ሁሉ በስማቸው ተሰይሞአል:: ለምሳሌ (Mon-day) ሰኞ በጨረቃ (moon- day) ቀን



www.ethiopianorthodox.org

አስመልክቶ ለጨረቃ ጣኦት የተሰጠ ነበር (Tu's day) ማክሰኞ Tu'S ለሚባል ጣኦት (Weden's-day) እሮቡ woden ለተሳኘ የጦር ጣአት (Thur's –day) ደግሞ ሀሙስ ሆኖ Thor ለሚባል ጠኦት የተለየ ሲሆን Friea's-day በመባል የሚታወቀው አርብ ለዚሁ በተለየ ቀን መስዋት የሚሰውላት የሴት አማልክት መክበሪያ ሲሉ የለዩት በመሆን አገልግሏል:: ለኮከቡ (አለመ ሰማይ) ወይም(planet) saturn ቅዳሜ ሲሰየም የፀሀይ አምልኮን ደግሞ ለማመልከት (Suns-day or Sunday ) የሚለውን የSunday መግለጫ ትርጉም ያለው ሆኖ የባዕድ አምልኮ የእምነት ታሪክ እንዳላቸው ፍንጭ ይሰጣል:: ይህንን ሁሉ ሳስተዋለው የዛሬው ምዕራባዊ ዘመን አቆጣጠር ምን ያህል በስልጣኔ ያልበሰለ ማህበረሰብ የፈለቀና የተሰራ እንዲሁም ኢ-ክርስቲያናዊ መሆኑን ማረጋገጥ አያዳግትም::

---

1. See Sergew, p. 200; ________. World history, vol. I USA Armed forces institute (Wisconsin, 1970) p. 124; ምንም እንኳን ይህ የተረጋገጠ ቢሆንም አንደንድ ፀሀፊዎች አውሮፓውያኑ ታህሳስ 28 ተከትለው ጌታ ከተወለደበት አመት ጀምሮ አዲስ አመት መሆን አለበት ብለው ጥርን አዲስ አመት አደረጉት የሚሉት ሀሳብ አለ:: ነገሩ ግን እስከ 1600 አ.እ.ድረስ በእስኮትለንድ እንዱሁም በእንግሊዝ እስከ 1751 አ.እ ድረስ አዲስ ዘመን በመጋቢት March 25 ላይ



ይውል ነበር:: ከላይ ከተጠቀሱት ጊዜዎች ጀምሮ ወደ ጥር (January ) ተዘዋውሮአል::

ይህ ሁናቴ ቀጥሎ በመንዝ የጌታችን ልደትን ሁሉ አልፎ የዘለቀው የዩልዮስ ዘመን መቁጠሪያና የሮሜ ቄሳሮች ጣኦት አምልኮና የባእድ አምልኮ ባህል በክርስትና ድል መንሳት አዲስ ምእራፍ ተለውጦ እንዲተካ አስገዳጅ ሁናቴ ተፈጠረ:: ነገሩ የሚጀምረው በቆስጠንጢኖሰ የክርስትና ሐይማኖትን ህጋዊነት በሚሳኑ አዋጅ በእ.ኤ.አ 313 ላይ የማወጅ ሥራ ነው:: ቆስጠንጢኖስ ይህን መሰል ውሳኔ ሊያሳልፍ የቻለው በ311 ዓ.ም ላይ ለስልጣን ተቀናቃኙ የነበረውን መምልኬ ጣኦት ማክሲመስ እንደ አሸዋ የበዛ ሰራዊት ይዞ ለጦርነት ሊገጥመው በቀረበ ጊዜ በተደረገለት ተአምር የተነሳ ወደ ክርስትና ሃይማኖት የመግባቱን ብፀአት ተከትሎ ነው::

ስለዚሁ ጉዳይ ታሪኩ ሲተረክ ይህን ይመስላል:: ቆሰጠንጢኖስ የከበበውን አደጋ ከተረዳ በኋላ ጭንቀትና ውጥረት ናላውን አዙረውት መድረሻ ያጣ ሲመስለው ወደ እናቱ እሌኒ ሀይማኖት አስተውሎ መፀለይ ጀመረ:: ለሊቱንም ታላቅ እራዕይ /ህልም/ ተገለፀለት በሰማይ ላይ ብሩህ የብርሃን መስቀል በጦር ሰራዊቱ ላይ እያበራ የእርሱም ጦር ፈረሰኞች እየፋነኑ ሲተሙ ጭንቀትና ፍርሃት ከእርሱ ሲርቅ ተስማው ታየውም ከመሰቀሉም ውስጥ ታላቅ ድምጽ ወጥቶ ይህንን



www.ethiopianorthodox.org

ቃል ተናገረው በዚህ መስቀል ምልክትነት አንተ ታሸንፋለህ /In hoc signo vinces/ በጠዋቱም ጦር ሰራዊቱን አስልፎ ሁሉንም በቀይ ቀለም መስቀልን ምልክት በመሳ አካላቸው እንዲያደርጉ አዘዘ በጦርነቱም ጠላቱ ሸሽቶ ሲጋልብ ከታይበር ወንዝ ገብቶ ሰጥሞ ሞተ:: የዚህ ታሪክ መጨረሻው የአፄ ካሌብና እና የፊንሀስ ጦርነት ጋር በመመሳሰል የሚያስደንቅ ነው::



ሥዕል 5: ቅዱስ ቆስጠንንጢኖስ ወልደ እሌኒ የተመለከተው እራዕይ የሚያሳይ



የሆነ ሆኖ ከዚህ በኋላ ክርስትና እና ክርስቲያኖች እንደይነኩ ትዕዛዝ ወጣ:: ሮማዊው አለም ግን ክርስትናን በመንግስት ሀይማኖት ደረጃ ለመቀበል ገና የቴዎዶሲየስን አዋጅ በ393 እ.ኤ.አ መጠበቅ ነበረበት:: ክርስትና በሮሜ ስልጣኔ ውስጥ ስር በሰደደቸበት ወቅት ይኸውም በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዲዮናሲዮስ ኤክሲጀስ የተሰኘ ጳጳስ ተነስቶ ከዛሬ ጀምሮ በክርስቲያናዊው ዘመን አቆጣጠር መቁጠር አለብን በማለት አዲስ መንፈሳዊ አዋጅን አወጀ በዚህም ምክንያት ለ500 አመታት አንድ ቀን እንኳን ወደ ኋላ መለስ ብለው ስለ ጌታ ልደት ስለ ዘመነ ፍዳ ህልፈት እና የዘመነ ምህረት መስጠት አስበው የማያውቁት የሮሜ ቄሳሮች የድሮውን የዩልዮስ ዘመን አቆጣጠር ክርሲቲያናዊ ለማስመሰል ተሯሯጡ::

ዲዮናስዮስም በግሌ ባጠናሁት ምርምር መሰረት ክርስቶስ የተወለደው ከሮሜ ጥንታዊ ግንባታ ተነስቶ ሲቆጠር 753ኛው አመት ላይ ነው ሲል ያመጣውን ስሌት እንዲሁ ተቀብለው በዩልዮስ ዘመን አቆጣጠር ላይ በመለጠፍ ወደ ፊት ተጓዙ:: ውሎ ሲያድር ግን ኮከብ ቆጣሪዎቻቸውን የዘመኑን ቀንና የወቅቱን ነገር አጢነው ከምድር ወገብ አመት /12 ስአት ብርሃን እና 12 ሰአት ሌሊት/ ይረዝም የነበረው ማለትም 365.242197 ቀናት ጋር የማይስተካከልና ቅድሚያ ያለው የዩልዮስ ዘመን መቁጠሪያ መሆኑን አስገንዝበው በእነርሱ



www.ethiopianorthodox.org

ስሌት መሠረት የ11 ደቂቃና 14 «ሰኮንድ» ቅድሚያ በየአመቱ ተደማምሮ በ1000 አመት ውስጥ 7 ቀናት ሊደርስ እንደሚችልም አሳዮ::

ይህንን ችግር ለመቅረፍ ፓፓ ግሪጎሪ አስራ ስምንተኛ ክስቶፈር ካልቪነስ (1537-1612) የተሰኘ ኮከብ ቆጣሪውን በመያዝ በ1583 ስብሰባ አድርጎ በዘመናት እየተንከባለሉ የመጡትን አስር ትርፍ ቀናት በአንድ ለሊት ውስጥ ለማጥፋት ወሰነ ይህንንም ጥቅምት 5 ይውል የነበረውን በማግስቱ ይከበር የነበረውን «የቅዱስ ፍራንሲስ» በአል ሰው ከእንቅልፉ ሲነቃ በአዋጅ «ዛሬ ጥቅምት 15 ሆኖአል» ተብሎ በዚህም አስር ቀን እንዲወድቅ አደረጉ ማለት ነው:: ይህ የተሃድሶ አካሄድ የጎርጎሪዮስ ዘመን አቆጣጠር በሚል አዲስ ሰያሜ ስለታወቀ በፊት የዩልዮስ ከዚያም «ክርስቲያናዊ» ቀጥሎም ዛሬ በመሻሻል ሂደት «ግሪጎሪያን ካላንደር» የተሰኘ ውን ዘመን መቁጠሪያ ሊጠቀሙ በቁ::

ምዕራባውያኑ እንደለመዱት ዛሬም «የግሪጎሪያን» ዘመን መቁጠሪያ ችግር የሞላበት ነው::» ማለታቸውንም አላቋረጡም በአሁኑ ጥናት መሠረት የጎርጎሪዮስ ዘመን አቆጣጠር እንደ ፍራሽ አሁንም ታድሶ ወደ አለም አቀፋዊ ዘመን አቆጣጠር መምጣት አለበት ይሉናል ይህም በሁለት መንገድ የተዘጋጀ ነው የመጀመሪያው አለም አቀፋዊ (International calendar) የተሰኘው ዘመን መቁጠሪያ 13 ወሮች



ያሉትና በ28፣31 እና 30 የሚዋኙቁት ወሮች ሁሉ 28 በማድረግ አንድ ወጥ የሚያደርግ ሲሆን፣ የአለም (World calendar) የተሰኘው ዘመን መቁጠሪያ ደግሞ አንድ አመትን በአራት ወቅት የሚከፍልና እያንዳንዱ ወቅት 91 ቀናት ብቻ ያሉት ሲሆን አንድ ትርፍ ቀን የመጀመሪያው ወቅት ላይ የምትደመር ያለው ያደርገዋል ይላሉ::

ይህ አስራር ከተዘጋጀ የቆየ ቢሆነም /20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው/ ዛሬ ድረስ በተግባር አልዋለም:: ምክንያቱ ደግሞ ለዘመናት እንደፈለጉ ሲያድሱትና የተለያየ ስም ሲሰጡት የነበረውን ዘመን መቁጠሪያቸው ይህን የመሰለ ለውጥ ቢያመጡበት ያለፈውን አቆጣጠር የሚያዛባና የሚያደናግር ስለሚያደርገው ወደ ስራ ይዘውት እንዳይገቡ ፋርሃቱ እንደ ቆፈን ወጥሮ ይዞአቸዋል:: ታዲያ «የራሷ ሲያርባት የሰው ታማስል» እንደተባለችው የመንደር ሴት በብዙ ችግር ተተብትቦ በጓዳቸው ባለው የዘመን መቁጠሪያ ላይ ብቻ አተኩረው መስራት ሲገባቸው ስለኢትዮጵያዊው ዘመን አቆጣጠር ማን አስተያየት ስጡ አላቸው? ይሄ ደግሞ ከፍርሀት ለመላቀቅና የአለምን ተቀባይነት ለማግኘት ወደ እውነትና ስህተትን ማመን መምጣት እንዳለባቸው ያሳያል:: እንዲሁም ለሰው ልጆች ፍቅር ኖሯቸው ወደ ሰላም መድረስ እንዳለባቸው ባለመረዳትና ባለመፈለግ የመጣባቸው ችግርን



www.ethiopianorthodox.org

የሚያሳይ ነው:: መፅሀፍ ቅዱስ «ፍቅር የፍርሃትን መንፈስ ያጠፋል» አይደል የሚለው! (1ኛ ዩሐ 4:18)



# ምእራፍ ስምንት

## የጌታችን የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደትና የሄሮድስ መንግስት

በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ እንደተገለፀው ጌታችን ሲወለድ ሄሮድስ ገሊላን እና ይሁዳን ጨምሮ ትራኮኒታስ፣ ቢታንያ እና የሃራንን አውራጃዎች ይገዛ ነበር:: ይህ ሄሮድስ በጌታ በሥቅለት ጊዜ ገሊላን ከገዛው ከልጁ ከሄሮድስ አንቲጳ የተለየ ነው ስሙም ሄሮድስ ወልደ ሐንጼፌር (አንቲጳተር) (Herod Antipater) በመባል ይታወቃል (ማቴ2:1:2) (የሉቃ 3:1) (ሉቃ 3:19) የገሊላን አውራጃም ከይሁዳ ጨምሮ እንዲገዛ በሮሜ ነገስታት በኦክቴቪያንና፡አንቶኒ የተወደደ ስለነበረ ተፈቅዶለታል::

በታሪክ እንደተዘገበው ይኸኛው ሄሮድስ የሮሜ ስራዊት የይሁዳ ወይም ምድረ እስራኤልን በቅኝ እንድትገዛ ወሳኝ የሆነ እርዳታን በፓርቲያውያን ጦርነት ጊዜ በማድረጉ ለዚህ ሥልጣን እንደበቃ ይታወቃል:: ‹ሄሮድስ ታላቁም› በመባል እንዲሞካሽም ምክንያት ሆነውለታል:: ይህ ሰው የቤተልሔምን 144,000 ህፃናትን ብቻ ሳይሆን የስልጣኔ ባለንጣ ናቸው ያላቸውን የራሱን ሚስት እና ልጅ (ማርያሚን



www.ethiopianorthodox.org

እና አንቲጳተር) ያስገደለ ነበር። በማቴዎስ ወንጌል በማቴ 2 ቁጥር 1-2 እንደተፃፈው ጌታችን ሄሮድስ በሚያስተዳድርበት ዘመን መወለዱን እንረዳለን ይህንንም መንፈሳዊ ጉዳይ ሄሮድስ ሊረዳ የቻለው በሰብአ ስገል መምጣት ምክንያት ነበር ።[1]

ይህንን በጥልቀት የሚገልፀው መፀሀፍ ተአምረ ኢየሱስ ነው። በተአምረ ኢየሱስ ላይ ስለ ሰብዓ ስገል ስለ ሄሮድስ እና ስለድንጋጤው ስለ ወስደው እርምጃ አንድ በአንድ ይዘረዝራልና ማየቱ ይበጃል ።

ለምሳሌ በተአምረ ኢየሱስ 7ኛ ተአምር ገፅ 28 እንዲህ የሚል ገፀ ንባብ አለ ቁጥርም11 ላይ ጀምረን ስናነብ «በኮከቡም ላይ እንደ ፀሀይ የሚያበራ ልጅዋን ታቅፋ ድንግል በብርሃን ዙፋን ተቀምጣ ትታያለች በልጅዋም እራስ ላይ የጌትነትን ዘውድ ተቀዳጅቶ ይታያል ይህ በታየ ጊዜ ሕፃኑ የተወለደበትን ቦታ ፈልጋቸሁ ማግኘት ይገባችኋል። ይህ ልዩ ኮከብ ስለ እርሱ በስማይ ላይ ታይቷልና።» ሲል የስብአ ስገል አመጣጥን ያወሳል።

---

1-See the source professor Shmuel Safari, The History of Israel from ancient **times to the modern formation** (Jerusalem, 1973) pp.114-118



ከቁጥር 12 ላይ «አስቀድሞ አባታችን አዳም ከገነት ወጥቶ ከተቀመጠበት ከደብረ ቅዱስ ተገኝቶ አባቶቻችን ያስቀመጡት ወርቅና ከርቤ ስለ ጌትነቱ ክብር እጅ መንሻ አቅርቡለት የሚል ፀሑፍ አገኙ»

ከቁጥር 13 «ከዚህም በኋላ ሶስቱ ነገሥታት ሕፃኑ የተወለደበትን ቦታ ለማግኘት ምድርን ይዞሩ ዘንድ ቆርጠው ተነሱ ከነርሱም ጋር ሶስት መቶ ጭፍራ አስከትለው ወረቅና ከርቤውን ይዘው ኮከብ እየመራቸው ከምሥራቅ በኩል መጡ።»

ከቁጥር 14 «በጉዞአቸውም ጊዜ ብዙ ችግርና ፈተና ደረሰባቸው አገራቸው እጅግ እሩቅ ነበርና ኢየሩሳሌም እስኪደርሱ ሁለት አመት ፈጀባቸው »

ስምንተኛው ምዕራፍ ላይ ያለው ተአምር ደግሞ እንዲህ ይላል «ስለ ጌታ ኢየሱስ መወለድ የምሥራቅ ነገሥታትም ማለትም ስብአ ስገል ከብዙ ሠራዊታቸው ጋር ከሩቅ ሀገር ወደ አየሩሳሌም በመጡ ጊዜ የሀገሪቱ ሰዎች ስለሰዎቹ ሁናቴ ፍርሃት ያዛቸው።»

ቁጥር 3 «በዚያን ዘመን በኢየሩሳሌም የነገሰው ሄሮድስ ነበርና ሰዎቹን ከመፍራት የተነሳ ከብዙ ገፀ በረከት እና እጅ መንሻ ጋር ወደ ፋርስ ነገሥታት መልክተኞች ላከ።»



www.ethiopianorthodox.org

ቁጥር 4 «መልክተኞቹም ለፋርስ ነገሥታት እጅ መንሻውን አድርሰው ወደ ፍልስጤም ምድር በምን ምክንያት እንደመጡ ጠየቋቸው።»

ከገፅ 33 ላይ «ነገሥታቱም ለተወለደው አምላክ እጅ መንሻ ካቀረቡለት ከሰገዱለትም በኋላ ወደ ሀገራቸው ለመሄድ ሲነሱ አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የፀናች ክብርት እመቤታችን የገብስ ዳቦ ስንቅ አሲያዘቻቸው ሌላ ምንም ነገር የላትም ነበርና።» እያለ ስለታሪኩ ይገልጥልናል።

በዚህ ሁሉ የምንረዳው ጌታ የሚወለድበት ሰአት በቀረበ ጊዜ ሰብአ ሰገል ከሀገራቸው መነሳታቸው እና በእግዚአብሔር መልአክ እየተመሩ ቤተልሔም በመድረሳቸው ሄሮድስ በፍርሃት መጨነቁን የሥልጣንም ጥመኛ ነበርና ከመንግስቴ ልወገድ ነውም ሲል በቤተልሔም ምድር ብቻ ያሉትን ህፃናት ማስወጨፍጨፉን እናይበታለን።ይህ በሆነ ጊዜ ጌታችን በእመቤታችን እቅፍ ሆኖ መሰደዱን የሚገልጽ በመሆኑ ዋና ማስረጃ አድርገን ታሪኩን እንረዳበታለን። አንድምታ ወንጌል (Exigency) እንደሚያብራራው በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 2 ቁጥር 11 ላይ እንዲህ ይላል « [ሰብአ ሰገል] ምን ጊዜ ተነስተው ምን ጊዜ ደርሰዋል ቢሉ ለልደት ሁለት አመት



ሲቀረው ተነስተው የልደት ዕለት ደርሰዋል። ይህ በምን ይታወቃል ቢሉ ኤጲንዬስ 'ዮም ተወልደ' /ዛሬ ተወለደ/ ይላልና ሲሉ አበው ሚስጥራቱን ያጎሉበትን ክፍል እናያለን።

ሰብአ ሰገል ጌታ በተወለደበት ጊዜ የመድረሳቸው ሌላኛው ማነፃፀሪያና ማመሳከሪያ በጌታችን የስደት ወቅት መጥምቀ መለኮት ዩሐንስንም እናቱ ቅድስት ኤልሳቤጥ ይዛው አሸሽታው ነበርና ጌታና መጥምቀ መለኮትም የ6 ወር ያህል የእድሜ ልዩነት አላቸውና ጌታ የአርባ ቀን ሕፃን ሲሆን መጥምቀ መለኮት 6 ወር ሲሆነው ስደት ተጀምሮአል። በዚህም በበርሃ በነበረ ጊዜ እናቱ የምተቸበትን መጥምቀ መለኮት ዮሐንስን ጌታ ሚዳቆ እናት ትሆነው ዘንድ በበረሃም ሲኖር አንዲት ድንጋይ ቤቱ ትሆነው ዘንድ በታአምራት እንዳደረገለት በሚገልፀው የቤተ ክርስቲያን መፀሀፍ መመልከት ይበልጥ ስለ ነገሩ እውቀት ያስጨብጣል።

ስለ ዮሐንስ በሚገልፀው በገድሉ ላይ 7 አመት ከመንፈቅ ሲሆን እናቱ ኤልሳቤጥ ሞተች ይላል። ተአምረ ማርያምም እንዲሁ በስንክሳር ደግሞ ኤልሳቤጥ የሞተችው 7 አመት በበረሃ ውስጥ ከዮሐንስ ጋር ኖራ ነው (ዘመስከረም) ልዩነቱም 6 ወር ነው በዚህም ስደት የተጀመረው ጌታ ከ40 ቀን



www.ethiopianorthodox.org


መስዋእት ርግብ ከቀረበለት በኋላ ሲሆን ዮሐንስ 6 ወር ያደረገ ህፃን በነበረበት ጊዜ ነው የሚል ማመልከቻ አለው

በተአምረ ማርያም ወይም ከቅዳሴ ማርያም ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ከቁጥር 166 ገፅም 235 እንደምንረዳው ጌታችን በስደት ጊዜ በነበረ ጊዜ እመቤታችን ስለ ልጅዋ ጥምና ድካም የትዕማን ቤት ሄዳ ለመነች:: በዚያም የነበረችው እመቤቲቱ ፀባይሽ መጥፎ ቢሆን እንጅ አንቺን የመሰለ ከመጋረጃም መች በወጣ ነበር ብላ በማፌዝዋ ዬሴፍ አረጋዊ ቢገስፃት ኮቴባ የተባለችው ወደል ባርያዋ እመቤቴን ደፍሮ የሚናገረውን ይህንን ፍየል ጠባቂ አሳየዋለሁ ብላ መጥታ ዬሴፍን በጥፊ ቃጥታ ከእመቤታችን እጅ ህፃኑን ነጥቃ ወደ መሬት አውርዳ ጥላው አስለቅሳዋለች በተአምራቱ ኮቴባን እና እመቤቲቱን ሊረዱዋቸው የወጡትንም ጐረቤቶቻቸውን ሁሉ ዝንጀሮ ሰላደረጋቸው የገዛ ውሾቻቸው ከቤታቸው አባርረዋቸዋል::

ስለ እነ ኮቴባ ጠቅሶ ይህ ገፀ ንባብ የጌታን እድሜ 2 አመት ያደርገዋል በዚህም አንድምታውና ተአምረ ማርያም (150 እና 270) የጌታን የስደት እድሜ 2 አመት ያደርጉታል



የጌታ እድሜ በስደቱ ጊዜ 6 ወር ነበር የተባለበትና በተደጋጋሚ አፀንኦት የተሰጠው ክፍል ምንጭ መፀሀፈ ስንክሳር ሲሆን ከጌታ ልደት ታህሳስ 28/29 ጀምሮ እስከ ግንቦት 24 (እመቤታችን ልጅዋን ሄሮድስ እንዳይገድልባት ከዮሴፍና ከስሎሜ ጋር ተሰዳ ግብጽ የገባችበት እለት) ያሉትን ወሮች በመቁጠር እንደሆነ ሰው ሊረዳ ይገባል:: ማንም ሰው ዘሬም ቢሆን የተወለደበትን ወር ይዘን እድሜው ይህን የህላል ብለን በሙሉ ቁጥር እንጠራለን እንጂ የተወለደው ታህሳስ 29 እድሜው 2 ወር ከሁለት ቀን በማለት የካቲት 30 ላይ ስላለ ህፃን አንናገርም ስለሆነም ከታህሳስ ጀምሮ እስከ ግንቦት ድረስ ስንቆጥር 6 ወሮችን እናገኛለን::




መግለጫ 3 :የጌታችን ከቤተልሔም ተነስቶ ግብፅ የሄደበት ስደት የወሰደው ጊዜ

ለነገር የተባ ሰው «ከታህሳስ 2 ቀን የያዘ ለግንቦት 6 ቀን የጐደለው ህፃን ነበር ጌታ በሰአቱ» ሊል ይችላል:: ወይም «5



www.ethiopianorthodox.org

ሙሉ ድፍን ወር ከ 26 ቀን አድርጓል» ሊልም ይችላል ምንም ቢሉ ምን ወደ 6 ወር ያደላ እንጂ ሌላ አይባልም::

እንደ ኢትዮጵያውያን የጥንት ባሕረ ሐሳብ የዘመን ዝርዝር (chronology) አመተ ምህረት የሚጀምረዉ የጌታ ልደት በሆነበት አመት መስከረም አንድ ዓ. ም ነው ስለዚህ 1ኛው አመተ ምህረት ታህሳስ 28 «ክርስቶስ ተወልደ» እንላለን:: ከዚያም 40 ቀን የኦሪት መስዋት ስዋ፤ ለ3 አመት ከ 6 ወር ስደት፤ በ4 አመቱ ወደ ምድረ እስራኤል መልስ ወይም ሞተ ሄሮድስ ሲል በ12 አመቱ ቤተ መቅደስ መግባቱን ሊቀ ከህናትን መጠየቁን እና ማስረዳቱን በ15 አመቱ ጢባርዮስ መንገሱን በ30 አመተ ምህረት ጥር 11 ጥምቀት በ34 ዓ.ም መጋቢት 27 ስቅለት ፤ በ317 ጉባኤ ኒቅያ ፤ በ 373 ጉባኤ ቁስጥንጥንያ፤በ423 ጉባኤ ኤፌሶን፤በ 444 ጉባኤ ቄልኬዶን (ከለባት) እያልን እንቆጥራለን::

ይህን ሁሉ ለማለት የተፈለገው ወደ አንድ ድምዳሜ ለመድረስ ነው:: ይኸውም ስለ ሄሮድስ ሞትና የአውሮፓውያኑ ዘመን መቁጠሪያ ሄሮድስ ሞተ የሚለው በ



4ኛው ቅ.ል.ክ (B.C) ስለ መሆኑ በደንብ እንድናጤን ተፈልጎ ነው::[1]

በወንጌል ደግሞ እንደምናነበው ሄሮድስ የቤተልሔምን ህፃናት ያስፈጀው ከሞተ በኋላ 4 አመት ቆይቶ ተነስቶ ሳይሆን አልቀረም ማለት ነው እንደ አውሮፓውያኑ ዘመን አቆጣጠር:: ይህ ከወንጌልና ከክርስቲያኑ ዘመን መቁጠሪያ ጋር የማይሄደው የምእራባውያን ዘመን አቆጣጠር እራሳቸው አምነውና መርምረው እያማጡ ጌታ የተወለደው በ6 ቅድመ ልደት ክርስቶስ ሳይሆን አይቀርም ብለዋል::[2]

---


1 Seven day Adventist Bible commentary (vol. 5) S.V Herods (review and herald publishing, 1956) p.42

2. -See the censes of Quirinius and the birth of Jesus of Nazareth, internet source.



www.ethiopianorthodox.org

ይህንንም ሲሉ ሄሮድስ የሞተው በ4 ቅ.ል.ክ ከሆነ እንደሁም የቤተክርስቲያ ህፃናትን ሲያስጨፈጭፍ ከ2 አመት በታች ያሉትን ግደሉ ካለ በኋላ ወዲያው ሞተ በማለት ወንጌልን እንኳን በቅጡ ለመረዳት ቸግሮአቸው በውል ሲዳክሩና ሲቃዡ ይስተዋላሉ:: እንደነርሱ አባባል የዘመን አቆጣጠሩ በዘመን መስመር ላይ ይህንን ይመስላል::




መግለጫ 4 :-የምእራባዊያኑ የዘመን አቆጣጠር ከጌታ ልደት ጋር ሲያነፃፅሩ

ስለዚህ ጌታ በ6 ቅድመ ልደት ወይም ዘመነ እግዚእ ሳይወለድ አልቀረም ይሉናል:: በነገራችን ላይ ግን ወንጌሉ ሄሮድስ የቤተልሔምን ህፃናት እንዳስገደለ ሞተ ይላልን? ጌታ ከስደት በተመለስ ጊዜ እድሜው ስንት ነበር? ለስደት ሲነሳስ እድሜው ስንት ነበር? የጌታ የስደት ዘመን የቤተልሄም ህፃናት ጭፍጨፋ በኋላ ለ2 አመት ነው ብሎ ለመደምደም በምን ማስረጃ ይችላሉ? በወንጌሉ ቃል (ማቴዎስ) ላይ እራሱ



ሄሮድስ ከሁለት አመት በታች የሚያህላቸውን ህፃናት ግደሉ ይላል እንጂ ሁለት አመት የሞላቸውን ህፃናት ብቻ አላለም ይህ ታዲያ ቅራኔ አልሆነባቸውም?

ከላይ ባየነው ሁናቴ ሄሮድስ ሞተ ብለው የሚናገሩትን አመት ያገኙት ከፍላቪየስ ጆሴፈስ ከተባለ የአይሁድ የታሪክ ፀሀፊ ስራ ሲሆን ጆሴፈስ ሄሮድስ የሞተው እንደጥንታውያኑ የሮማውያን አቆጣጠር ሮሜ ከተመሰረተች በ 750 አመት በኋላ ነው ሲል ያስቀመጠውን በመያዝ በሉቃስ ወንጌል ላይ ም1:3 :22-23 ላይ ጌታችን ስብከቱን ሲጀምር ጢባርዮስ ከነገሰ በአስራ አምስተኛይቱ አመት ነበር ሲል ገልፆ የጌታን እድሜ 30 በማድረጉ ይህንን ይዘው በመንደርደር ጢባርዮስ እንደ ጥንታውያኑ የሮሜ አቆጣጠር የነገሰው በ 765 ላይ ሲሆን አስራ አምስት አመት ተደምሮበት ወደ 780 ሲገባ ያም ላይ 30 አመት ሲቀነስ 750 ስለሚመጣ ዲዮናሲዮስ ኤክሲጀስ የጌታን እድሜ በጥናቱ ደረስኩበት ካለዉ ከ 753 (አንድ አመተ እግዚእ የሚቆጠረው 750 ጀምሮ እስከ 753) ላይ የአራት አመት ልዩነቶችን ያሳያል በሚል ነው::



www.ethiopianorthodox.org

በዚህም ጥንታውያኑ የሮሜዎች ዘመን አቆጣጠር አፈታት ላይ እራሱ ችግር እንደለ መረዳት ቀላል ነው እንዴት ነው የጌታ እድሜና የሄሮድስ ሞት የተገጣጠመው በማለት ጌታ ሲወለድ ሄሮድስ ሞተ ማለት አይሆንም ወይ ? የሚል ወሳኝ ጥያቄ መጋረጥ ያስችለናል ነገር ግን ዘመን አቆጣጠሩ የተዛባና በይበልጡኑ ደግሞ የጢባርዮስ የንግሥና ዘመን ያሳሳታቸው ስለመሆኑ ጥርጥር የለውም::

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን እውነተኛና ቀና አፈታት ጌታችን በእመቤታችን ጀርባ ታዝሎ ወደ ግብፅ እና ኢትዮጵያ ሲሰደድ ስድስት ወሩ ነበር:: በግብፅና በኢትዮጵያም እየተዘዋወሩ ምድሪቱን ባርከዋል:: ከ3 አመት ከ6 ወር በኋላ ሔሮድስ ስለሞተ የጌታችን መላእክ ወደ እስራኤል ምድር ይመልሳቸው ዘንድ ተገልፆ ዮሴፍን አዘዘው (ማቴ 1:19-23)

የጌታ የልደት ዘመን 3 አመት ከ6 ወር ነው የሚባለው በዮሐንስ እራኢ 12: 13-16 ጀምሮ ያለውን ገፀ ንባብ ሚስጢር በአንድምታ በተፈታበት መሠረት መሆኑን ባለፉት ክፍሎች አይተናል:: በዚህ ሁናቴ 6 ወር ከ3 አመት ከ6 ወር ላይ ሲደመር የጌታን እድሜ በሞተ ሄሮድስ ጊዜ ላይ



አራት አመት የደረገዋል በዚህ ላይ ሄሮድስ ሲሞት በአንድ ቀን ከጣና ደሴት ተነስተው ምድረ እስራኤል መግባት ቢቻላቸውም ለጌታ ተድላ ሥጋ የለበትምና (ለተከታዮቹ ስደትን ይባርክ ዘንድ አምላክ እራሱ የሥጋን ፈተና ይቀበላልና) ምድረ እስራኤል ድረስ በእግር ተጉዘዋል:: የጌታን ሥደት ታሪክ እያብራራ የሚገልጸው ተአምረ ኢየሱስ ጌታ ከስደት መልስ ናዝሬት ሲገባ እድሜው 5 አመት መሆኑን ይገልፃል:: ተአምረ ኢየሱስ አስራ አራተኛ ተአምር ገጽ 49 ጌታ ወፎችን ከጭቃ ፈጠረ የሚለውን ተመልከት


ከላይ ባየነው ድምር 'ሞተ ሄሮድስ' የጌታ እድሜ 4 አመት ሲሆን የመጣ መሆኑን እንረዳለን እንጠነቅቅማለን::

ምእራባውያኑ የሄሮድስን ሞት ካገኙበት ወይም አገኘነው ካሉት ከጆሴፈስ አይሁዳዊ ዘመን ጥቆማ በመነሳት እና መመርመር መልካም ነው::ያ ደግሞ የሄሮድስን ሞት በ4 ቅ.ል.ክ. ያደርግባቸዋል:: ይሄ ደግሞ ለኛ ወሳኝ የሆነ መረጃችን ነው:: በወንጌል እንደተፃፈውና አሁን አለሙ ሁሉ እንደሚስማማው ሔሮድስ ከጌታ ልደት በፊት የሞተ ሳይሆን ጌታ እድሜው 4 ዓመት ሲሆን የሞተ መሆኑን ከላይ እንዳየነው ተረጋግጦአል አቆጣጠሩንም ከላይ አይተነዋል::



www.ethiopianorthodox.org

ይህ ደግሞ ሲተነተን አውሮፓውያኑ አንድ አ.እ ወይም (Anno dominie) ብለው መቁጠር የጀመሩት ጌታ እድሜው ስምንት አመቱ ሲሆን ነው ለማለት ያስችላቸዋል እነርሱም ይህንን መረጃ ይዘው በቅጡ ሳይመረምሩት ሊታበዩ ይፈልጋሉ ነገሩ ግን ከዚያ በጣም የተለየ መሆኑን እንመልከት። ይህ በንፅፅር ሲታይ ይህን ይመስላል።




መግለጫ 5 ፡-ክርስቲያናዊውና ጎርጎሪያዊው ዘመን አቆጣጠር ልዩነት

ይህ ማለት ጌታችን ሄሮድስ እስኪሞት አራት አመት የነበረ ሲሆን ሄሮድስ ከሞተ በኋላ በጐርጐርያውያኑ ዘመን መቁጠሪያ አራት አመት ድረስ ቅድመ ልደት ክርስቶስ ሆኖ የሰነበተበት ዘመን አለ። እነዚህን 4 ( የጌታ እድሜ ) 4 ሄሮድስ ከሞተ በኋላ ያለው ያልተቆጠረ አመት ሲደመሩ የ8 አመት ልዩነት ያመጣሉ።



እንደ ዲዮናሲዮስ ስህተታዊ ግምት ጌታ ተወልዶአል ሲል ያስቀመጠው አመት ከእውነተኛው ልደት በ8 አመት የቀደመ ሲሆን በ4 አመት ወደ ኃላ ቢያወርደው ሞተ ሄሮድስን እንደገና 4አመት ወደ ኃላ ቢያወርደው የጌታን ልደት ይደርስበት እንደነበረ ማወቅ ያስፈልጋል ዲዮናሲዮስ በ532 ዓ.እ ላይ የጌታ ልደት ከሆነ ዛሬ 532 አመት ነው ያለበት ጊዜ ላይ 8 አመት የግድ ሊቀነስ እንደሚገባው ከላይ አይተናል ስለሆነም እርሱም 532 ያለው አመት በእርግጥ 524 ነበር። የ 8 አመቱ ጭማሪ ስህተት ተጠያቂ ዲዮናሲዮስ ሲሆን ባለማረም ያላስተካከሉት ደግሞ የአሁኑ ዘመን ምዕራባውያን ናቸው።


ለመሆኑ ጌታ ከመወለዱ በፊት አራት አመት ሄሮድስ ሞቶ ነበር ብሎ የሚያሳያቸው ዘመን መቁጠሪያና ለዘመናት ስለ አቆጣጠራቸው አንድስ እንኳን በጥበብ ጉልህ ስህተቱን አለማሳየቱ አውሮፓውያኑ ለመፅሀፍ ቅዱስ ምን ያህል ዝቅተኛ ግምት እንደ ሚሰጡ እና የሚያወሩትንስ እንኳን እንዳላወቁ ያረጋግጣል።

ይህ ማለት ደግሞ ዛሬ ላይ በማስተዋል ስንመለከተው ጌታ ከተወለደ በኋላ እስከ 8 አመት ድረስ ያለውን ጊዜ አንዱ ብለው ሳይቆጥሩ ፈረንጆቹ ዘግይተው የተነሱ ናቸው። በማለት አንዳንዶቹ የነሱ ዘመን መቀጠሪያ ላይ 8 ዓመት የኛ ላይ 16 አመት መደመር አለበት ይላሉ። ሀሰቡ ግን እጅግ ስህተተኛ



www.ethiopianorthodox.org

ነው:: ምክንያቱም እኛ ስንቆጥር ሄሮድስ ከጌታ ልደት በፊት ሞቶአል አላልንምና በዚህም ስሌት ይህችን ስምንት አመት ስንመለከት የአፈ ታሪኩን የሮሜ ግንባታ አቆጣጠር እና የዲዮናስዮስ ስሌት ምን ያህል የተሳሳቱ መሆናቸውን እንረዳለን ስለ ሆነም የኛ ዘመን 2000 ሲል የፈረንጆች 2008 በማለት ይህቸን የ8 አመት ልዩነት በግልጽ ወጥታ ስትመጣ እንመለከታታለን የእኛ ዘመን አቆጣጠር በማስረጃ ሲታይ ይህን ይመስላል::




ማመልከቻ 6:- ክርስቲያናዊው የዘመን መስመር በጌታ እድሜ

ከላይ ያየነው የ7 አመት እና የ15 አመት ጭፍን መደመር የነጮችን (የጐርጐሪዮስና የዲዮናስዮስና ድርሰት አፈ ታሪካዊው የሮሜ ግንባታ ወደ ኋላ የሚቆጥር በማስመሰል) ትክክለኛ አመዘጋገብና ስህተት የሌለው የአመታት ምዝገባ ነው ከሚል መደምደሚያ የሚነሳ በመሆኑ በራሱ ውድቅ ሃሳብ እንዲሆን የደርገዋል ይህንንም በዝርዝር ቀጥሎ እናየዋለን::

ለክርስትናው ሃይማኖትና ባህል በጣም ቅርብ ትስስር ያለው የግብፅና የኢትዮጵያ ህዝብ ስለ ጌታ ልደት አመታቱን ከአሪት ጋር እያጣመሩ ለመቁጠር ይቀድሙ እንጂ አያንሱም ስለዚህ መላ የሌለውን የህፃናት ተረት ላይ የተመሰረተ



የዘመን መነሻ አድርገው ከሚቆጥሩ የዘመን መቁጠሪያዎች ይልቅ የኛው ዘመን መቁጠሪያ ስለሚበልጥ ነገሩን በጥንቃቄ መርምሮ 8 አመት ከምዕራባውያኑ ማንሳት የግድ ይላል:: ይህ ማለት ደግሞ ከምራባውያኑ 2008 ላይ 8 አመት ሲቀነስ 2000 ዓ.ም ይሰጠናል:: ይህንን በይበልጥ የሚያጠናክር መረጃ በሚቀጥለው ምእራፍ እናያለን::

ከዚህ ላይ ግን በአስተውሎ ሊመረመሩ የሚገቡ ብዙ የተወዛገቡና የተሳከሩ ታሪኮች እና የመፅሀፍ ቅዱስን መረጃ የማያስታርቁ አመቶች በምዕራባውያን አቆጣጠር ዘንድ አሉ:: እነዚህም፤


1ኛ በሉቃስ ወንጌል 3:22 ላይ ያለው የጌታችን መጠመቅና እድሜው ሰላሳ አመት ሲሆን ጢባሪዮስ ከነገስ 15ተኛይቱ አመት የመሆንዋ ጉዳይ

2ኛ በጥንታዊው የሮሜ አቆጣጠር መሠረት ጢባረዮስ በ765 ነግሶአል ስለሚባለው አቆጣጠር

3ኛ ሄሮድስ በ750 አመት ነው የሞተው የሚለውን ጥንታዊው የሮሜ አቆጣጠር ከግሪጐሪያውያኑ ጋር እንደገና: ሲመሳከር የሚያሳዩት ይህ ነው የማይባል ግራ የተጋባ እና የተመሳቀለ ልዩነት ነው:: በመጀመሪያ ነጥብ ብንጀምር በዘመን መስመር ላይ ሀሳቡ ሲቀመጥ ይህንን ይመስላል::



www.ethiopianorthodox.org




ማመልከቻ 7:- አመተ እግዚእ እና ጥንታዊው የሮሜ አቆጣጠር ሲመሳከር

ከላይ እንዳየነው በአሁኑ ሰአት ጌታችን ከ4 እስከ 6 አመት በፊት ተወልዶአል ወደሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል:: የሄሮድስ ሞት 750 ላይ የመሆን ምክንያት ወደ እዚህ ድምደሜ መድረሳቸው ዋና ምክንያት መሆኑም ይታወቃል:: በዚህ ስሌት መሠረትም 750 እስከ 780 ሰላሳ ዓመት እንደሚሆን መመልከት አያዳግትም ብሎም የጢባርዮስ ንግስናን 765 ከሆነ ደግሞ አስራ አምስት አመት እላዩ ላይ ሲጨመሩ 780 የመምጣቱንም ነገር ማወቅ ቀላል ነው:: ይህ ግን ከአመተ እግዚእ (AD) አቆጣጠር ጋር ሲቀመጥ ጭራሹኑ እየተሳከረ የሚሄድ መሆኑን መገንዘብ ይገባል በተለየያኝርም ሁለተኛውንም ነጥብ የሚነካ ስለሆነ አብሮ መተንተን ተገቢ ነው::

ጢባርዮስ በታሪክ አመዘጋገብ ነገስ ተብሎ የሚታወቀው በ14 አመተ እግዚእ ስለሆነ በቀጥታ በሮሜ አቆጣጠር በ766 ዓመት በመሆን ይተረጐማል ይህ ማለት ደግሞ ከ766 ላይ 15 ሲደምሩ 781 እንጂ ሌላ ቁጥር አይሰጥም በአጭሩ ለመናገር የጌታን ልደት በ750 (በሞተ




ሄሮድስ ዘመን ነው) ካልን የጢባሪዮስን ዘመነ ነግስና 766 ነው ካልን የጌታ እድሜ 31 በጥምቀቱ ጊዜ ልናደርገው ነው:: ይህ ደግሞ ወንጌሉን የሚቃረን ስለ ሆነ ስህተቱ ያለው በጢባርዮስ የንግስና ዘመን መሆኑን ብዙዎቹ ወደ ማመን ይመጣሉ:: ይህንንም የሚያብራሩበት መንገድ አለ:: እኒህም ሰዎች ጢባሪዮስ ከ13 አመተ እግዚእ ጀምሮ እንደገዛና ሙሉ ባለ ስልጣን በመሆኑ የንግስናው ዘመኑ አስራ አራት ይባል እንጂ በአስራ አራት አ.እ የአውጉጦስ ሞት በመሆኑ እንዳሁ በቀድሞው ስልጣኑ ቀጥሉብትል ይህ አስራ አራት አመተ እግዚእ ስለዚህ የሚዘግበው የአወግስጦስን ሞት እንጂ የጢባሪዮስ ንግስና በ13 አመተ እግዚአ ነው የሚል ሃሳብ ነው:: ነገር ግን በዚሁ ሀሳብ ላይ ደግሞ ብዙ ስህተቶች አሉ:: እነኝህም የሚከተሉት ማመሳከሪያዎች ናቸው::

ጢባሪዮስ በነገሰ በ15ኛይቱ አመት ጌታችን እድሜው ሰላሳ ከነበረ ጢባሪዮስ ሲነግስ ጌታ እድሜው እኩሉን ወይም 15 አመት ነበር ማለት ነው:: ይህ ደግሞ ከ765 ላይ ሲቀነስ (15 አመት) ወደ 750 ያመጣናል:: ይህ ደግሞ ጌታ ሲወለድ ሄሮድስ ሞተ ማለት ነው:: ቅድም በዘመነ እግዚእ ላይ ጢባሪዮስ በ13 ቢሉ በ14 አመተ እግዚእ ነገሰ የሚለው ላይ የግድ 4 አመት ጨምሮ ከ753 የተነሳውን የዲዮናስዮስ አቆጣጠር ወደ 750 መመለስ መደመር ግድ ይላል:: ሊደረግም በዘመን መስመር ላይ ይህንን ይመስላል::



www.ethiopianorthodox.org





ማመልከቻ 8: የጥ.ሮ.አ ከአመተ እግዚእ ጋር ከጌታ ልደት ካሉት ዘመን ሲነሳ (ድ.ል.ክ.ማለት ድህረ ልደተ ክርስቶስ)

በዚህም (ሞተ ሄሮድስ) ወይም የጌታ ልደት 750 የተባለው ተፍልሶ 751 ይሆናል:: የለም 750 የተወለደበት ስለሆነ አንድ ብለህ ቁጠር ለሚል ደግሞ የጢባሪዮስ ንግስና በ764 ጥንታዊ የሮሜ አቆጣጠር (ጥ.ሮ.አ) ላይ ይመጣል:: ይህ ደግሞ የጢባርዮስ ዘመነ ንግስና የተባለው ጋር ችግር እንዳለበት አመላካች ነው:: ምክንያቱም (ከሙሉ ቁጥር 750 ጀምሮ እስከ 759) በየትም ዘመን አቆጣጠር ላይ ተነስቶ ሲቆጠር አስር አመት መሆኑን ከመረዳት ጋር ተያይዞ ጌታ በ 750 ጥ.ሮ.አ ከተወለደ 750 አንድ አመት ተብሎ የሚጠራ በመሆኑ ነው:: ይሄ ደግሞ የጌታን እድሜ በ15 አመቱ ላይ በጥንታዊው የሮሜ አቆጣጠር ወደ 764 ያመጣዋል::

በመጨረሻም እነዚህን አቆጣጠሮች ማለትም በ750 የጌታ ልደት ነው ብሎ በሚያስበው ጥንታዊው የሮሜ አቆጣጠርና ዘመነ እግዚእ ወይም ጎርጎሪያዊው ዘመን አቆጣጠር በዘመን መሰመር ላይ አብረው በተነፃፃሪ ሁኔታ ሲቀመጡ ይህን ይመስላሉ






ማመልከቻ 9:- ሶስቱ የጌታን ልደት ዘመን ከተለያዩ አቆጣጠሮች ጋር እንዲሁም የታሪክ ማመላከቻዎች ጋር የሚያሳይ

ከዚህ ጋር በግልፅ የሚታየው የምንገነዘበው ነጥብ ቢኖር የምእራባውያኑ ዘመን አቆጣጠር እርስ በእርሱ የሚጋጭ በመሆኑ ምንም አመኔታ ሊቸረው እንደማይችል እርስ በእርሱ ሲመሳከር በግልጥ ይታያል:: በተዘማጅ ደግሞ የኢትዮጵያው ዘመን አቆጣጠር ትክክለኛ ነው ሲባል በዚህ ውስን ማስረጃ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ጠንካራ መረጃዎች ጭምር የተደገፎ ስለሆነ በሚቀናለው ምእራፍ ይህንኑ እናያለን::



www.ethiopianorthodox.org

እዚህ ላይ ለማከል ያህል የዮልዮስ ዘመን መቁጠሪያ እንደ ጎርጎሪያውያኑ በ42 ቅ.ል.ክ. አንድ ብሎ የተጀመረ ነው የሚለውን ይዘን ዲዮናሲዮስ በ532 አ.እ ላይ የጌታ ልደት አመት ብሎ ያሰተማረውን ትምህርት የቆጠረበት የትኛው እንደሆነ ማለትም በጥንታዊ ሮሜ ይሁን በዩልዮስ ወይም በዲዮናሲዮስ አንድ እያሉ የቆጠሩበትና የሚያመሳክሩበት ዘመን መቁጠሪያና ዘመን አቆጣጠር በይበልጥ ውሉ የጠፋ ባሕረ ሐሳብ እንዲኖራቸው ምክንያት ሆኖአል ዩልዮስ አንድ አመት ብሎ የቆጠረውን ዛሬ ላይ ለማግኘት ብሎም በዚያ ሲቆጥሩ የነበሩትን (ጥ.ሮ.አ) ምእተ አመታት በመያዝ እስከ ዲዮናሲዮስ ደርሶ እርሱ ዩልዮናዊውን ወይም ጥንታዊውን ሮሜ ዘመን መቁጠሪያን ለታሪክ አካሄድና ለምርምሩ የትኛውን እንደያዘ ለመረዳትና ለማወቅ በጣም ይቸግራል:: በእውነትም ግራ ያጋባል!

ይህንንም አመት እስካላወቁ ድረስ ብሎም የጥንታዊ ሮሜ አቆጣጠር ቀርቶ ዩልዮስ የተካው እና የተሰራበትን ዘመን ካልተረዳን ወደ ድምዳሜና ግልፅ አቆጣጠር መምጣት አይቻልም::

እንደ አንድምታ ወንጌል ዘሉቃስ ም3 ቁጥር 1-2 ሌላ ልዩ የሆነ የጌታ ልደት ማመልከቻ ተቀምጦአል ይኸውም እንደ አቡሻከር አጉስጦስ (ኢክቴቪያን) በነገሰ በ42ኛው አመት ጌታ ተወለደ ሲል የአውግስጦስ ንግስና በ43/42 የነበረው



ሁለተኛው ትሪውምቪራ (ሶስትዮሽ ግዛት) የሚጠቀም ይመስላል ከዚህ አቆጣጠር ጋር አያይዞ አውግስጦስ ንጉሰ ነገስትነቱን ደርቦ በያዘ ጊዜ ማለትም ተቀናቃኝ ወይም ግዛት ከፍሎ የሚገዛ እንደ ማርክ አንቷን ያለው በጠፋለት ጊዜ ይህም በ27 ቅ.ል.ክ ላይ አስራ ስምንት አመት ሲደምሩ (ሲቆጥሩ) የጌታ ልደት አመት ነው ይላል





ማመልከቻ 10:- ከላይ የተጠቀሰው ዘመን ከጎርጎርዮስ አቆጣጠር ጋር ሲነፃፀር

ከ26 ቅ.ል.ክ ላይ 18 አመት ሲቀንሱ (ቅ.ል.ክ ስለሚቀንስ) 8 ቅ.ል.ክ ትመጣለች (ይህችን የስምንት አመት መዘግየት ተመልከት) ነገር ግን ይህ ምልከታ 8 አመት ከምእራባዊው አቆጣጠር የተለየ ሆኖ ሲያሳየን ወደ ኋላ የዘገየበት የራሱ የሆነ ምስጢር ያለው በመሆኑ ወደ አንድ ድምዳሜ ለመድረስ አስቸግሮአል:: እንደ ሄሮድስ ሞት ወደ ኋላ 8 አመት የሚያመለክት ይሆንን? በእርግጥም ከላይ ያየናቸው ሁሉ ይህንን የሚያወሱ ከሆነ ይህም ተመሳሳይ የሆነ ትርጓሜ ያለው ይመስላል ነገሩን ግን በጥልቅ በመመርመር አቡነ ቁርሎስ ይህን ያሉበትን ምስጢር በደንብ ማጥናት ይጠይቃል::




www.ethiopianorthodox.org

ይህ ማመልከቻ በዘመን መስመር ሲቀመጥ የሚከተለውን ይመስላል





ማመልከቻ11:- ጠቅላላ የአንድምታው የጌታ ልደት ማመልከቻ

በአንድምታው ላይ በንፅፅር የተቀመጡ ሶስት ማመልከቻዎች አሉ:: እነሆም የመጀመሪያው በሉቃስ ወንጌል ላይ ያለው ጌታ በጥምቀቱ ዘመን 30 ሲሞላው ዮሐንስ መጥምቅ ዘመኑ 30 አመት ከመንፈቅ ሲሆን ያለው ጋር አያይዞ ጢባሪዮስ በነገሰ በ15ኛይቱ አመት የምትለውን ይዞ «ጌታ ከአውጉስጦስ ዘመነ ንግስና 15 አመት ከጢባሪዮስ ዘመነ ንግስና 15 አመት ያመጣል::» ይላል ይህም በዘመን መስመር ሲታይ ይህን ይመስላል






ምእራባውያኑ ጢባርዮስን በ14 አ.እ ነገሰ ሲሉ አውጉስጦስ በ 14 አ.እ ሞተ ይላሉ ሁለተኛው ማመልከቻ የአውጉስጦስ ዘመነ ንግስና በጠቅላላው 56 አመት ነው ከዚያም ዘመን ውስጥ እርሱ (አውጉስጦስ) በነገሰ በ42ኛይቱ አመት ላይ ጌታ ተወለደ የሚል ነው:: ይህም 41 አመት ሲሆን እርሱ ከነገሰ በኋላ ያለውን አንድ ሁለት፣ እያሉ ሲቆጥሩ ይገኛል ማለት ነው::





ማመልከቻ12:- አውጉስጦስ የገዛበት ዘመን ከጌታ ልደት ጋር ማነፃፀሪያ

ሶስተኛው ማነፃፀሪያ ቅዱስ ቄርሎስ የተናገረው ሲሆን እርሱም ብፁእ ቅዱስ የሆነ የክርስትናን ሀይማኖት ጠባቂ የተዋህዶ አርበኛ የትሩፋትና የገድል መምህር ሊቀጳጳስ ዘ እስክንድርያ ነው:: አቡነ ቄርሎስ እንዳስተማረው አውጉስጦስ ንጉሰ ነገስት ከተባለ በኋላ አስራ ስምንት አመት (ይህም ንጉሰ ነገስት የተባለበት አመት ተቆጥሮ ነው) ሲቆጥሩ የሚያገኙት ነው ይላል በዘመን መስመር ላይ ይህ ሲቀመጥ ይህንን ይመስላል




www.ethiopianorthodox.org




ማመልከቻ13:- የቅዱስ ቁርሎስ ማመልከቻ

ምእራባውያን በ42 ቅ.ል.ክ አውጉስጦስ ትሪውምቪራ በሚል ሶስትዮሽ ከማርክ አንቷንና ጋር ነገሰ ሲሉ በ27 ቅ.ል.ክ ላይ ደግሞ ተቀናቃኞቹ ጠፍተው ንጉስ ነገስት ወይም አምባገነን ተባለ በማለት የሚቀጥለውን ዘመን መስመር ያስቀምጣሉ::




ማመልከቻ14:- የግሪጎርያን አቆጣጠርና የአውጉስጦስ ህይወት

በዚህ አዲስ ማመልከቻ ከጎርጎርያውያኑ ጋር ያለው ልዩነትን በአግባቡ ለመረዳት አቡሻከርንና የቅዱስ ቁርሎስን ድርሰት በሚገባ ማጥናት ያስፈልጋል:: ስለሆነም ለወደፊት ምርምር እንዲደረግበት የማመለከት ሥራን ይህ ፅሁፍ በማሳየት ለወደፊት የምርምር መንደርደሪያ ሊሆን ይችላል::



# ምዕራፍ ዘጠኝ

# የቅዱስ ሉቃስ ወንጌል ታሪካዊ ማመልከቻና አይሁዳዊው

## ጆሴፈስ የፃፈው የአይሁድ ታሪክ

በመፀሀፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ጌታችን ልደት በጥልቀት ከፃፉት መካከል ቅዱስ ማቴዎስና ቅዱስ ሉቃስ ተጠቃሽ ናቸው:: ቅዱስ ሉቃስ በወንጌሉ ምዕራፍ 2 ቁጥር 1 ጀምሮ እንደተፃፈው «በሮሜ አውግስጦስ ቄሳር ነግሶ ሳለ በሶሪያ ቄሬኔዎስ ደጃዝማቹ (ገዢ) በተባለበት ጊዜ ከቄሳር ትዕዛዝ ወጣ ይህም የእስራኤል ሰው ሁሉ ይቆጠር ዘንድ የሚያዝ ነበር::» ይላል በዚህ ገፀ ንባብ ዋና ተጠቃሽ የታሪክ ማመላከቻ ቄሬኔዎስ በሶሪያ ደጃዝማች በሆነ ጊዜ የሚለውና ከቄሳር ሰው ሁሉ ይቆጠር (ይፃፍ) ዘንድ ትዕዛዝ ወጣ:: ይህችም የመጀመሪያይቱ መቆጠር (መፃፍ) ናት የሚሉት ሀረጐች ናቸው::

ጆሴፈስ የሚባል በ32? [1] አመተ እግዚእ እስከ 100 አመተ እግዚእ እንደኖረ የሚነገር አይሁዳዊ ሰው ነው::

---

1. የጥያቄ ምልክት መኖሩ የምእረባውያኑን አቆጣጠር ስህተተኛነት የሚያሳይ መሆኑን እና አመታቱ በትክክል የተመዘገቡ እንደይደሉ ያመለክታል



www.ethiopianorthodox.org

ይህ ሰው በመጀመሪያው አመተ ምህረት ላይ ስለነበረው ሁናቴ፣ ስለ አይሁድ ጠቅላላ ታሪክ፣ ብሎም ስለ ጌታችን፣ ስለ የመጀመሪያው ህዝብ ቆጠራ እና ስለ ሄሮድስ ሞት የዘገበ የታሪክ ፀሀፊ ነበር::

ጆሴፈስ በ70? አመተ እግዚእ የእስራኤላውያን አመጽ እና የእየሩሳሌም ጥፋት ውስጥ መሪ ሆኖ የተሳተፈም ጭምር ነበር፡ በዮዳፋት የነበረው ምሽግ ውስጥ የነበሩት አይሁዳውያን ከሮሜ ጦር ጋር ተዋግተው የሞቱት ሲሞቱ የተረፉት እርስ በእርስ ተቀራደው ከመማረክ ሞትን በመረጡበት ሰዓት ጆሴፈስ እና ሁለት አይሁዳዉያን ብቻ መገዳደል እንደሌለባቸው ተማምነው እጃቸውን ለሮሜ ጦር ሰጥተዋል:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለሮማውያን ምርኮ በመሆን ከወገኖቹ ተነጥሎ መረጃ እየሰጠ በቁም እስር እስከ እድሜው ፍፃሜ ኖሮአል:: በመዘመኑም ብዙ መጽሐፍቶችን ጽፎአል::

ጆሴፈስ በፃፈው የአይሁድ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ጽህፈት ቄሬኔዎስ በሶርያ ተሹሞ ሳለ የተቆጠረ ሲሆን እንደ አውሮፖውያኑ ግሪጎሪያን አቆጣጠር በ7 ዓመተ እግዚእ እንደሆነ ያሳያል:: ይህ ደግሞ በመጀመሪያይቱ ጽህፈት (ቆጠራ) በ7 አመተ እግዚእ ከሆነ የምእራባውያኑ ዘመን መቆጠሪያ በ7 አመት ቀድሞ ሄዶአል ማለት ይሆናል:: ከላይ ባየነው መሰረት የግሪጎሪያኑ ዘመን መቁጠሪያ ባይታመንም



ይህን ቁጥር ወስደን ከኢትዮጵያዊው ዘመን መቁጠሪያ 2000 ዓ.ም./2001 ዓ.ም. ላይ ስንደምረው 2007/2008 ይሰጠናል ማለት ነው::[1] ይህ ማለት ደግሞ ምእራባውያኑ ጌታ ሲወለድ 7 አመተ እግዚእ ብለው ቆጥረዋል ማለት ነው:: ጆሴፈስ ባመላከተው መረጃ ደግሞ ከምራባውያኑ 2007/8 ላይ 7 አመት ስንቀንስ 2000/2001 ዓ.ም. እናገኛለን በዚህም የኛ ዘመን አቆጣጠር ትክክለኛ እንደሆነ የተረዳ ይሆናል::

ጆሴፈስ ስለ ጌታ የፃፈው አንቀፅ ደግሞ በይበልጥ ትኩረት የሚሰጠው ነው የእርሱ አገላለጽ ሳይዛባ እንዳለ ሲነበብ እንዲህ ይላል::

«በዚህ ጊዜ ኢየሱስ የሚባል የጥበብ ሰው ነበር» «ሰው» ነው ለማለት የምንችል ከሆነ ነው ምክንያቱም ታላላቅ ተአምራት ሰሪና እውነትን ሰባኪ ስለ ነበር አሕዛብንና አይሁዳውያንን በትምህርቱ ወደራሱ አምጥቶአቸው ነበር::

---

1. የኛና የግርጎሪያኑ ዘመን አቆጣጠር በ7 አመትና በ8 ይለያያል በኛ አዲስ አመት መስከረም ሲገባ በ7 አመት ግርጎሪያኑ ይቀድመን የነርሱ ጥር ላይ ሲውል በ8 ይቀድመናል በገና እለት አመት ያለመለወጣቸው ክርስቲያናዊ ዘመን አቆጣጠርን የተከተለ የአመት ለውጥ የላቸውም ያስብላል:: ስለዚህ በሁለት አመቶች (1999/2000 ወይም 2000/2001) እያሉ ማስቀመጥ ያስፈልጋል::



www.ethiopianorthodox.org

እርሱም ክርስቶስ ነበር ጲላጦስም ከኛ ሰዎች (አይሁዳውያን) መካከል ታላላቆቹ (ሃና እና ቀያፋ) በመከሩት ምክንያት በመስቀል ይሞት ዘንድ አዘዘ::
የሚወዱትም የሞተ መሰሏቸው ነበር (ደቀ መዛመርት) በሦስተኛው ቀን ግን ህያው ሆኖ ታያቸው ይህም ነብያት አስቀድሞ እንደ ተነበዩት ሆነ:: ከዚህ ውጭ አስር ሺህ የሚያህሉ ታምራቶችን እንደሰራና በርሱም የተጠሩ ክርስቲያን የሚባሉ ቡድኖች መመሰረታቸው እስከዛሬ ይታወቃል::» ይላል

ምንም እንኳን አንዳንዶቹ ይህ መጽሐፍና ጽሁፍ በክርስቲያኖች የተደረሰ ነው ለማለት ቢደፍሩም ቅሉ ግን ማንም ምንም ቢያደርግ ሊያዛባው የማይችል እንደ ብረት የጠነከረ ማስረጃያ ስለመሆኑ ግልጽ ነው:: አስር ሺህ ታምራቶች ከተባሉት ውስጥ በወንጌል፣ ተአምረ ኢየሱስ እና ተአምረ ማርያምን ጨምሮ ስንቆጥር የተጠቀሰውን ያህል እንደሚመላ መረዳት እንችላለን:: ከነዚህም አንዳንዶቹ ከባድ ከመሆናቸው የተነሣ ፍፁም እምነት የሌለው ሰው እንዳይደናቀፍ እና ሰውም ደግሞ ጎዶሎ ነውና እንዳይስት ቅዱስ ዮሐንስ እንዲህ እያለ መፃፉን ማስተዋል አለብን::
«ከዚህ መጽሐፍ ውጭ ደግሞ ያልተፃፉ ኢየሱስ ያደረጋቸው ብዙ ተአምራቶች አሉ» (ዮሐ. 20፣ 30-31) ኢየሱስ ያደረጋቸው ተዓምራቶች በሙሉ ተዘርዝረው ይፃፉ ቢባል ሰማይ እንደ ብራና ባህርም እንደ ቀለም ቢሆን ባልበቃ ነበር:: (ዮሐ. 21: 25)
ከላይኛው ጥቅስ ላይ ወንጌሉን «አንድ መጽሐፍ» ብሎ ሌላ መጽሐፍ አለ ያለው ተአምረ ኢየሱስን ሲሆን እርሱንም ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ ጽፎታልና ሌላ መጽሐፍ አለ ሊል ቅዱስ ዮሐንስ ችሏል::
ጆሴፈስ ይህንንም መረጃም በማቅረቡ ስለ እውነተኛው ዘመን አቆጣጠር ዋነኛው ምንጭ በመሆን ለአለም ባለውለተኛ ያደርገዋል:: ስለሆነም እርሱ ያስቀመጠው መረጃ ከኢትዮጵያውያኑ ዘመን አቆጣጠር ጋር የሚጣጣም እና የሚገናኝ እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ዘመን አቆጣጠር አመላካች ሊሆን እንደማይችል በቀላሉ መገንዘብ እንችላለን::



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ አስር

## አቡነ አውሳቤዎስ ስለ ጌታችን ልደት የገለፀው ማስረጃ

አውሳቤዎስ የቤተክርስትያን ታሪክ አባት ይባላል:: ይህም ስለ ወንጌልና ስለ ቤተክርስትያን ከክርስትና በአለም ሁሉ መሰበክ በኋላ አስፍቶና አጉልቶ ለመፃፍ ቀዳሚ ስለነበረ ነው:: እርሱም እንደ አንድምታ ወንጌል ትርጓሜ መግቢያ መጽሐፍ ቅዱስን በዘር፣ በአንቀጽና በምዕራፍ እንደቆጠረም ተጽፏል:: ትሩፋቱም ብዙ ከመሆኑም የተነሣ ርእሰ ሊቃውንት ሊባል ይገባዋል:: ዛሬ ድረስ በእርሱ ተጋድሎ መጽሐፍት እንዳይበረዝ፣ ዝንጋኤ ታሪክን ከማወቅ ወደ ኋላ እንዳያስቀረን አድርጓልና:: አውሳቤዎስ ስለ ጌታችን ልደት ያሰፈረልን መረጃ አለ:: ይህም መረጃ ስለ ጌታ ልደት ዘመን በሦስት ወገን ሲመሳከር ወደ አንድ አይነት አመት የሚያመላክት አድርጎ አስቀምጦታል::

አውሳቤዎስ እንደፃፈው ስለ ጌታችን የልደት ዘመን ይህንን ብሎአል::

« [ጌታችን የተወለደው] በአርባ ሁለተኛው አመተ ንግስና ለአውጉስጦስ እንዲሁም ግብጽ በገበረችበት እና አንቶኒ እንደሁም ኪሊዮፓትራ ከሞቱ በሀያ ስምንተኛው አመት ሲሆን የተሎሜ ስርወ መንግስት ያበቃበት ቄሬኔዎስ ደግሞ በሶሪያ ደጅአዝማች ሆኖ የመጀመሪያው ጽህፈት በተቆጠረችበት ዘመን ነው» ይላል

አውሳቤዎስ ያስቀመጠው መረጃ ከቀድሞ ምዕራፍ ጋር እንደታየው ቄሬኔዎስ በሶርያ ደጅአዝማች ሲባል የመጀመሪያው ጽህፈት (ቆጠራ) ሆነ ብሎ ያስቀመጠውን ሰባት አመተ እግዚአን ያካትታል::

በማስቀጠልም በአርባ ሁለተኛው አመት አውግስጦስ ከነገሰ ሲል ሌላ ወደ እዚሁ አመት የሚያመላክት አቆጣጠር ያስቀምጣል:: ብዙዎቹ እንደሚስማሙት አውግስጦስ በ27 ቅ.ል.ክ ነገሰ ብለው ይናገራሉ:: ነገር ግን ከዚህ በእጥፉ በራቀ ሁኔታ ታሪክ ሲያስረዳ በዚያን አመት የሮሜ ምክር ቤት (Senate) አውግስጦስ (Augustus) የሚለውን የክብር ማዕረግ እንጂ ሌላ እንዳላደረገለት ግልጽ ይሆናል:: አውግስጦስም ማለት «የከበረው» የሚል ማዕረግ እንጂ ከስልጣን ጋር የተያያዘ አይደለም:: በእላይኛው አመት 27 ቅ.ል.ክ ላይ ተነስቶ ቢቆጠር አርባ ሁለት አመት የጌታ ልደት በ14 ዓመተ እግዚእ ላይ ያደርገዋል ይህ ደግሞ ከመጀመሪያው ጽህፈት በ7 ዓመት የቀደመ ነው:: (በ7 ዓመት መቅደሙን ልብ በል) የሰባት አመት ልዩነቶች መኖራቸውን ካስተዋልን እንዲሁም ወደ ፊት 7 ዓመት የተሻገሩ (ቅድመ ልደት B.C.) ሳይሆን (በዓመተ እግዝእ A.D.) መሆናቸው ተያይዞ በኢትዮጵያዊያንና በግሪጎሪያውያን መካከል ያሉትን የቀደሙት ሰባት ዓመት



www.ethiopianorthodox.org

ልዩነቶች እንድናስተውል ያስገድደናል:: አውግስጦስ በመጀመሪያ ጊዜ በሮሜ ሀገር ልማድ እንደነበረው የምክር ቤቱ መሪ ተናጋሪ ሆኖና ንግስና በሚመስል ሁኔታ ታላቅ ሹመት የተሾመው ኮንሱል (Consul) በመባል በጥር (January) አዲስ አመት ከመግባቱ ጀምሮ በ34 ቅ.ል.ክ ጀምሮ ነበር::[1] እዚህ አመት ላይ 42 ስንጨምርበት ስምንት አመተ እግዚእን እናገኛ ለን:: ይህም ከላይኛው መረጃ ወይም ከመጀመሪያው ጽህፈት በሰባት አመት እግዚእ መሆን ጋር ይጣጣማል::

የኢትዮጵያውያንና የምዕራባውያን አቆጣጠር ልዩነቱ 7 እና 8 ዓመቶች መሆናቸው ዋነኛው ምክንያት እነርሱ ቀድመው ከታህሳስ 28 አንድ ብለው ጀምረው እዚያ ሲመለሱ አመት ሲያደርጉ (አመት ሲሞላላቸው) እኛ ደግሞ መስከረም አንድን እየጠበቅን አንድ አመት የማለታችን ጉዳይ ነው:: በዚህም እኛ ወይም እነርሱ ቀደሙ ለማለት 532 አ.እ. ላይ የተወሰነው አመትን ከእኛ ጋር አብሮ ማየት ያስፈልጋል:: ሁለቱ አመቶች ማለትም የኛ ዓመተ ምህረትና በዲዮናሲዮስ የተወሰነው አመትን አይቶ 7 አመት ወይም 8 አመት ልዩነት አለ ማለት ይቻላል:: አሊያ ግን በደፈናው የጠራው ልዩነት 7 አመት ወይም 8 ነው ለማለት ያስችግራል::

1. See the dictatorship of Julius Caesar, Jemes, Brestad; **Ancienit Times. The history of the old world** (Jim and company, 1916) p. 591; See also wikipedia the free encyclopedia S.V. **Augustus** p. 16



ሶስተኛው የአውሳቤዎስ መረጃ የጌታችን ልደት ሮማውያን ግብጽን ሙሉ በሙሉ ከተቆጣጠሩ በኋላ እና የክሊዮፓትራና የማርክ አንቶኒ ሞት በኋላ 28 ዓመቶች ሲደመሩበት የጌታ ልደት ዘመን ነው ብሎአል:: በአክቴቪያንና በአንቶኒ መካከል በተደረገው የባህር ላይ ውጊያ የግብጽ ሀይል የነበረው የአንቶኒና የኪሊዮፓትራ ጦር ተሸንፏል:: ይህ እንግዲህ የአክቲዮም ጦርነት በመባል ሲታወቅ በ31 ቅ.ል.ክ እንደተደረገ ይነገራል:: በአመቱ በተደረገ የግብፅ ወረራ (በ30 ቅ.ል.ክ) አንቶኒና ኪሊዮፓትራ በመሞታቸው ግብፅን የመቆጣጠሩ ስራን አክቴቪያን ይያያዘዋል::

በሂደቱ ግን በራሱ አጎት ከኪሊዮፓትራ የተወለደው ቄሳርዮን የተሰኘው ልጅ የስልጣኑ ባላንጣ እንደሆነ በመረዳት ከተደበቀበት ስፍራ አድኖ ለመያዝ ፍለጋውን አጧጧፈው:: በዚህም ድርጊቱ ላይ ጥያቄ ላነሱበት ሰዎች «ሁለት ቄሳሮች ለአለም ብዙ ናቸው አንድ ብቻ ይበቃል» በሚል ሽሙጥ የተቀመመ ነበር:: በአመት ወይም በሁለት አመት ውስጥ ገና ልጅ የነበረውን ቄሳርዮንን በመያዝ ሊገድለው ችሏል:: ይህ እንግዲህ ወደ 29 እና 28 ቅ.ል.ክ ያደርሰናል:: ነገር ግን ግብፅ የተረጋጋች ሀገርና ሮማውያን ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠሩዋት ለመሆን ብዙ ዘመን እንደሚፈጅ ግልጽ ነው ካለፉት ማስረጃዎች ላይ ስንነሣ የሚመጡት 7/8 ዘመኖች በየቦታው የማስገበር ትግል ቢካሄድበት የግብፅ መገበረ ወደ 20 ቅ.ል.ክ




www.ethiopianorthodox.org

ሊጠጋ ነው ማለት ነው:: ይህ እንግዲህ ጥልቅ የሆነ የጥናት ክፍል ሲሆን «ግብፅ ሙሉ በሙሉ የተያዘችበት ዓመት ይህ ነው!» የሚል ድምዳሜ እስካልተደረሰ ድረስ መረጃውን በቅጡ ለመተርጐም ይቸግራል:: ነገር ግን ወደ ታች እየወረደ (ከ30 በታች) መሄዱ ግን አያጠራጥርም ስለሆነም ከዚሁ ላይ 28 ዓመት ሲቀንሱበት 1ኛውን አመተ እግዚእን ያለፈ አመት እንደሚያሳይ እርግጥ ነው:: በመሆኑም የጐርጐርያውያኑ ዘመን አቆጣጠር ወደፊት የቀደመ ነው ለማለት ያስችላል:: በቀላሉ በሂሳብ አቀማመጥ ግብፅ በላይኛው ማመላከቻ ሲገመት በ20? ቅ.ል.ክ ብትያዝ፤20 ቅ.ል.ክ + 28 ዓመት = 8 አመተ እግዚእ ይሰጠናል ማለት ነው::

እነዚህ መረጃዎች ሁሉ በቀላሉ እንደሚያመለክቱት የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በትክክለኛው የጌታ ልደት ዓመት ላይ መመስረቱን ያረጋግጣሉ ይህ በሚቀጥለው ስዕላዊ መረጃ ሲቀመጥ የሚከተለውን ይመስላል::






*ስዕል 15፣ የአወሳቤዎስ የጌታ የሶስቱን ጌታ የልደት ዘመን እንዲሁም የታሪክ ማመልከቻዎች*



www.ethiopianorthodox.org

በነዚህ መረጃዎች መሠረት ምእራባውያን ጌታችን ተወለደ ብለው መቁጠር የጀመሩት በ7/8 ዓመት ቀድመው መሆኑን በግልጽ ያሳያል:: በዚህም የትኛው ዘመን መቁጠሪያ ትክክለኛ የትኛው ስህተተኛ መሆኑን መረዳት ይቻላል::



## ምእራፍ አሥራ አንድ

### ሊቁ ገማልያል ስለ የገሊላው ይሁዳ እና የፅህፈት ዘመን የተናገረው ማመልከቻ

በሐዋርያት ሥራ ምእራፍ 5 ከቁጥር 35-38 ላይ እንዲህ የሚል ቃል አለ::

«ስለ እነዚህ ሰዎች (ሐዋርያት) ምን እንደምታደርጉ ተጠንቀቁ:: ከዚህ ወራት አስቀድሞ ቴዎዳስ 'እኔ ታላቅ ነኝ' ብሎ ተነስቶ ነበርና አራት መቶ የሚያህሉ ሰዎችም ከእርሱ ጋር ተባበሩ:: እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበታተኑ እንደ ምናምንም ሆኑ ከዚህ በኋላ ሰዎች በተጻፉበት ዘመን የገሊላው ይሁዳ ተነሳ:: ብዙ ሰዎችንም አሸፍቶ አስከተለ:: እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበታተኑ::»

ገማልያል ይህንን የተናገረው አይሁድ በሐዋርያት ላይ መከራን በማፅናታቸው የተነሳ ነበር በዚያን ዘመን ሐዋርያት በታላላቅ ተአምራት ስራቸው የተነሳ ኢየሩሳሌም በትምህርታቸው እንድትሞላ አድርገው ነበር:: የኦሪት መስዋትና እምነት እያለፈ መሆኑን የተረዱት አይሁድ ሐዋርያትን ለመግደል እየተማከሩ ሳሉ ነበር ገማልያል የተሰኘ ው የኦሪት ሊቅ ከላይ ያነበብነውን ጥቅስ የተናገራቸው::



www.ethiopianorthodox.org

በጥቅሱ ላይ እንደምንረዳው 'የገሊላው ይሁዳ' የተባለው ሰው ሮማውያን የእስራኤልን ሰው ሁሉ ለግብር በሚቆጥሩበት ዘመን ተከታይ በማብዛት ለእግዚአብሔር እንጂ ለሮሜዎች ግብር ልንገብር አይገባም ብሎ ታላቅ ጦርነትን ከሮሜዎች ጋር አስነሳ ታሪኩን ፍላቪየስ ጆሴፈስ እንደዘገበው እንዲህ ይነበባል::

> «በዚያን ዘመን የአርኬላዎስ ግዛት የነበረው የይሁዳ ክፍል ወደ ወረዳ ደረጃ ዝቅ አለ:: ኮፓኒየስ የሮሜ ፈረሰኛ ጦር መሪ የነበረው የገዢ (ፕሮኩራተር) መአረግ ይዞ በሰዎችም ላይ የህይወትና የሞትን ስልጣን ከቄሳር በእጁ እንዲሆን ተቀብሎ መጣ:: ኮፖኒየስ በሚያስተዳድርበት ጊዜ አንድ ገሊላዊ ስሙም ይሁዳ የተባለ የሀገሩን ሰዎች ያሳምፅ ዘንድ ተነሳ እርሱም ለሮማውያን እንደ እግዚአብሔር ከገበራችሁ ፈሪዎች ናችሁ እንዴት ለተራ ሰዎች ትንበረከካላችሁ እያለ አነሳሳቸው» በማለት ታሪኩን ይገልፃል::[1]

[1] The war of the Jews books 2 chapter 8 section one; see also chapter 17 section 8 for the second quotation.



በዚህ ገፀ ንባብ ላይ እንደምንረዳው ኮፖኒየስ የተባለ የሮሜ ፈረሰኛ ጦር መሪ ስልጣን ሲይዝ በፀሀፊትም ይቆጠሩ ዘንድ ትእዛዝ ከቄሳር (አውጎስጦስ) ሲወጣ ከሶሪያ የሁሉ የበላይ የነበረው ቄሬኔዎስ ደጃዝማቹ ትእዛዚቱ መፈጸምዋን በሚቆጣጠርበት ወቅት ጌታ ተወልዶአል:: ይህንን ጊዜ ጆሴፈስ ሲገልፀው በ6/7 አ.ም. ላይ ነበር ብሎአል:: ይህ ገፀ ንባብ የሉቃስ ወንጌልን የጌታ ልደት መረጃን ከመሰከረ በኋላ ሌላ ከማቴዎስ ወንጌል ጋር የሚያያዝ ወሳኝ መረጃን በዚሁ መፅሀፍ ላይ በምእራፍ አስራ ሰባት ቁጥርም 8 ጆሴፈስ እንዲህ በማለት ይገልፀዋል::

> «የገሊላው ይሁዳ ልጅ ምናሴም ዋና የሆኑትን የአይሁድ ሰዎች ይዞ ወደ ማሳዳ ምሽግ አቀና (የገሊላው ይሁዳ አይሁድን ቄሬኔዎስ በፃፈበት ዘመን የወቀሳቸው እና እንዲያምፁ ያደረገው ነው:: እርሱም ዋና አታላይ ሲሆን እንደ ነብይ ለማስመሰል የሚሞክር ነበር:: አይሁድንም እንደ ነብይ ለማስመሰል የሚሞክር ነበር:: አይሁድንም ከሮማውያን በፊት ለእግዚአብሔር እንዲገብሩ እንዲገባቸው የሚናገራቸው ሰው ነበረ) በዚያም የነበረውን የንጉስ ሔሮድስን የጦር እቃ ግምጃ ቤት ሰብሮ መሳሪያውን ለተከታዮቹና ለወንበዴዎች አደለ:: እንደ ንጉስም ታጅቦ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ:: የአመፁም መሪ ሆኖ ከተማዋ እንድትከበብ ትእዛዝ ሰጠ:: ግንቡን ለመናድ ግን የሚያስፈልገው መሳሪያ አልነበራቸውም:: ወደ እርሱም

በተጠጉ ጊዜ የጦር ፋላፃዎች በላያቸው ላይ ከላይ ይለቁባቸው ጀመር (ሮሜዎች) በዚህም ምክንያት ከሩቅ በታ ጀምረው ውስጥ ለውስጥ መሬቱን እየቆፈሩ መሰረቱን ሊያናጉ ተጉ:: በመሰረቱም ላይ በደረሱ ጊዜ የሚቀጣጠል ጨምረው እሳት አነደዱ:: መሰረቱም ነዶ ሲያልቅ ግንቡ ፈረሰ:: ከውስጥ ያሉት ሮሜዎች ግን የሚያደርጉት ገብቶአቸው ሁለተኛ ግንብ ገንብተው ቆዮአቸው:: የሆነውንም ባዩ ጊዜም በጣሙን ተበሳጩ ከውስጥ የነበሩት አይሁዳውያንና የአመጽ ተባባሪዎቻቸው ከእነርሱ ጋር ይቀላቀሉ ዘንድ ሮሜዎቹን ስለወተወቱ ስለበዙባቸውም ይወጡ ዘንድ ፈቀዱላቸው የከተማዋም በር በተከፈተ ጊዜ ከውጭ የነበሩ የምናሴ ተከታዮች ወደ ውስጥ ዘልቀው ገቡ:: የሮሜ ወታደሮችም ተስፋ ቆርጠው ሀሞታቸው ፈሶ ነበር:: እየሸሹም ወደ ቤተ መንግስት ግንብ ገቡ የምናሴም ወገኖች የያዙዋቸውን ወታደሮች ገደሉ በመንደራቸውም ያለውን ዘርፈው አቃጠሉ::»

እንዲህም እያለ በጌታ ልደት ጊዜና በዋዜማው የነበረውን አመፅ ይገልፃል:: በዚህ መረጃ (evidence) እንደምንረዳው የገሊላው ይሁዳ በአመፀበት ዘመን ቁሬኔዎስ ቆጠራ የሚያደርግበት እንደሆነ ይታወቃል:: በሌላ በኩል ደግሞ ሄሮድስ ያልሞተና ገገር የነበረበት ዘመን መሆኑንም



እንመለከታለን:: ይህ እንዴት ይታወቃል ቢሉ «የንጉስ ሄሮድስ የጦር እቃ ግምጃ ቤቱን ምናሴ በሩን ሰብሮ መሳሪያውን ለተከታዮቹና ወንበዴዎች አደለ» ያለውን በማምጣት ይፈታል:: ሄሮድስ ሞቶ ቢሆን ኖሮ 'የንጉስ ሄሮድስ' ብሎ ግምጃ ቤቱን ባልጠቀሰም ነበር በዘመኑ የነገሰው ይወርሰዋልና የእርሱን ስም በጠራ ነበር:: አሊያም ሮማውያኑን ጠቅሶ በእነርሱ እጅ የነበረው የጦር ግምጃ ቤት ባለ ነበር:: ስለዚህ በሁለቱም ገለፃዎች ሉቃስንና ማቴዎስን በሚስጥራት ያስታርቃል:: ሉቃስ ስለ ቁሬኔዎስ፣ ስለ ጽህፈት (ግብር) ቢፅፍ ማቴዎስ ደግሞ ስለ ሄሮድስ፣ ስለ ሰብአ ሰገል ስለ፣ ጦር በኢየሩሳሌም መጠንከር ይፅፋልና ነው::

የጌታችንን ታሪክ ልብ ብለን በወንጌል ገላጭነት ከመረመርን ደግሞ በኋለኛው ጊዜ አይሁድ ታሪክ እየጠቀሱ ጌታን ለመክሰስ ይህችውን የፅህፈት ዘመን አመፅን ተጠቅመውባታል:: እንዴት ይታወቃል ቢሉ ጌታችን አይሁድን ስለ አምላክነቱ ቢናገራቸው ታሪክ ጠቅሰው ለተንኮል ለክህደት እና ለክስ ይቸኩሉ ነበር:: ለምሳሌም 'ጌታችን ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሶስት ቀን አነሳዋለሁ' ብሎ ስለ ትንሳኤው ልእልና ስለ ስጋው ሞት ቢናገር አይሁድ ታሪክ ጠቅሰው ዘሩባቤል 46 አመት የገነባውን እኛ 30 አመት ያነፅነውን ሄሮድስም 2 አመት ያደሰውን እና ያሳመረውን ቤተመቅደስ እርሱ በ3 ቀን እሰራዋለሁ ይፍረስ ይላል እንዲሉት ማለት



www.ethiopianorthodox.org

ነው:: (አንድምታ ወንጌል ቅዱስ ዘ ዮሐንስ ምእራፍ 2 ቁጥር 19 ጀምሮ ተመልከት) በዚህም ዘመን ማለትም ጌታችን በተወለደበት ዘመን የሆነውን ታሪክ ለሮሜ መንግስት በማስታወስ (ሉቃ 23:1-25) እንዲሁም ጌታችንን 'የገሊላው ሰው' ይሉት ነበርና (ዮሐ 7:42፣ 7:53) ይህም እንደ ይሁዳ ዘ ገሊላ ወይም እንደ የሀገሩ ሰው ይሁዳ በእናንተ ላይ አመፃን ሊያስነሳ ይሻል ብለው ከሮሜዎቹ ጋር ሊያጋጩት በመመኘት ግብርን ለቄሳር ልንገብር ይገባልን? ወይስ ለእግዚአብሔር? ብለው አምላካቸውን ሊፈትኑ እና ሊሸነግሉ ሲነሱ ይታያል (ማቴ 22:15-22)

የጆሴፈስ መፀሀፍ ዘመናትን የሚጠቁም እንጂ ሂደቱን በዘመን አስተካክሎ ወጥ ያደረገ ተከታታይነትን (Cronological) የጠበቀ መጽሐፍ አይደለም:: በመሆኑም ይህንን ያልተረዱ ሰዎች ይህ ፅሁፍ ክፍል የተጻፈው አርኬላዎስ በነገሰበት ዘመን ታሪኩ ስለሚጀምር ከዚያን ጊዜ አንስቶ ስላለው ብቻ ይፅፋል ይላሉ:: ነገሩን ሳስተዋለው ግን ጆሴፈስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጣጣም ወሳኝ ማስረጃ ጥሎ በማለፍ 'እፁብ እፁብ' እንድንል አስገድዶናል:: ይኸውም የገሊላው ይሁዳ ባመፀበት ዘመን ቄሬኔዎስ በሶርያ ገዢ ነበር ይላል:: አያይዞም የመጀመሪያው ጽህፈት በሆነ ጊዜ አመፅ ተነሳ ሄሮድስ ንጉሱ ያስቀመጠውን የጦር እቃ ግምጃ ቤት የይሁዳ ልጅ ምናሴ በሩን ሰብሮ ዘረፈው እያለ ወሳኝና ቁልፍ



የሆኑ መረጃዎችን በማስቀመጡ ዛሬ ላይ ተመራመርን ያሉ ምእራባውያን የወንጌሉን ነገር ለማጥላላት ብቻ ሲሉ ሄሮድስ በጽህፈት ጊዜ ያልነበረ ወይም የሞተ ነው በማለት ዘመን አቆጣጠራቸው ትክክል እንደሆነ ወንጌላውያኑም የተሳሳቱ ለማስመሰል የሚሞከሩበት ብዙ ድርሰቶችን ደርሰዋል::

ሀቁና እና እውነታው ግን በዘመኑ በነበረ የታሪክ ፀሀፊ እንደፃፈው ወንጌላውያኑ አንዱ የፃፈውን ሌላው ሳይደግመው እንደፃፈ ዋና ማስረጃና ምስክር ሆኖ ተገኝቶአል:: በዚህም የምእራብያውያኑ ግምትና ትምህርት (ስለ ዘመን አቆጣጠር) ህፀፅ የተሞላ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ እንረዳለን::



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አስራ ሁለት

## በዘመን መቁጠሪያው ላይ ያለ ተቃውሞ

በ1997 ዓ.ም. በአዲስ ትሪቢውን ጋዜጣ ላይ ስለኢትዮጵያዊው ዘመን አቆጣጠር አስመልክቶ የጋለ ክርክር ተካሄዶ ነበር:: ክርክሩ በሁለት አንጃዎች መካከል ሲሆን አንዱ ቡድን ዘመን መቁጠሪያው አስፈላጊ ነው:: እንዲሁም ትክክለኛ እና የባህላችንን ታላቅነት የሚገልጽ ነው የሚል ሲሆን ሌላኛ ው ደግሞ ዘመን መቁጠሪያው ኋላቀር፣ የተንቀራፈፈና ከአለም ጋር በአግባቡ እንኳን እንዳንግባባ መሰናክል የሆነ ነው የሚል ነበር::

በጋዜጣው ላይ ከተፃፉት ጽሁፎችና ፀሐፊዎች ማንነት ስንነሣ ግን ይህ የአሁጉራት ርቀት፣ የገንዘብ እጥረት፣ የሰዓት ጥበት ሳይገድባቸው በዘመን መቁጠሪያው የመቀጠል ወይም ያለመቀጠል እጣ የተከራከሩት ኢትጵያውያን ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ብቻ መሆኑ ከማሳዘን አልፎ ያስተክዛል:: ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮና ልማድ በወጣ ሁኔታ በእኛ ሀገር ላይ ብቻ ያለው የራስን ባህል ተቃዋሚ ኢትዮጵያዊ ማንነት አገር በቀልን ሁሉ አንጓጣጭ፣ የነጮች የበላይነትን እና የባህል ታላቅነት መስካሪና አድናቂ ሰው መፈጠሩ ለነገረው ለሀገሪቱ መጭ እጣ ተስፋ አስቆራጭ መንፈሳዊ ጦርነት ሆኖ በህይወታችን እና በህይወቴ ታዝቤዋለሁ::



ምንም እንኳን በአብዛኛው እኛ ኢትዮጵያውያን በባዶ ሜዳ ላይ ኩራት ቢኖረንም (ኩሩ ሕዝብ) ብንሆንም ቅሉ ዛሬ ዛሬ ይህ እንኳን ብርቅ ሆኖ የተፈጠረው ትውልድ ስለአገሩ እና ስለ ሕዝቡ ታላቅነት ለመመስከር እንደ ትልቅ ሞት ቆጥሮ ሲብከነከን ሲንገሸገሽ እናየዋለን:: ይህ ታዲያ ሁል ጊዜ በለመድናት «የቅኝ ገዢዎች ቅስም ሰባሪ» የምትለውን ሐረግ በቅጡ እንድንመረምር ሊያስገድደን የሚገባ ጉዳይ ስለመሆኑ አያከራክርም::

ብሎም በገሀድ ቅኝ ከተገዙ አፍሪካውያን ወንድሞቻችን ይልቅ ዛሬ እኛ መንፈሳችንን ለነጮች ባህልና አስተሳሰብ ተንበርካኪ መሆኑ ከየት የመጣ ነው? ብለን ጥልቅ ጥናት ማካሄድ ይገባናል:: ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ጃማይካዊነት፣ ከአፍሪካዊነት ይልቅ ፈረንጅ፣ ከአበሻ ይልቅ አረብ መሆንን የመረጡት የኛው ጉዶች በጉያችን ሲተራመሱ አይቶ እንዳላየ ማለፉ ነገ የማንነት ግጭት (Identity Crisis) ውስጥ የገባና ሀገሩን ከችግር ሊያወጣ የማይችል የባእዳን ምቹ መሣሪያ ትውልድ እንዲመሠረት ምቹ አጋጣሚ መፍጠር መሆኑንም ማወቅ ይገባል:: ያ ሆነ ማለት ደግሞ ነጫጮቹ ሆነ ሌሎቹ ለዘመናት ብራቸውን እየረጩ የተፍጨረጨሩለት አላማ ተሳካ ማለት ነው «ይማህረነ ክርስቶስ» ከማለት ውጭ ምን መፍትሄ አለ::



www.ethiopianorthodox.org

የአስራው ምዕት በዓል እንኳን ከመከበሩ ዋዜማ ላይ አንዳንድ አክራሪ ቡድኖች «ማን ተወለደ ብለን ነው የምናከብረው» ወይም «ይህ ዘመን መቁጠሪያ መላውን ኢትዮጵያዊ አይወክልም» ሲሉ ተደምጠዋል:: በፕሮቴስታንት አለሙና በኢትዮጵያም ያሉ ክፍሎች በአብላጫው የሚጠቀሙት የግሪጐሪያውያን ዘመን መቆጠሪያ እንደሆነም ይስተዋላል:: ምንም እንኳን «ማን ተወለደና» ለማለት ባይደፍሩም ቅሉ ትክክለኛ የዘመን መቁጠሪያ ነው ለማለት ግን እንደማይበረቱ እንገምታለን ከበረቱም ደግሞ እሰየው መልካም በርቱበት የሚያስብል ይሆናል::

ሌሎች ክፍሎች ደግሞ እራሳቸው ግራ የተጋቡና ሌላውንም ግራ የሚያጋቡ ናቸው:: ከላይ ኦርቶዶክሳዊያን ነን ይላሉ በሌላ በኩል ደግሞ የቤተ ክርስቲያኗን ትምህርት ይቃወማሉ:: ከላይ «ለኢትዮጵያ ሀገሬ ፍቅር አለኝ!» ይላሉ በገሀድ ግን የነጮችን የበላይነት ያስተጋባሉ:: ለዚያም ይሰራሉ:: የሀገረን ባህል ወግና ስልጣኔ ያንጓጥጣሉ ይቃወማሉ:: ባለፈው ምእራፍ እንዳየነው እንደነዚህ አይነት ክፍሎች ዘመን መቁጠሪያው ይቀየር እስከማለት ደርሰዋል::

እነዚህ ሁሉ ክፍሎች የሚያወሱት አንድ ሀሳብ አለ ይኸውም የኢትዮጵያ ዘመን መቁጠሪያ አለም አቀፋዊ ለሆነው የንግድ፣ የእውቀት እና የፖለቲካ ሂደት መገልገያ ባለመሆኑ ይህንን ዘመን መቁጠሪያ መጠቀም ወደ ኋላ የሚያስቀር



ወይም ከሰለጠነው አለም ጋር አብሮ የማያራምድ ዘመን አቆጣጠር ሆኖ ይይዘናል የሚል ነው:: እንደ እውነታው ከሆነ በአሁን ሰዓት ምእራባዊያን ባላቸው የፖለቲካ የምጣኔ ሀብት እና የጦር የበላይነት በመጠቀም በመላው አለም ዘመን መቁጠሪያቸውን በውድና በግድ እያሸከሙ አብላጫው የአለም ክፍል ተጠቃሚው ሊሆን ችሏል::

ዛሬ ላይ ዘመን መቆጠሪያቸው የተዛባ መሆኑን ሲረዱ «ኢየሱስ ክርስቶስ የሚባል ጭራሹን አልተወለደም» «ዘመን አቆጣጠራችን መታደስና አለመ አቀፋዊ እንጂ ክርስቲያናዊ መሆን የለበትም::» በማለት ያሳሳቱትን አለም በማደናገር ወደ ለመዱት የባህል ወራራና የአይምሮ የቅኝ ግዛት ውስጥ ለማስገባት በተራ ክህደትና ውሸት ሲቀጥፉ ይታያሉ:: [1]

ነገር ግን እንደ ቻይና፣ ጃፖን፣ እስራኤል፣ ኢትዮጵያ፣ ግብጽና ሌሎች እስላማዊ ሀገሮች ይህንን ዘመን አቆጣጠር የማይጠቀሙ መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል:: በዋናነት ግን ዘመን አቆጣጠራችን አንዳች እንኳን ከመሰልጠን የማያግደን መሆኑን በስርአት መረዳት አለመቻላችን ያሳዝናል:: ለመሆኑ ዘመን አቆጣጠር ከማደግና ከመበልፀግ ጋር ምን አገናኘው?

1 See Kenneth Harding **"Do any first century Historians mention the Jesus of Christianity** (Internet, 2002) p.p 1-3; J. M. Robertson, **The Silence of Josephus** (internet, N. D) pp. 1-4



www.ethiopianorthodox.org

የሚል ጥያቄ ብቻ ለእነዚህ ክፍሎች መወርወር እፈልጋለሁ:: የትኛውም ሀገር ከነበረበት አስከፊ የድህነት አረንቋና ማጥ ሊወጣ የቻለው ጠንክሮ በመስራቱ፣ ለህዝብ እድገት ተቆርቋሪ አመራር መኖሩ፣ የአገር ልማትን አስቀድሞ ከሙስናና ከግል ጥቅማ ጥቅም በፀዳ ሁኔታ የሚንቀሳቀስ ዜጋ በመብዛቱ ብቻ እንጂ በቀንና በወር አቆጣጠር የሰለጠነ ምንም ሀገር የለም:: ለኛም የሚያዋጣን ከእንቁ በላይ የሚበልጠውን ባህላችንን አጥብቀን ይዘን ወደ ስራ በመግባት በጥረት እና ያለማቋረጥ በመበርታት ለውጥ ማምጣት ብቻ ነው::

ካለፉት ምእራፎች እንደምንረዳው ከምእራባውያኑ ጎርጎርያውያን ዘመን መቁጠሪያ ላይ ከተገኘው የአሁኑ አመት ማለትም 2008 ላይ 8 ዓመት የቀደመበት ሲነሣ 2000 እንደሚመጣ ነው:: ይህ ደግሞ የኛውን ዘመን መቁጠሪያ ሌላው ሁሉ ቢቀር በጥቂት ማስረጃዎች (አንድም ይሁን) የታሪክና የሃይማኖት ፀሀፊዎች ባስቀመጡት ማመልከቻና ቅርስ መሠረት ትክክል መምጣቱን ማየት ችለናል::

ጎርጎሳውያኑ እራሳቸው ባደረጉት ምርምር ከነርሱ ጋር የሚገናኝም ወይም የሚቀራረብ ምንም አይነት ታሪካዊ ማመላከቻ አላገኙም:: ይህ እንግዲህ ታላቅነት መሆኑን ተገንዝበን ይሆን? ስንቶቻችንስ ይህንን ውድ ዘመን መቁጠሪያችንን በሚገባ እንጠብቃለን? እናከብርማለን? «ዘመን መቁጠሪያው ይቅር!» የሚለው ሀሳብ በቅጡ ሲያጤኑት



«በእጅ የያዙትን ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጥሩታል» የሚለውን የአበው ብሂል ያስታውሰናልና ይታረም እያልን ወደ መደምደሚያው እናመራለን::



www.ethiopianorthodox.org

## መደምደሚያ

ፀሀፊው ይህችን ጽሁፍ ለመፃፍ የገፋፋው ነገር ቢኖር በሀገር ውስጥ ባለው ፀጥታ ምክንያት ነው:: ይህ ፀጥታ ያልኩት ነገር ስለ ዘመን መቁጠሪያው ትክክለኛነት የማሳየትና የማስረዳትን ነገር ማንም ሲመሰክር ያለማዳመጥን ሁናቴ ለመግለጽ ነው:: የውጭ ሀገር ጋዜጠኞች በማያገባቸው ገብተው ስለ ኢትዮጵያውያን ዘመን አቆጣጠር ያሻቸውን ተናግረዋል:: በእኛ ዘንድ ደግሞ ምላሹ ፀጥታ ነበር:: በቅጡ ስለ ዘመን መቁጠሪያችን የሚያስረዱ አባቶች ጠፍተውም አይደለም:: አለም ሊደርስበት የማይችለውን መንፈሳዊ እውቀት የተቃኙ የጠሩ ሊቃውንት እነርሱ አለምን እረስተው አለምም በተለይ እነርሱን ረስታ እንደተርታ እቃ በየገዳማቱ በየበረሃው እየተሰደዱ የወደቁትን የት ዘንግተናቸው?

እኔ በበኩሌ ይህ ጽሁፍ ስለዘመን መቁጠሪያችን ሙሉ ማብራሪያ ይሰጣል የሚል ሀሳብ የለኝም ይልቁንም ትንሽ ነገር ይገኝ ወደ የማያልቀውና የማይጉድለው የአባቶች አንድምታ ለመድረስ ይህችን ጽሁፍ ጫጭሬ አባቶቼ በመልክ በመልኩ እያደረጉ ብራናውን እየዳመጡ ቀለሙን እየበጠበጡ መላውን ዓለም በዋናነትም እኛ ልጆቻቸውን በመገረም አፍ እንዲያስከፍቱ ማነሳሻ እንዲሆን ገፀ በረከት አድርጌ ለመስጠት እንጂ:: በአሁኑ ጊዜ «ሚሊኒየም» የሚለውን ቃልና በተያያዥ አመተ ምህረቱ የ2000 መሆኑን ያልሰማ ቢኖር ጥቂት ነው::



ስለዘመን አቆጣጠሩም ይህ ነው ብሎ ማስረዳት የሚፈልግ በመጥፋቱ ይህ ጽሁፍ ተዘጋጅቶአል:: ከብዙ በጥቂቱም የኢትዮጵያን ታላቅነት ይገልፃል ተብሎ ታስቧል ይህንን ስንል ታዲያ በአዲሱ አስራ ምዕት ወደ ጥንተ ሞገሳችን ለመሻገር እንጂ በባዶ ሜዳ እንደለመድነው ለመታበይ እንዳይደለ ተገንዘቡልኝ:: ለመሆኑ እንዴት ነው በአዲሱ አስራ ምዕት ለውጥ የምናመጣው? ብለን ብንጠይቅ መልሱ የሚሆነው መጀመሪያ ስህተታችንን አውቀን ማረምና በጎ ሰዎች ወደ መሆን መምጣት ስንችል ብቻ ነው::

በተገላቢጦሹ ግን ዛሬም ቢሆን ከትላንቱ የተለየ ምንም አላየንም:: ይህም ትላንት እንደነበረ እየተደራረበ ሄዶ ታላቅ ውድቀትን ወልዷል:: ድህነት እስከ አጥንቱ ዘልቆ የገባ ማህበረሰብ፣ በጭካኔ እየተረገጠ የሚኖር ገበሬ፣ የጭቃ ሹሞችና የመንደር ባለስልጣኖች መጫወቻ እንዲሆን የተፈረደበት በሚመስል ሂደት ለዘመናት ስንንፏቀቅ ከርመናል:: በዚህ ዘመን ደግሞ እድገት ማምጣት ሩጫው የሚደናቀፈው ከአገር ውስጥ እኛው በእኛው በምናደርገው ሹኩቻ ብቻ የሚፈፀም ሳይሆን ከአለም አቀፍ የምጣኔ ሀብትና የባህል እንዲሁም የፖለቲካ የበላይነትን ለማረጋገጥ በሚዳክሩ ሃይሎች የተንኮል መራወጥ ጭምር መሆኑ አሌ አይባልም:: «በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ» እንዲሉ ይህን አለም አቀፋዊ ተጽእኖ በመቋቋም «ድሀ ሆናችሁ፣ ባርነታችሁን አምናችሁ፣



www.ethiopianorthodox.org

ባህላችሁን ጥላችሁ፣ ማንነታችሁን ክዳችሁ ኑሩልን» ለሚሉን ሁሉ ምላሽ ሊሆን የሚገባው እንደነ ቻይና እና ህንድ እነርሱን የሚቀናቀን እና የሚፎካከር የሀገር ልማት በማምጣት ሊሆን ሲገባ የባሰውኑ አብዛኛውን ጥፋት ፍፃሚዎቹ እኛው ለእኛው መሆናችን ከማሣዘን አልፎ ያንገበግባል::

ዛሬ የእያንዳንዱ ሰው ህይወት በውጥረት የተሞላ ነው:: ሕዝባችን የቀን ውሎ የሌሊት አዳሩ ሁሉ በኑሮ ውድነትና፣ በስጋት፣ በፍቅር እጦት ነገ ስለ አለው ክፉ ቀን እየባዘነ የቁም ቅዥት ኑሮ ነዋሪ ሆኗል:: ከድጡ ወደ ማጡ እንዲሉ ተስፋ የሚሰጡ ፍሬዎች ባለማየታችን ሁሉችን ወደ ተስፋ መቁረጡ ድንበር ተዳርሰናል:: ይህ ሀገራዊ ቀውስን የመውሰድ ብቃት ያለው የምጣኔ ሀብት ድቀትና የገበያ አለመረጋጋት የፖለቲካ ትርምስን እንዳይፈጥር ብዙ መስራት የግድ ነው:: አሁን ወሬና ሽንገላን በመጠቀም ጥሩን ህይወት እገፋለሁ ያለ ሰው ካለ በጣም ተሳስቷል:: ይልቁንም አሁን ከጥላቻ ይልቅ መፈቃቀር፣ ከመበታተን ይልቅ መቀራረብ፣ ከሙስና ይልቅ ሕዝብን የሚጠቅም ስራ፣ ከልዩነት ይልቅ ልዩነትን በመነናገገር መፍታት፣ ከስልጣን ወንበር ላይ የሙጥኝ ከማለት ይልቅ ስልጣን ወደ ማጋራት አስተሳሰብ ልንመጣ ይገባል::



ያለበለዚያ ሁካታ፣ ግጭት እና ጥላቻ ላይ የተመሰረተ እንቅስቃሴ ማንንም ሰው ወደ ማይጠቅም ጎዳና ሀገርን ይወስዳል እንጂ አንድም ሰው እንኳን እንደማይጠቀም ግልጽ ነው:: እውነት ይመሰከር ከተባለ አንዳንዶች የተወለዱበትን ሀገርና ባህል ለከርሣቸው ሲሉ በመሸጥ በሆዳቸው እንደ እባብ የተሳቡ እና በመሬት ላይ እየተንከባለሉ ስለ ነጮች የዘመን አቆጣጠር የበላይነት፣ የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ኋላቀርነት የባሕረ ሐሳብ መጽሐፍት ጐደሎነት እናሳያለን ሲሉ ጽፈዋል:: ተናግረዋል:: መስክረውማል:: ሌሎችም ይሁዳዊ በሆነ ሰብእና ወገናቸውን እና ሀገራቸውን እንደቁም ከብት ለጥቂት ዶላር አሳልፈው ለመሸጥ የማይራሩ ሆነው ተገኝተዋል:: የባሰባቸው ደግዋ እራሳቸውን ለጊዜያዊ ጥቅም ብለው የምእራባውያን ርካሽ በህልና እርኩሰት ማጠራቀሚያ ገንዳ አድርገዋል:: ይህም አንዱ ኢትዮጵያዊ ለሌላኛው ጥላቻ እና ጥርጣሬን እንዲያተርፈ ታላቅ ምክንያት ሆኖአል::

ይህ እንግዲህ ምን ያህል ከሀገር ውስጥ በራሳችን ድክመት ከድንበር ውጭ ላሉ ጠላቶቻችን የተከፈትነው ክፍተት እንዳለ ያመለክታል:: አልፎ ተርፎ እያንዳንዳችን ጎራ ከፍለን ከመባላቱና፣ ከመጨቃጨቅ ውጭ ተቃራኒ የሆነውን ሀሳብ በጥሞና በማዳመጥ ሰፊው ህዝብን ሊጠቅም ወደሚችለውና አገርን ሊያሳድግ ወደሚችል ሐሳብ ላይ ብቻ በጋራ በማተኮር ስንረባረብ አይታይም::



www.ethiopianorthodox.org

ይህ ደግሞ ለጠላቶቻችን ምቹ አጋጣሚ ፈጥሮ የተያያዘውን ፍም በማራገባቸው በእያንዳችን ህይወት ላይ ስለነገው መራራ ቀን ከወዲሁ የነገሮችን ጉዞ በማየት እንድንጨነቅ አስገድዶናል። ስለዚህ ነገር በፍፁም ተአምራዊ ሚስጢር ከገለፀው ከትንቢተ(እንባቆም 3-7) ቃል በቀር ምን ብሎ መናገር ይቻላል። «የኢትዮጵያ ድንኳኖች ሲጨነቁ አየሁ።» ይህችን ቀን ለኔ መቼም ቢሆን ከዚህ ቃል ወጪ ሊገልጽልኝ የሚወደውን ያርቅልኝ።

የኢትዮጵያ ህዝብ በአለም ላይ ካለ ከማንኛውም ህዝብ ይልቅ ነፃነቱን የጠበቀ ታላቅ ህዝብ ነው። ይህም የተቻለው በራስ ስራና ሀይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ጽኑ ክንድ ነበር። የኢትዮጵያ ህዝብ የዚያን ያህል በአለም ውስጥ ካለ ከማንኛ ውም ሕዝብ ይልቅ በባንዳዎች የተጠቃና፣ የተረገጠ፣ የተንገላታና፣ የተዋረደ ስለመሆኑ ታሪክ ምስክር ነው። የሩቁን እንኳን ስንመለከት በጣሊያን የሚመራውን ዘመናዊ ጦር ያሣፈረ ሕዝብ ሀገሩን እና ወገኑን በምታውቀው ዮዲት የተፈታ ነበር። ከግራኝ አህመድ ጋር በመሆን እየመሩና እራሳቸው እየወጉ ከእርሱ ይልቅ ይህ ነው የማይባል ጥፋትን ያጠፉ «ክርስቲያን» የነበሩ ባንዳዎች ብዙዎች ነበሩ (ካስታንሆዞ ተመልከት) ከጣሊያንም መጥፋት መልስ በኂላ አርበኞች ተሸረው ባንዶች ስለተሾሙ አዝማሪው፣



«ኢትዮጵያ አገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ፤
የሰራልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ!»

ሲል ገጥሞ ዘመን የማይፍቀውን ምፀት እስከ ዛሬ ተክሎ አልፏል።

በውኑ የዚህስ አገር ባንዳዎች የተለዩ ናቸው ከሰው ዘር እንኳን የወጡ የማይመስሉ ባእዳን ፍጥረት (UFO) ይመስል ከህፃንነት እስከ ሽምግልና ባደጉበት ሕዝብ እና ሀገር፣ ወገንና ዘመድ፣ መንደርና ወንዝ፣ ወግና ባህል ላይ ይህ ነው የማይባል በደል ሲያደርሱ ከማየት በስተቀር የሚያሳዝን ነገር ምን አለ? ሌሎቹ ለእግዚአብሔር ክብር ለቤተክርስትያን ሞገስ ስጋቸውን ለረሀብ ሰውነታቸውን ለአረር በሰጡባት ሀገር ሌላው ደግሞ ቅዱሳን ንዋያቱን ለማዘረፍ፣ የእምነት አሻራውን ለማጉደፍ፣ ስበብና ምክንያት የሚፈልግ ብቻ ሆኖ ይገኛል። ከእርሱ ጊዜ በፊት ለም የነበረውን አፈር ሞልቶ የሚፈሰውን ጅረት ልምላሜ የተላበሰውን ምድረ ገነት ወደ በረሃ ለመቀየር የማይራራውንስ ምን ይሉታል? ከላይ ስታዩ የጠቆሩ ውስጣቸው ግን በለምጽ ነዶ ከገረጡ ከአፍሪካዊያንና ኢትዮጵያውያን ፈረንጆች እግዚአብሔር በምህረቱ ይሰውረን። «የወረት ፍቅር ለጊዜው ይደምቅ» እንዲሉ ነጮቹ አባቶች ለጊዜው የብርና የወርቅ ገፀ በረከት ቢያዥጎደጉዱ የድለላና የሽንገላ ቃላቶቻቸውን ቢዘሩ የጭብጨባና የሀሰት ከበሬታን ቢቸሩን ምን ይረባናል። በዚህ ምድር ሆነ በወዲያኛው ሰውን



www.ethiopianorthodox.org

መልካም ሥራው ብቻ ይከተለዋል ሕሊናው ደግሞ በስራው ሥራ እንዲዳኝ ያስገድደዋል: ታዲያ ነገሩ ይህ ሆኖ ሳለ ነጫጮቹ አታሞአቸውን ቢደልቁ በእጃቸው ቢያጨበጭቡ እሪታቸውን እያቀለጡ ዶላር ቢሸልሙን ምን ይጠቅመናል:: እንደ ሀምሌ ነጐድጓድ በምድሪቱ ላይ ያልፋል የኢትዮጵያም ድንኳኖች ሲጨነቁ ይኖራሉ::

ጨለማና መቅሰፍት፣ እረሀብ እና ጉርፍ፣ ጭንቀት እና ድህነት፣ እርዛት እና ጦርነት ያመሰው ማንነታችን ሁሉ ተወግዶ ኢትዮጵያ አረንጓዴ ምንጣፍ የተነጠፈባት የሰላም እና የእድገት፣ የብልጽግና እና የበረከት፣ የሥራ እና የፍቅር ሀገር እንድትሆን ሁሉም ሰው ዛሬ ላይ ቆሞ በሀቅና በቅን ልቦና በንፁህ ህሊና ሊጋደል ይገባል:: በአለም ላይ መልካም ሆነው ያለፉ ሰዎች ሁሉ ለወገናቸውና ብሎም ለሰው ልጅ በማሰብ በጐ ሥራን ያከናወኑት ብቻ ናቸው:: ሁላችንን እግዚአብሔር ይርዳን:: እንደእነርሱ ሰው ለመሆን!

## ተፈፀመ



## ዋቢ መጽሐፍት /Bibliography/

### 1) በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፉ መጽሐፍት


- Compton's Encyclopedia S.V. 'Calendar' Chicago: University of Chicago. 1983
- Horniblow and Sullivan, The March of time: Mighty men and Deeds London: 1999
- Breasted, James. (PHD). Ancient Times: A History of the Early World. Boston: Ginn and company. 1916
- Hitti, Philip. History of the Arabs. London: Macmillan press LTD. 1970.
- Jhosephus, Flavious. The wars of the Jews Vol. II.
- Harding, Kenneth. "Do any First century Historians Mention the Jesus of Christianity. (internet source: atheists of sillion valley home page)
- Shamuel, safari. The History of Israel from ancient times to the Modern formation. Jerusalem: 1973




www.ethiopianorthodox.org

- Sergew, Hable Sellassie. Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270. Addis Ababa: United printers. 1972
- Seven day Adventist Bible Commentary in Seven volumes. Vol. 5. S.V. 'Herod' USA: Review and Herald. 1956
- Taddesse, Tamrat. Church and State in Ethiopia 1270-1527. London: Oxford press.1972
- Trimingham, T. Islam in Ethiopia. London: Frank Cass, 1952
- Wikipedia the free encyclopedia S.V. Agustus casar
- World History (Vol. I) USA Armed forces Institute. Wisconsin: 1970




## 2) በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ መጽሐፍት


1. ሚኒሊክ መርእድ አለሙ፣ መጽሐፍ ቅዱስና ኢትዮጵያ፤ አዲስ አበባ፣ ኢሜጅ ፓብሊሺንግ፣ 1999 ዓ.ም
2. ሰማንያ ወ አሀዱ መጽሐፍ ቅዱስ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፣ 1995 ዓ.ም
3. ስንክሳር በግእዝና በአማርኛ፣ አዲስ አበባ ትንሳኤ ዘ ጉባኤ፣ 1995 ዓ.ም
4. አስራት ገብረ ማርያም እና ገብረሕይወት መሐሪ፤ የዘመን አቆጣጠር፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1984 ዓ.ም
5. በእምነት ምትኩ፣ የኢትዮጵያ ታላቁ ሀብት ባሕረ ሀሳብ (የዘመን አቆጣጠር)፣ ባህርዳር፣ ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ 1984 ዓ.ም
6. አንድምታ ወንጌል ቅዱስ በግእዝና በአማርኛ፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ 1988 ዓ.ም
7. ተአምረ ማርያም፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ማተሚያ ቤት 1996 ዓ.ም
8. ተአምረ ኢየሱስ፣ አዲስ አበባ ተስፋ ገብረሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ማተሚያ ቤት 1990




www.ethiopianorthodox.org

9. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአክሱም እስከ ዛጉዬ፤ አዲስ አበባ ፤ብርሃንና ሰላም ቀ/ኃ/ሥ/ማ/ቤ/ት፣ 1966 ዓ.ም

10. ጌታቸው ኃይሌ፣ ባሕረ ሐሳብ የዘመን አቆጣጠር ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋር፤ኮሌጅቪል፤ መጥምቀ ዮሐንስ ዩኒቨርስቲ፣ 1993 ዓ.ም

11. በሪሁን ከበደ፣ የዋልድባ ገዳም ታሪክ፣ አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1983 ዓ.ም



# እርማት

ገፅ- 16 ቁጥር 1 specific objective የተቆረጠ ነውና በአንድ ላይ ይነበብ
ገፅ-16 የመጀመሪያው ጥያቄ መጨረሻው ላይ "በእኛ ትክክል ይመጣል ወይ?" በሚል ይስተከል
ገፅ- 22 ያስፈልጋልስ የሚለው ወደ ያስፈልጋል[4]
ገፅ- 22 መጽሀፍ የሚለው በመጽሀፈ ይነበብ የመጨረሻው አንቀጽ መስመር 1
ገፅ- 24 ኢትዬጲያውያን የሚለው በኢትዮጵያዊያን ይነበብ አንቀጽ ሁለት መስመር 1
ገፅ- 24 የመጨረሻው መስመር ላይ "መሆኑን" የሚለው መውጣት አለበት አን.2 መ 10
ገፅ- 39 እርስችውን የሚለው በእራሳቸው በሚል ይነበብ አንቀጽ 1 መስመር 6
ገፅ- 42 አደም የሚለው በአዳም ይነበብ አንቀጽ 3 መስመር 3
ገፅ- 43 የስረዳናል የሚለው በያስረዳናል ይነበብ አንቀጽ 1 መስመር 4
ገፅ- 44 ስንተ የሚለው በሰንበተ ይነበብ ዳንኤል አንቀጽ 1 መስመር 1
ገፅ- 45 የደርገወዋል የሚለው በያደርገዋል ይነበብ 4 አንቀጽ 1 መስመር 8
ገፅ- 46 በሕረ የሚለው በባሕረ ይነበብ አንቀጽ 1 መስመር
ገፅ- 49 የ የምትለው ፊደል ከዲዮቅልጢያኖስ ላይ ጠፍታ ይነበብ
ገፅ- 52 የስጠናል የሚለው በይሰጠናል ይነበብ አንቀጽ 1 መስመር 2
ገፅ- 59 የተተመው የሚለው በየታተመው ይነበብ አንቀጽ 3 መስመር 3
ገፅ- 84 ተአምር የሚለው በተአምረ ይነበብ አንቀጽ 1 መስመር 7
ገፅ- 90 ማስመስከሪያው ተቆርጦ የመጀመሪያ መስመር በወዲያኛው ገጽ (91) ሆኖአል በመጀመሪያ መስመር ላይ ያለው ወደማጣቀሻው ገብቶ ይነበብ (It is part of the footnote)
ገፅ- 92 የተመለከተው የሚለውን በየተመለከተውን በሚል ይነበብ
ገፅ- 161 የምተችበትን የሚለው በየሞተችበትን ይነበብ 25 አንቀጽ መስመር 7
ገፅ- 111 አንዱ የሚለው በአንድ ይነበብ አንቀጽ 2 መስመር 2
ገፅ- 115 ሊደረግም የሚለው በሲደረግም ይነበብ አንቀጽ 2 መጨረሻ መስመር 1
ገፅ- 142 ስነገረው የሚለው በስነገው ይነበብ አንቀጽ 2 መስመር 9

www.ethiopianorthodox.org